# ምዕራፍ 11፤

## ሙሴና መሐመድ አይመሳሰሉም።

አያ ዲዳት ከወገኖችህ ልብ አድርገህ ስማ፣ሙሴና መሐመድ በምንም ነገር አይመሳሰሉም፤አንድ ነገድም አይደሉም፤እንዴታ?ትል እንደሆነ የሚከተሉትን ምክንያቶች አንብ፤

1. በዘር፣ከዚህ በፊት እንዳየነው፣ሙሴ እስራኤላዊ ሲሆን መሐመድ እስማኤላዊ ዐረብ [6]ነው። እስራኤላዊ የሚባል የያቆብ ዘር ብቻ ነው፤(ዘፍ.35:9-) ያቆብ ከሚሶጳጣምያ በተመለሰ ጊዜ እግዚአብሔር "ዳግመኛ ተገለጠለትና ባረከው። ደግሞም ስምህ ያዕቅብ ነው፣ ከእግ ዲህ ወዲህ ግን እስራኤል ትባላለህ እንጂ ያዕቅብ ተብለህ አትጠራም "እስራኤል"ብሎ ጠራው________።

ሙሴም ከወንድሞችህ መሃል ያላቸው ግብጽ ወርደው ተባዝተው፣ በሙሴ መሪነት ከግብጽ የወጡቱን የያዕቆብን የልጅ ልጆች እስራኤላውያን ነው እንጂ፣ከእነሱ ውጭ ወንድሞታችሁ ሊል በምንም ዐይነት አይችልም። ከዚያ ውጭ ያለውንም ጠላትህን ጥላ ወዳጅህ ውደድ ብሎ ሚና ለይቶ ተናግሯል። የእስራኤል አውራ ጠላትም ዐረብ እንደሆነ የዘመናችን ታሪክ ይመስክራል። ትንቢቱም የተነገረ ለይሥሐቅ ለያዕቆብ ዘር ነው። እስማኤል ዲቃላ ነው፤ያገባውም የአብርሃምን ነገድ ስላልሆነ የተስፋው ትንቢት ተከፋይ አይደለም፣ ዘሩም በተከታታይ በአብርሃም፣በይሥሐቅ አልተቆጠረም። በዲቃላነቱም እንደቄጡሩራ ልጆች ከይሥሐቅ ጋራ እንዳይወርስ ተሰዷል።

2. ይሥሐቅ የእመቤቲቱ የሣራ በሕግ የተገባችዋ ምሽት፣እስማኤል ግን አቤሜሌክ የሰጣት የሣራ ባሪያ የአገር ልጅ ነው። አጋር የሣራ እንጂ የአብርሃም ባሪያም አይደለችም። በዘመኑ ሥርዓት ወንድ ዘር መተካት ስላለበት ሣራ ስትመክን ጊዜ ከባሪያዩ ውለድ ብላ ሰጠችው እንጂ አብርሃም ያለ ሣራ ፍቃድ የወለደባት አይደለችም።

(ዘፍ.16:1-፤) ሦራይ ግን የአብርሃም ምሽት ልጅ አልወለደችም ነበር። ስሟን አጋር የሚሏት የምስር ባሪያ ነበረቻት። ሦራይ (ሳራይ) አብርሃምን አለችው። እነሆ!እግዚአብሔር እንዳልወልድ ከለከለኝ፣ወደ ባሪያዬ ግባ፣ምን አልባት ከእርስዋ ልጆች አገኝ እንደሆነ፣አብርሃምም ለሳራይ ነገር እሽ አለ። አብርሃም በከነዓን ምድር ዐሥር ዓመት ከተቀመጠ በኋላ፣ሳራይ የአብርሃም ምሽት የምስረቱን አጋርን ባሪያዋን ወስዳ ለአብርሃም ምሽት ትሆነው ዘንድ ሰጠችው። እሱም ከአጋር ደረሰ፣አረገዘችም። እንዳረገዘችም በአየች ጊዜ እመቤቷን አቃለለቻት። ሦራም አብርሃምን አለችው፣እኔ ካንተ እበደላለሁ። እኔ ባሪያዬን ላንተ ለብብትህ ሰጠሁህ፣እንዳረገዘችም ባየች ጊዜ እኔን አቃለለችኝ፣እግዚአብሔር በእኔና ባንተ መካከል ይፍረድ፣አብርሃምም

ሣራይን አላት፣እነሆ ባሪያሽ በእጅሽ ናት እንደወደድሽ አድርጊያት። ሣራይም መከራ አሳያቻት አጋርም ከፊቷ ኮበለለች። (ምዕራፍን ጨርሶ ያነቧል) የመሐመድ አባት እስማኤል የዚች ልጅ ነው።

3. የተሰፋ ልጅ አይደለም፤እስማኤል የተወለደው ማንኛቸውም ሰው በሚወለድበት በግብረ ወሲብ እንጂ እንደነ ዮሐንስ፣ ክርስቶስ በቃል ኪዳንና በትንቢት አይደለም። ለዚህ ግን ከዚህ በፊት የተጻፈውን (ዘፍ.14:15-21)ን ይመለከቷል። መሐመድማ እንዲያውም በሁለት ወጣቶች የወሲብ ፈቃድ መጣ እንጂ ከመጥፎ በቀር በጥሩ ትንቢት ይመጣል ተብሎ አልተነገረለትም።

4. በአስተዳደግ፤ሙሴ ከፈርዖን ቤት ስላደገ፣አስተዳደር፣የሰው ልጅን እኩልነት ግጥም አድርጎ ያውቃል፣መሐመድ ግን መጀመሪያም ጥጃ ጠባቂ በኋላም የነጋዴ ነረደማን በመሆኑ ያደገበት የኖረበት በጀኔራ ንነቱምጊዜ እየሳበው፣ሴትን የወንድ ታናሽ አድርጎ ጽፏል፤ አዝዝዋል ወንዱን በምሽቱ ላይ ያለመጠን አሠልጥኗል፣በውርስ ጊዜ ደግሞ ለወንድ ልጅ ዕጥፍ፣ለሴት ልጅ ግን ሢሶ አዝዝዋል፤ (ሱራህ:4:11) ከዚህም በላይ ሱራህ 4ን በሞላ ያነበበ የመሐመድን የሰው ልጅ መብት በስፊው ሊረዳ ይችላል፣ምንነቱንም ያረጋግጣል።

5. በእዮነት(በልምድ) ሙሴ ከግብጽ ቤተ መንግሥት፣ከፈርዖን ቤት ብዙ ነገር አይቷል። ለመሐመድ ግን ሕዝብ የመምራትና የሕዝብ ማስታደር ዕድል በልምድ አላጋጠመውም።

6. በትምህርት፣ሙሴ በመላ የግብጻውያንን ጥበብና የወገኖቹን የዕብራውያን ቋንቋና ዕውቀት ግጥም አድርጎ አጥንቷል፣መሐመድ ግን ግመል ከመንዳት በቀር ምንም አያውቅ ነበር። በዚህ ብቻ እንኳ ሙሴ መሐመድን እንደኔ ያለ ሊለው አይችልም።

7. <u>በጋብቻ፣በሕገ አውሰቦ፣</u> በክርስቶስ ንጽጽር ጊዜ እንደታየው ሙሴ ያገባ አንዲት ሴት ብቻ፣ያውም በሕግ፣መሐመድ ግን ገንዘብ ካየባት ማንንም ሴት የሚነትት፣የሰውሩን እናውቅም እኛ፣በይፋ ግን 13 ያገባ ነበር። ሙሴና መሐመድ ቢመሳሰሉ ኑሮ፣እነቱና ወንድሙ ምሽትህን ፈትተህ ሌላ አግባ ብለው ሲጣሉት በተስማማ ነበር፤መስፍን ነውና፣መሐመድና ተከታዮቹ እንደሚያደርጉት ብዙ ሴቶችም ማግባት ይችል ነበር። ነገር ግን የመሐመድ ተመሳሳይ ስላልሆነ አላደረገውም።

8. ሙሴ እስራኤልን ወደ ምድረ ርስት በእግዚአብሔር ትእዛዝ እየመራ ሲያስገባ በመንገድ አላሳለፈው ያሉትን ወጋ እንጂ እንደ መሐመድ በሃይማኖት ስም ዓለምን እየዞረ አልወረረም። መሣሪያ የሌላቸውን ሕፃናትና ሴቶች አልጨፈጨፈም። በዚህ ጓደኞቹ ጨካኞች አረመኔዎች የጦር መሪዎች(ጀኔራሎች)ሀኒባል፣አውግስጦስ ቄሳር፣

እስክንድር፣ናቡከደነጾር፣ኔሮንወዘተ ናቸው እንጂ ነቢያትስ አይደሉም
9. ሙሴ የእስራኤል መሪ እንጂ ሠራዊቱን የተነሣ ጀኔራል አልነበረም፣አይደለም።
10. ሙሴ እስራኤልን ከግብጽ ባርነት አውጥቶ እግዚአብሔር በተስፋ ወደ ሰጣቸው ሀገር ወደ ከንዓን መርቷል፤በዚህ ተቃራኒ መሐመድ ግን በዙሪያ ያሉትን እስራኤልን (አይሁድን) ከክርስቲያን ጋራ (የመጽፍ ሰዎች) አጥፍቷል፣በጦር ኀይል አጥፍታል፣ ባሪያ አድርጓል።
11. ሙሴ ከፈጣሪው ጋራ ተነጋግሮ ሲመለስ በገጹ ብርሃን ተሞሉበት ነበር፤ (ዘፀ.34:29-35) እንዲሁም ሆነ ሙሴ ከተራራ በወረደ ጊዜ ሁለቱ የምስክር ጽላቶች በሙሴ እጅ ነበሩ። ሙሴም ከተራራው በወረደ ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋራ ስለተነጋገረ ፊቱ እንዳንጸባረቀ አላወቀም ነበር። አሮንና የእስራኤል ልጆችም ሁሉ ሙሴን ባዩ ጊዜ፣እነሆ ፊቱ እንደ-ባረቀ፣ወደ እሱም ይቀርቡ ዘንድ ፈሩ። ሙሴም ጠራቸው፣አሮንም የማኅበሩ አለቆችም ሁሉ ወደ እርሱ ተመለሱ ሙሴም ተናገራቸው። ከዚያም በኋላ የእስራኤል ልጆች ሁሉ ቀረቡ እግዚአብሔርም በሲና ተራራ የተናገረውን ሁሉ አዘዛቸው። ሙሴም ለእነርሱ ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ በፊቱ መሸፈኛ አደረገ። ወንጌሉን (ማቴ.17:1-8፤ማር. 9:2 ፣ሉቃ.9:28-34)ዕይ። በዚህ ተነጻጻሪ መሐመድ ግን ራእይ አየሁ ብሉ፣ብርድ እንደያዘው ሰው ሲንቀጠቀጥ ከርሟል። (መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሐመድ፣ገጽ 14 አንቀጽ ሁለትን ዕይ።) በዚህም የሚሰበው ጋኔን ያጠናፈረው፣ዛር ያስጎራው፣ ባሪያ የጣለው ርኩስ መንፈስ ያሳበደው በሽተኛ ሰው መሆኑ ነው።
12.ሙሴ ከእስራኤል ሕዝብ የተለየ ሀብትና ድሌብ አልነበረውም፣ መሐመድ ግን ጀኔራል ስለ ነበረ ለሀብቱ፣ለገንዘቡ፣ለድሌቡ፣ለጥሪቱ፣ ለወርቁ ቁጥር ወይም መስፈርት አልነበረውም።
13. መሐመድ የሴትንና የወንድን መብት ሲሠራ ለጦርነት የሚከተሉት ወንዶች እንዲቀበሉት አድርጎ ነው፤ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም።
14. <u>በጋብቻ፣</u> በአውስቦ ሙሴና ክርስቶስ ይመሳሰላሉ በሚለው ርእስ እንዳየነው አውስቦ በሙሴም ሆነ በክርስቶስ ክቡር ነው፣በመሐመድ ግን ወንድን እንደ እንስሳ በእንስቷ ላይ የሚያሠለጥን ሕግ የለሽ ልቅ ነው። ወድ ምሽቱን እንደ አካሉ ስለ፣ማያያት የቤተ ሰብ ኀላፊነት የለውም፣አይሰማውም፤ሴቷም የእኩልነት መብት ስለ ሌላት ጋብቻ በመሐመድ ሕግ ሥሪያ ነው። ስለዚህ እንደ ሙሴ የጋብቻ ሥራ ሠራ ማለት አይቻልም። ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችም የሚያመንዝሩ እነሱን ስላሞችንና አረማውያንን ተከትለው ነው።

15. በሞትና በመቃብር፣ሙሴ የተቀበረበትን እስከዛሬ የሚያውቅ የለም፣መሐድ ግን እንደ ተራ ሰው ታሞ ተፈራግጦ፣አጣጥሮ ነው የሞተ።
(ዘዐ.34:1-6) ሙሴም ለሞዓብ በኢያሪኮ ፊት ለፊት ወደ አለው ወደ ናባው ተራራ ወደ ፈስጋ ራስ ሚዳ ወጣ፤እግዚአብሔርም እስከ ዳን ድረስ ያለውን የገለዓድን፣ምድር የንፍታሌንም ምድር ሁሉ፣የኤፍሬ ምንና የምናሴንም ምድር እስከ ምዕራብም ባሕር ድረስ ያለውን የይሁዳን ምድር ሁሉ፣ደቡቡንም፣ እስከ ዞዓር ድረስ ያለውንም፣ የዘንባባ ዛፎች ያሉበትን ከተማ የኢያሪኮን ሸለቆ ሜዳ አሳየው። እግዚአብሔርም ለዘርህ እሰጥሃለሁ ብዬ ለአብርሃም ለይስሥሐቅ ለያዕቆብም (ከዚህ ላይ እስማኤል የለም) የማልሁላቸው ምድር ይህች ናት። በዐይንህ እንድታያት አደረግሁህ፣ነገር ግን ወደዚያች አትሻገ ርም አለው። የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴም እንደ እግዚአብሔር ቃል በዚያ በሞዓብ ምድር ሞተ። በቤተ ፌጎርም ፊት ለፊት፣በሞዓብ ምድር በሸለቆው ውስጥ ተቀበረ። እስከ ዛሬም ድረስ መቃብሩን ማንም አላወቀም።
16. መሐመድ እንደሞተ ቀረ፤ተነሥቷል የሚል ተረት ቢኖርም የባልቴት ተረት እንጂ በቁርአን ውስጥ ስለሌላ ከመጽሐፈ ባልቴትነት ከልጆች ተረት አያልፍም፣ ሙሴ ግን በደብረ ታቦር ከኤልያስ ጋራ መጥቶ የጌታን ብርሃነ መለኮት አክብራል። ከኤልያስም ጋራ ሰለ መጣ እንደ ኤልያስ ሕያው ነው ለማለት ያስቻሉ። (ማቴ.17:1-8) በስድስት ቀን በኋላ፣ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው። በፊታቸውም ተለወጠ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፣ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ። እነሆም ሙሴና ኤልያስ ከርሱ ጋራ ሲነጋገሩ ታዩአቸው። ጴጥሮስም መልሶ" ኢየሱስን፣ጌታ ሆይ! በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው ብትፈቅድስ፣ በዚህ ሦስት ዳስ፣አንዱን ላንተ፣አንዱን ለሙሴ፣አንዱንም ለኤልያስ እንሥራ" አለ። እሱም እየተናገረ ሳለ፣እነሆ! ብሩህ ደመና ጋረዳቸው፣ እነሆም ከደመናው "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጂ ይህ ነው፣ እርሱን ስሙት" የሚል ድምፅ መጣ። ደቀ መዛምርቱም ሰምተው በፊታቸው ወደቁ፡ እጅግም ፈርተው ነበር። ኢየሱስም ቀርቦ ዳሰሳቸ ውና" ተነሡ አትፍሩም አላቸው። ዐይናቸውንም አቅንተው ቢያዩ ከኢየሱስ በቀር ማንንም አላዩም። (ማር.9:2-8 ፤ሉቃ.9:28-36)
ይህ ሁሉ ልዩነት እያለ ሙሴንና መሐመድን ማመሳሰል ዐይን አውጣ ድርቅናና ውሼት ነው።
ከዚህም በላይ ሰለ ክርስቶስ የተናገረ መሲሕ ሙሴ ብቻ ስላልሆነ ትንቢቶቹ በቅደም ተከተል እንዴት እንደተፈጸሙ ለማወቅ ምዕራፍ 7ን ያንቧል።

## ምዕራፍ 12፤

## ክርስቶስ ከእሱ በኋላ ለሚመጡ ሐሰውተ ነቢያት፤

ይህ ርእስ ክርስቶስ ከእሱ በኋላ ነቢይ ነኝ እያሉ ለሚመጡ ውሸታም ሰዎች ቢባል ይቀና ነበር። ግን ሐሰውተ ነቢያት፣ (ነቢያትን የሚያስተባብሉ)ሐሳውያን ነቢያት፣ሐሳዊ፣ሐሳዊ መሲሕንና የመሳሰሉት ቃላትም የተለመዱ ስለሆነ ከተለመደና እኛም ስሜቱን ከሸጋገረ ብለን፣ውሸታም ነቢያት እያልን ጽፈናል።

እያ አሕመድ ዲዳት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ክርስቶስ የተነገረውን ትንቢት ሁሉ አጣሞ ተርጉሞ ለመሐመድ ሰጥቶ ይህም ይህም ለመሐመድ ነው የተነገረ ይላል። ይህ ግን እውነት እንዳልሆነ በአለፉት ምዕራፎች አስረድተናል። ትንቢት ሁሉ ዳንኤል እንደተናገ ረው በሱባኤው ክርስቶስ በመጣበት ዘመን አልፏል።

(ዳን.9፡25)ይህን ልብ ብለህ አስተውል፣ኢየሩሳሌም እንድትታደስ ትእዛዝ ከወጣበት ጊዜ አንሥቶ መሲሕ እስከሚመጣበት ድረስ ሰባት ጊዜ ሰባት ዓመታት ያልፋሉ፤ኢየሩሳሌም ትታደሳለች፤መንገዶችና ምሽጎች ይሠሩላታል። ሰባት ጊዜ ስልሳ ሁለት ዓመታትም ጸንታ ትቆያለች፤ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ የመከራ ዘመን ይሆናል። ያም ጊዜ ሲፈጸም መሲሕ ይገደላል፤ከተማዋና ቤተ መቅደሱ አንድ ታላቅ መሪ በሚያዘምተው ሠራዊት ይደመሰሳሉ። መጨረሻም ጊዜ እንደጎርፍ በድንገት ይመጣል፣እግዚአብሔር ያዘጋጀውም ጥፋት ይከተላል። ያም መሪ ከብዙ ሕዝቦች ጋር እስከ ሰባት ዓመት ድረስ በጠበቀ ሁኔታ ቃል ኪዳን ይገባል። የሰባቱ ዓመት እኩሌታ ሲያልፍ መሥዋዕትና ቁርባን ማቅረብን ይከለክላል፤በቤተ መቅደሱም ማዕከላዊ ስፍራ ላይ አጸያፊ የሆነ የጥፋት ርኩሰት እንዲፈጸምበት ይደረጋል፤ይህም የሚሆነው እግዚአብሔር በወሰነው መሠረት እስከሚወገድበት ጊዜ ነው።

ይህ ትንቢት ቃል ለቃል ተፈጽሟል፤ኢየሩሳሌም ታድሳለች፣በተባለው ዘመን መሲሕ ኢየሱስ (ክርስቶስ)ተገሏል፣እሱ በሞተ በሰባኛው ዓመት ደግሞ በሮም ጀነራል በቲቶ (ጥጦስ) መሪነት የታደሰችው ኢየሩሳሌም ተመዝብራለች፣ፈርሳለች፣ተወራለች፤ንዋያት ቅድሳትም ሮም ወርደዋ ል መሥዋዕትም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቀሟል። ከዚያ በኋላ ሐሳዊ መሲሕ (ወይም ውሸታም ነቢይ) እንጂ ደግ ነቢይ እንደማይመጣ ነቢያትም ሐዋርያትም በግልጥ ተናግረዋልና አልመጣም አይመጣምም።

የሐሳውያን ነቢያትን መምጣት ክርስቶስና ሐዋርያት በግልጥ ተናግረዋል። ይልቁንም የሁለቱን፣አንዱ ከዚህ በፊት መጥቶ ሥላሴን አስክዶ፣ክርስቶስን አስተባብሎ ብዙ ሕዝብ አጥፍቶ አልፏል፣

ሁለተኛው ደግሞ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ዋዜማ ይመጣል እይተባለ ይጠበቃል።

እንዲህ ከሆነ ለምን ክርስቶስና ሐዋርያት ከእሱ በኋላ የሚመጡትን መስሕታን ሐሰዉተ መሲሕ በግልጥ ስም ጠርተው፣አንገት ቆጠርው አልተናገሩም? ለሚል ጠያቂ መልሱ ቀላል ነው፤እንኳንስ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስና ሐዋርያት ይቅርና ከሱ በፊት የተነሡ ነቢያት ሰም እየጠሩ ተናግረዋል። ሃማኖት የሚያጠና፣ሕዝብ የሚረዳ ደግ ሰው የሆነ እንደሆነ በዚያ ስም ለመጠራት ብዙ ይጓጓል፤በዚህ ተቃራኒ ሃይማኖት ያስከዳል እንደነጅስካንና ሌሎች አረማውያን የሆነ እንደሆነ ግን በክፉ ስም የሚጠራ የለም።
ለምሳሌ ኢሳይያስ የቂሮስን መምጣት የኢየሩሳሌምን መታደስ ከሦስት መቶ ዘመን በፊት ስሙን ጠርቶ ተናግሯል፤ ኤርምያስም የናቡከደነጸርን መምጣት መላልሶ ተንብዮአል።
(ኢሳ.44:28)ቂሮስን ሕዝቤን የምታስተዳድርልኝ ዕቅዴን ሁሉ የምተፈ ጽም፣ኢየሩሳሌም እንድትሠራና የቤተ መቅደስም መሠረት እንዲጣል የምታደርግልኝ አንተ ነህ እለዋለሁ።
እንኳንስ እነሱና በሀገራችንም አንዳንድ ባሕታውያን የተናገሩትን ይዘው መሳፍንቱ ስማቸውን ይለውጣሉ፣ለምሳሌ ዐፄ ቴዎድሮስ ከካሣ ቴዎድሮስ፣ዐፄ ዮሐንስ ከካሣ ወደ ዮሐንስ፣ኀይለ ሥላሴ ከተፈሪ ወደ ኀሥ፣ደጃች ሥዩም ወደ ራስ ኀይሉ፣ኀይለ ኢየሱስ በዚህ ዐይነት ስማቸውን የሚለወጡ ብዙዎች ስለሆኑ ነው እንጂ ስሙን መጥራት ችግር አይደለም።
ስለዚህ እኛም ስም መጥራቱን ትተን ከክርስቶስ በኋላ ስለ ሚመጡት ውሸታም ነቢያት የተጻፈውን በደፈናው እንጽፋለን፤አንብቦ እነማን እንደሆኑ መረዳቱን፣መገመቱን ለአስተዋይ አንባቢ ትተን። (ማቴ.24) ኢየሱስ ከመቅደስ ወጥቶ ሲሄድ ደቀ መዛሙርቱ የቤተ መቅደሱን ሕንፃ ሊያሳዩት ወደ እሱ ቀረቡ። እርሱ ግን "ይህን ሁሉ ሕንፃ ታያላችሁን? በእውነት እላችኋለሁ ደንጊያ በደንጊያ ላይ ተነባብሮ ሳይፈርስ የሚቀር የለም" አላቸው። (ከዚህ ቀጥሎ በጠቅላላ ስለ ዓለም (ዘመን) ተንትና ነግሯቸዋል)። ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተራራ ተቀምጦ ሳለ ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን ወደ እርሱ ቀርበው፣" ይህ ሁሉ ነገር የሚሆነው መቼ ነው? የመምጫህና የዓለም መጨረሻስ ምልክቱ ምንድ ን ነው?" ሲሉ ጠየቁት። ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፣ማንም ሰው እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፣ምክንያቱም ብዙዎች እኔ መሲሕ ነኝ፣እያሉ በስሚ ይመጣሉ፣ብዙዎችንም ያስታሉ፤የጦርነት ድምፅና የጦርነት ወሬ ትሰማላችሁ፤ይህ ሁሉ መሆን ስላለበት አትደንግጡ፣—— በዚያን ጊዜ ሰዎች ለመከራ አሳልፈው ይሰጧችኋል፣ ይገድሏችኋል። በስሜም ምክንያት በሕዝቦች ሁሉ ዘንድ የተጣላችሁ ትሆናላችሁ፤በዚ

በዚያን ጊዜ ብዙዎች ሃይማኖታቸውን በመካድ ይሰናከላሉ፣እንዱ ሌላውን አሳልፎ ይሰጣል፣ሰዎችም እርስ በርሳቸው ይጣላሉ፣ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉ፤ብዙዎችንም ያስታሉ——፤"በዚያን ጊዜ እነሆ! መሲሕ ከዚህ አለ" ቢሏችሁ አትመኑ፤ምክንያቱም ሐሰተኞች መሲሖችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉ፤እነሱ ቢቻላቸውስ የእግዚአብሔርን ምርጦች እንኳ ለማሳሳት ታላላቅ ተአምራትና ድንቅ ነገሮችን ያሳያሉ:: እንግዲህ ይህን ሁሉ አስቀድሜ ነግሬአችኋለሁ፤ስለዚህ እነሆ! በበረሃ አለ ቢሏችሁ አትሂዱ፣እነሆ! በሰውር ቦታ አለ ቢሏችሁም አትመኑ::——፤የዚህን ጥቅስ ተመሳሳይ(ማር.13:3-13፤ሉቃ.21:7-19) ያነቧል::

<u>ስለ ሐሳውያን ነቢያት የክርስቶስ ተከታዮች ሐዋርያትስ ምን ብለዋል?</u>

(1ዮሐ.2:18)ልጆቼ ሆይ! ይህ የመጨረሻው ሰዓት ነው፣ "የክርስቶስ ተቃዋሚ ይመጣል" ሲባል ሰምታችኋል፣እነሆ! አሁን እንኳ ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ተነሥተዋል:: በዚህም ምክንያት የመጨረሻው መሆኑን እናውቃለን::——፤

(4:1-3) ልጆቼ ሆይ! በዓለም ላይ ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ስለተነሡ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ይልቅስ መንፈሶች ከእግዚአብሔር መሆናቸ ውንና አለመሆናቸውን መርምሩ፤የእግዚአብሔርን መንፈስ ለይታች ሁ የምታውቁት እነሆ!በዚህ ነው፣ኢየሱስ ሰው ሆኖ በሥጋ መገለጡን የማያምን መንፈስ ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ አይደለም፤ይህም መንፈስ ይመጣል ሲባል የሰማችሁት የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ነው::——:(1ጢሞ.1-2) መንፈስ ግን በግልጥ እንዲህ ይላል፤በኋላኛው ዘመን አንዳንድ ሰዎች አሳሳች መናፍስትንና የአጋንንትን ትምህርት በመከተል ሃይማኖተን ይክዳሉ::——፤

(2ጢሞ.3) በመጨረሻ ቀኖች የሚያስጨንቅ ጊዜ እንደሚመጣ ዕወቅ፣ ሰዎች ራሳቸውን የሚወድዱ፣ለገንዘብ የሚስገበገቡ፣ትምክሕተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ተሳዳቢዎች፣ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ውለታ ቢሶች፣ ሃይማኖተ ቢሶች፣ፍቅር የሌላቸው፣ከሰዎች ጋራ በምንም የማይስማሙ የሰው ስም የሚያጠፉ፣ራሳቸውን የማይቆጣጠሩ፣ጨካኞች፣መልካም የሆነውን ነገር የሚጠሉ፣ከዳተኞች ጥንቃቄ የሌላቸው፣በትዕቢት የተነፉ እግዚአብሔርን ከመውደድ ይልቅ ሥጋዊ ደስታን የሚወዱ ይሆናሉ፤እንዲሁም ሃይማኖት ያላቸው ይመስላሉ፤ነገር ግን የሃይማኖ ትን ኀይል ይክዳሉ:: ከእነዚህ ሰዎች ራቅ::——::

## ምዕራፍ 13፣

## ከክርስቶስ በኋላ ነቢይ የለም፣

የብሉይና የሐዲስ ጉልላት(ፒራሚድ)ክርስቶስ ነው። ነቢያት የክርስቶስን መምጣት ከሺ ዘመን በፊት አስቀድመው በትንቢት እየተናገሩ መንገዱን ጠርገዋል። ሐዋርያት ደግሞ የተነገረውን ትንቢት ሁሉ ጨርሶ፣ዓለምን አድኖ በአባቱ ቀኝ በክብር ተቀምጧል እያሉ ዓለምን ዙረው አስተምረዋል፣ሰብከዋል።ትንቢት የተነገረለት፣ሱባኤ የተቆጠረለት፣ሰው የሆነ አምላክ፣ሊቀ ካህናት፣ንጉሠ ነገሥት፣ሊቀ ሰማዕት፣ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ መሆኑን በተጨባጭ ለማስረዳት ይህ ምዕራፍ ተዘጋጅቷል።

ከሁሉም ሁሉን ይወቀ ምዕራፍ 20 ከክርስቶስ በኋላ ነቢይ የለም በሚል ርእስ በአጭሩ በደፈናው፣ስም ሳንጠቅስ ጽፈን ነበር፤አሁን ግን ሰላሞች ራሳቸው ደምበር ጥሰው፣አትራ ዘለው ክርስቶስ አምላክ አይደለም፤አምላክም ልክ እንደ ሰባልዮስ አንድ ገጽ እንጂ ሦስት ገጽ አይደለም፤እያሉ የመሣለቂያ ክታባት ስለበተኑ፣አንበው-ት ባልገባቸው በራሳቸው ቁርአንና በቅዱሳት መጻሕፍት ለመርታት ይህ ጥናት በስፊው ቀረበ። ከስልምና በቀር ለሌላው የሃይማኖት ጥያቄ ግን ሁለቱን መጻሕፍቱን ማማከር ያሻል።

አልቦ ነቢይ ድኅረ ክርስቶስ፣ የትንቢት ሁሉ መፈጸሚያ ክርስቶስ ነው።

<u>የነቢይ መግለጫ፣</u> የነቢያት ትርጉም የመጣው ነበየ፣ ተነበየ ካለው ግሥ ነው፣ይኸውም በዕብራይስጥ አንድ ሰው ስለ ሦስተኛ ሰው ተናገረ ማለት ነበር፣እንደ ጠበቃ፣ስለዚህ እስራኤል ባጠፉ ቁጥር ነቢያት እየተነሡ በእግዚአብሔር ስም ይገሥጹ ጀመር። ሕዝቡም አልሰማ ሲል ጊዜ እግዚአብሔር ይቀጣል ሆነ፣በኋላ ጥቂት በጥቂት አስተዋይ ሰዎች ሲገሥጹ፣እግዚአብሔርም ሲቀጣ፤ ትንቢት፣ አስቀድሞ መናገርን ያሳይ ጀመረ። (በዚህ ትርጉም መሐመድ ነቢይ አይደለም፣አንዳንዴ ከመጽሐፈ ባልቲትና ተረት በቀር በቁርአን ተናግሮት የተፈጸመ ነገር የለምና፡) በኋላ እየመረጠ ለሕዝቡ እንዲህ በል እያለ እግዚአብሔር ሲያዝዝ፣ነቢይም ሲላክ፣ ትንቢትም ይደርስ ይፈጽማል ሆነ፣ስለዚህ አስቀድሞ የተናገረ ሁሉ ነቢይ ይባል ጀመር። በዚህ ትርጉም ከነቢያተ እስራኤል ብዙዎች ስለ ክርስቶስ መምጣት ተናግረዋል፤ጌታም ሐዋርያትም ስለ ሐሳዊ መሲሕ በሰፊው ተናግረዋል፤እሱም የክርስትና ጠላት ከነተከታዮቹ መሆኑ ነው። ነቢያትም እንደ ሁኔታቸው ልዩ ልዩ ስም አሏቸው።

ከዚህ የምናየው ግን ትልቁን ሊቀ ነቢያት በትስብእቱ ወልደ ማርያም፣በመለኮቱ ወልደ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። ብዙ ፖለቲከኞች ከሃይማኖት ተጠግተው ሰውን ለማታለል፣ነቢይ ነን

ከእግዚአብሔር ተልከናል እያሉ መደዷውን ያታልላሉ፣አታለዋል። ከክርስቶስ በቀር ሌሎች ሁሉ የተቆጠረውን ሱባኤ የተነገረው ትንቢት አልሞሉም፣አላሟሉም:ምክንያቱም ለክርሰቶስ የተነገሩትን አላሟሉማ! አያሟሉም። ያ ትንቢት የተነገረለት ነቢይ፣የእግዚአብሔር መልእክተ ኛ፣ነቢይ፣ ሊቀ ካህናት፣ሊቀ ስማዕት፣የመከራ ሰው፣ ንጉሠ ነገሥት ወልደ እግዚአብሔር፣ወልደ፣ ዳዊት፣ ወልደ አብርሃም፣ በመለኮቱ ከአባቱ ከእግዚአብሔር አብ ጋራ እኩል፣ጥንት የሌለ ዘለዓለም ሕያው፣በሥጋው (በትስብእቱ) ከኀጢአት በቀር ልክ እንደኛ የሚበላ፣ የሚጠጣ፣የሚደክም፣የሚቀባ፣ የሚከበር፣ የከበረ፣ የተቀባ፣ ከመለኮት ተዋሕዶ በድንግልና የተወለደ ነው። ከክርስቶስ በኋላም በፊትም የመጡት ሰርባቶች (ፖለተከኞች) ግን ምንም አምላክ ልኮናል ቢሉም ሁሉም የተወለዱት በዘርዐ ብእሲ ሲሆን ዘርዓቸው ደግሞ ትንቢት ከተነገረለት ከአብርሃምና ከያዕቆብ ዘር ውጭ ነው። የኢየሱስን (ዒሳን) ክርስቶስነት (መሲሕነት) ነቢይነት የሚቀበል፣ነቢያትን፣መዝሙርን ወንጌልን፣የሚያምን ሁሉ፣እውነተኛ ከሆነ በሌላ ባህል ሰላደገ ቶሎ ባይዋገውም ይህን ሐቅ አስተውሎ መቀበል አለበት። ከሁሉ አስቀድሞ ሙሴ ሊቀ ነቢያት በኦሪት ዘዳግም(18:18-20) እስራኤልን ሲሰናበት እንዲህ ብሏል፤

አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወገኖችህ እንደኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፣እርሱንም ስማው፣እግዚአብሔር አለኝ፣ የተናገሩት መል ካም ነው፣ከወንድሞቻቸው መካከል እንዳንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለ ሁ፣ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፣ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል በስሜም የሚናገረውን ቃል የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ። ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን በስሜ በድፍረት የሚናገር ወይንም በሌላ አማልእክት ስም የሚናገር ነቢይ እሱ ይገደላል። ይህን ጥቅስ አስተውለን ብናየው ክርስቶስ ወይም ትልቁ ነቢይ ከአብርሃም ሕጋዊ ልጅ ከያዕቆብ ዘር እንጂ ከአብርሃም ምሽት ባሪያ ልጆች፣ዲቃ ሎች ከአጋር ልጅ ኢስማኤል ደግሞም ከቆጥሩ ልጆች እንደማይወለ ድ ቁልጭ አድርጎ ይናገራል። እንደምን ቢሉ እንደኛ ከወንድሞቻቸ ው መካከል ሲል የሚያሳየው የያዕቆብን ልጆች ብቻ ነው። እስራኤል ከያዕቆብ ልጆች ከዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል በቀር የቀረውን ወንድማችን አይሉምና። ከዚህም ሌላ ዐረብና እስራኤል የዘለዓለም ጠላት እንጂ ወንድማማች አይደሉምና። የሚገዳደሉ ጠላት ደመኛ እንጂ ቢዛመድም ወንድማች አይባሉምና። ስለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እናቀርባለን።

አብርሃም ይሥሐቅን ባረከ፤ሕፃኑም አደገ፣ጡትም ጣለ። አብርሃምም ይሥሐቅን ጡት ባስጣለበት ቀን ግብዣ አደረገ። ሣራም ግብጻዊቱ

አጋር ለአብርሃም የወለደችለትን ልጅ ሲሥቅ አየችው:: አብርሃምንም ይህችን ባሪያ ከነልጇ አሳድ፤የዚች ባሪያ ልጅ ከልጄ ከይሥሐቅ ጋራ አይወርስምና አለችው:: ይህም ነገር አብርሃምን ስለ ልጁ በጣም አስቸገረው:: እግዚአብሔርም አብርሃምን ስለ ባርይህና ስለብላቴናው አትዘን፤ሣራ የምትነግርህን ቃል ሁሉ ስማ፣ በይሥሐቅ ዘርህ ይጠራልና አለው::

ስለዚህ በበነጋው ማልዶ ተነሥቶ ባሪያውን አጋርን ከልጆዋ ከእስማኤል ጋራ አባረረ:: ሁለተኛውም አልተገናኙም:: ለመሥዋዕትም የቀረበው ይሥሐቅ እንጂ ስላሞች እንደሚሉት እስማኤል አይደለም:: እስላሞች ራሳቸውን ለማጋነን ብለው የፈጠሩት ስለሆነ ከቅዱሳት መጻሕፍት አይገኝም:: በእስራኤልና በዐረቦች መካከልም የደም እንጂ የሃይማኖትና የፍቅር ወንድማማችነት የለም::

ለሁሉም ጥቅሱን እንጨርስ፤

የባሪያይቱን ልጅ ደግሞ ሕዝብ አደርገዋለሁ ዘርህ ነውና፤አብርሃም ም ማልዶ ተነሣ፤እንጀራም ወስዶ አቁማዳ ውሃም ለአጋር በትከሻዋ አሸከማት፤ብላቴናውንም ሰጥቶ አስወጣት:: እርሷም ሄደች በቤርሳቤ ህም ምድረ በዳ ተቅበዘበዘች:: ውሃውም ከአቁማዳው አለቀ፤ብላቴናው ንም ከአንድ ቁጥቋጦ በታች ጣለችው፤እስዋም ሄደች ብላቴናው ሲሞት አልየው ብላ፤ቀስት ተወርውሮ የሚደረስበትን ያህል ርቃ፤በአ ንጻሩ ተቀመጠች፤ፊት ለፊትም ተቀመጠች፣ ቃሏንም አሰምታ አለቀሰች:: እግዚአብሔርም የብላቴናውን ድምጽ ሰማ:: የእግዚአብሔ ርም መልአክ ከሰማይ አጋርን እንዲህ ሲል ጠራት አጋር ሆይ! ምን ሆንሽ? እግዚአብሔር የብላቴናውን ድምጽ ባለበት ሰምቷልና አትፍሪ ተነሽ፣ብላቴናውንም አንሽ፣እጅሽንም በእሱ አንጥኚው፣ትልቅ ሕዝብ አደርገዋለሁና፤እግዚአብሔርም ዐይኗን ከፈተላት፤የውሃ ጉድጓድም ዐየች፤ሂዳም አቁማዳዋን በውሃ ሞላች ብላቴናውንም አጠጣች:: እግዚአብሔርም ከብላቴናው ጋራ ነበር:: አደገም በምድረ በዳም ተቀመጠ፤እናቱም ከምድረ ግብጽ ሚስት ወሰደችለት:: (ዘፍ.21:8-21) በዘመኑ በቅዱስ መጽሐፍ የተጻፈው ይህ ነው:: ከዚህ በፊትም በይሥሐቅ እንጂ በእስማኤል በኩል እንደ ማይመጣ ጌታ እግዚአብሔ ር ፍርጥ፣እርግጥ አድርጎ ተናግሯል:: (ዘፍ.17:15-25) እግዚአብሔ ርም አብርሃምን አለው፤የምሽትህን የሦራን ስም ሦራ ብለህ አትጥራ ስሟዋ ሣራ ይሆናል እንጂ፤እባርካታለሁ፤ደግሞም ከእስዋ ልጅ እሰጥ ሃለሁ:: እባርካታለሁ፤ደግሞም ከእስዋ ልጅ እሰጥሃለሁ:: እባርካትም አለሁ:: የአሕዛብም እናት ትሆናለች፤የአሕዛብ ነገሥታት ከርስዋ ይወጣሉ:: አብርሃምም በግንባሩ ወደቀ ሣቀም፤በልቡም አለ፤የመቶ ዓመት ሰው በውኑ ልጅ ይወልዳልን? ዘጠና ዓመት የሆናትም ሣራ

ትወልዳለችን አብርሃምም እግዚአብሔርን እስማኤል በፊትህ ቢኖር በወደድሁ ነበር አለው። እግዚአብሔርም አለ በእውነት ምሽትህ ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች ስሙንም ይሥሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ፤ ከርሱ በኋላ ለዘሩ የዘለዓለም ቃል ኪዳን እንዲሆን ቃል ኪዳኔን ከርሱ ጋር አቆማለሁ ስለ እስማኤልም ሰምቼሃለሁ፣እነሆ ባርኬዋለሁ፣ፍሬአ ማም አደርገዋለሁ፣እጅግም አበዛዋለሁ፤ ዐሥራ ሁለት አለቆችም ይወልዳል፣ታላቅ ሕዝብም እንዲሆን አደርገዋለሁ። ቃል ኪዳኔን ግን በሚመጣው ዓመት በዚሁ ጊዜ ሣራ ከምትወልድልህ ከይሥሐቅ ጋራ አቆማለሁ። እስማኤልን አብርሃም ከቤቱ ካስወጣ በኋላ እስማኤል ወደ አባቱ ቤት አልተመለሰም። ከዚህ በኋላ ሁለቱ ወንድማማቾችም አልታረቁም። ከአብርሃምም ሞት በኋላ እግዚአብሄር ይሥሐቅን ባረከው መረቀውም። (ዘፍ.25:11)

የአብርሃሙ ይሥሐቅን በመባረክ፣እስማኤልን በማባረር ተደመደ መ። ይሥሐቅ ም ያዕቆብን ባረከ፤ይሥሐቅም ስለ ምሽቱ ወደ እግዚአ ብሔር ጸለየ፣መካን ነበረችና፤እግዚአብሔርም ተለመነው። ርብቃም ምሽቱ ፀነሰች፤ልጆቹም በሆዷ ውስጥ ይተጋሉ ነበር። እሷም እንዲህ ከሆነ ይህ ለኔ ምኔ ነው አለች። እግዚአብሔርንም ትጠይቅ ዘንድ ሄደች፣ እግዚአብሔርም አላት፣"ሁለቱ ወገኖች በማሕፀንሽ ናቸው። ሁለቱም ሕዝብ ከሆድሽ ይከፈላሉ፤ሕዝብም ይበረታል ታላቁም ለታናሹ ይገዛል። "ትወልድ ዘንድ ዘመንዋ በደረሰ ጊዜ፣እነሆ በማሕፀ ንዋ መንታ ነበሩ። በፊትም የወጣው ቀይ ነበረ፣ሁለንተናውም ጠጉር ለብሶ ነበር ስሙም ኤሳው ተባለ። ከዚያም በኋላ ወንድሙ መጣ። በእጁም የኤሳውን ተረከዝ ይዞ ነበር፣ስሙም ያዕቆብ ተባለ።(25:21-26)እነዚህም እንደ ይሥሐቅና እስማኤል ለጊዜው ወንድማማቹ፣ለፍጻ ሜው ግን ልጆቻቸው ተለያይተው፣ተቆራርጠው ቀርተዋል። ኤሳውስ እንዲያውም ከአሕዛብ ወገን ሁለት ሴቶች አግብቶ ይሥሐቅንና ርብቃን ሲያሳዝናቸው ኖረ እንጂ አልተመረቀም። (ዘፍ.26:3435)ይሥ ሐቅም ያዕቆብን ዘርህ ይባረክ፣የእናትህ ልጆች ይስገዱልህ፣የምድር አሕዛብ ይገዙልህ ብሎ መረቀው፣(ዘፍ.27:1-30) ያዕቆብም ይሁዳን ባረከ። ያዕቆብም ዕለተ ሞቱ ደርሶ ዐሥራ ሁለቱን ልጆቹን ሲመርቅ ከእርሱ ዘር ክርስቶስ የሚወለድበትን ይሁዳን እንዲህ ብሎ መረቀው፣ሁሉም በክርስቶስ ደረሰ፣ተፈጸመ። "ይሁዳ ወንድሞችህ አንተን ያመሰግኑሃል፣እጅህ በጠላቶችህ ደንደስ ላይ ነው፤የአባትህ ልጆች በፊትህ ይሰግዳሉ። ይሁዳ የአንበሳ ደቦል ነው፣ልጄ ሆይ! ከደንህ ወጣህ፣እንደ አንበሳ አሸመቀህ፣እንደ ሴት አንበሳ አደባህ፣ያስ ነሣው ዘንድ ማን ይችላል? በትረ መንግሥት/ይሁዳ አይጠፋም፣

የገኘሮም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል፣ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ የአሕዛብ መታዘዝም ከእሱ ይሆናል። ውርንጭላውን በወይን ግንድ ያስራል፣የአህያይቱንም ግልገል በወይን ሐረግ፣ልብሱን በወይን ያጥባል፣መጎናጸፊያውንም በወይን ደም፣ዐይኑም ከወይን ይቀላል፣ ጥርሱም ከወተት ነጭ ይሆናል። (ዘፍ.49: 8-12)

ይህን ትንቢት ቃል በቃል ከክርስቶስ በቀር ከያዕቆብ አንድ ከእስማኤልም ሆነ ከወንድሙ ከኤሳው ልጆች የፈጸመ የለም። እስራኤልም ወንድምህን እንደራስህ ውደድ፣ጠላትህን ጥላ ሲሉ ወንድም ከያዕቆብ ልጆች ከዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል የሚወለደውን እስራኤላዊን፣ጠላት ደግሞ ከዚያ ውጭ ያለውን ስለሆነ፣ለእስማኤልና ለኤሳው ርግማንና ጠላትነት ማስረጃ አስከዚህ የተጠቀሰ ነው ያብቃንና ወደ ሌሎች ቃላት እንመለስ። እግዚአብሔርም አለኝ ከወንድሞቻቸው መካከል እንዳንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፣ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ። ይህ ቃል ቃለ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አካላዊ ቃል ሥጋ ለብሶ ትስብእትን ይዋሐዳልና።

ያዘዝሁትን ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፣በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀለዋለሁ። ይህንም ኋላ በፈለገ ዮርዳኖስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲጠመቅ፣በደብረ ታቦር መለኮቱን ሲገልጥ፣የምወደው ልጄ ይህ ነው፣ስሙት ብሎ አረጋግጦለታል።

ይህንለማጣመታታ አያ ዲዳትና መሰሎቹ ብዙ ያልተያዘ ነገር ዘባርቀዋል፣ለፍልፈዋል። የሚያነቡት ሰላልገባቸውም ይሁን ለራሳቸው ዓላማ እንዲመቻቸው አይሁድ፣ እስራኤል፣ነቢይ ወዘተ የመሳሰሉትን ቃላት ሁሉ ያለቦታቸው ያስገባሉ።አይሁድን በእስራኤል ፈንታ፣መመሳሰልን በማጠቃለል ያስገባሉ። ይህን ለማረጋገጥ በመቅደሙ የተጠቀሱትን እስላማውያን ከታባት ማንበብ ይቻላል፣እኛ ግን ያን ሁሉ ገለብጠን በዘመነ ውድ ወረቀት ማባዛት ስለማንችል የሚከተሉትን አናቀጽ ብቻ ገልብጠን ላንባቢ አቅርበን እንዲህ ይላሉ እያልን እናልፋለን።

(ከአያ አሕመድ ዲዳት መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙሐመድ ምን ይላል? ገጽ.6)

አንቀጹን በአፍሪካንኛ አንብቤ እንደ ጨረስሁ በተሰባበረ እንጋገሬ ይቅርታ ጠየቅሁ። ካህኑ ደኅና እንደ ተናገርሁ አረጋገጠልኝ። ወዲያውም ይህ ትንቢት ማነን ይመለከታል ብዬ ጠየቅሁ። ቅንጣት ታህል ሳያመናታ ኢየሱስንቢል መለሰልኝ። ለምን ኢየሱስን የእሱ ስምኮ ከዚህ አልተጠቀሰም አልሁኝ።ካህኑም ትንቢቶች ወደፊት የሚሆነውን ነገር የሚገልጡ የቃላት ሥዕሎች እነደ መሆናቸው መጠን በዚህ አንቀጽ የተደረደሩት ቃላት እሱን ጥሩ አድረገው ሲገልጹት እናገኛለን

በዚህ ትንቢት ውስጥ እንኳ እንዳተ ያለ የሚሉትን እጅግ አስፈላጊ ቃላት ማየት ይቻላል። ዝጆኹቱ እንደ አንተ ያለ ሲል እንደ ሙሴ ያለ ማለቱ ነው። እናም ኢየሱስ ከሙሴ ጋራ ይመሳሰላል አለኝ። እንደምን አድርጎ ነው ኢየሱስ ከሙሴ ጋራ የሚመሳሰል? ብዬ ጥያቄ አቀረብሁ የካህኑ መልስ እንዲህ የሚል ነበር፤በመጀመሪያ ደረጃ ሙሴ ይሁዳዊ (አይሁድ) ነበር፤ (ሙሴ በነገዱ ሌዋዊ፤በሕዝቡ እስራኤላዊ እንጂ ይሁዳ ወይም አይሁድ አልነበረም።) ኢየሱስም እንዲሁ አይሁድ ነበር፤በሁለተኛ ደረጃ ሙሴ ነቢይ እንደ ነበረ ሁሉ ኢየሱም ነቢይ ነበር፤ስለዚህ ኢየሱስ ሙሴን ይመስላል። እግዚአብሔርም ለሙሴ እንዳንተ ያለ ነቢይ ብሎ የተነበየለት በትክክል ይህንን ነው። በሙሴና በኢየሱስ መካከል ያለ ሌላ መመሳሰል ልታስታውስ ትችላለህ? ብዬ ጠየቅሁት። ካህኑም ሌላ እንደማያስታውስ ተናገረ። "ዘዳግም.18:18 ላይ በሰፈረው ትንቢት የተሚነውን ለማግኘት መመዘኛዎቹ እነዚህ ብቻ ከሆኑ በዚህ መሠረት ከሙሴ በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱት ውስጥ ሰሎሞን፤ኢሳያስ ሕዝቅኤል፤ሆሴዕ፤ኢዩኤል፤ሚልክያስ ዮሐንስ መጥምቁ ወዘተ. የመሳሰሉትን መመዘኛው ይመጥናቸዋል ማለት ነው። ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ አይሁዶችም (ሁሉም እስራኤላውያን እንጂ አይሁድስ አልነበሩም) ነቢያትም ነበሩና ነው። ለምን ትንቢቱን ከእነዚህ ነቢያት ለአንዱ አንሰጥም? ለምንስ ለኢየሱስ ብቻ እንሰጣለን ለምንስ አንዱን ብስል ሌላውን ጥሬ እናደርጋለን? አልሁት። ካህኑ ምንም አልመለሰም። ቀጠልሁ፤አየህ፤የኔ መደምደሚያ ኢየሱስ ከሙሴ ጋራ በእጅጉ አይመሳሰልም የሚል ነው፤ከተሳሳትሁ እንድታረም እፈልጋለሁ።

በዚህ አኳኋን እየደነፋ እስከ እንቀጹ ፍጻሜ ድረስ ሌሎቹን አለመመሳል ቀጥኳል፤እነሱም፤አባትና እናት፤ታምራዊ ልደት የጋብቻ ትስስር፤ኢየሱስን ወገኖቹ አልተቀበሉትም፤ሐዲስ ሕግጋት አላወጣም አሟሟታቸው የሰማይ ቤት ማረፊያ ወዘተ. ምዕራፉ ስለረዘመ ለአንባቢ እንዳይሰለች ከዚህ ላይ ገተን የሙሴንና የኢየሱስ መመሳሰል የሚያሳየውን ምዕራፍ 10 እንዲያነብ ጠቁመን ወደ ሚቀጥለው እንሸጋገራለን።

<u>ምዕራፍ 14፣</u>

## <u>የመሐመድ ታሪክና ስልምና</u>

ይህ መጽሐፍ ከሁለት ሊከፈል ይችላል፤ክርስትናና ስልምና ተብሎ፤በመጀመሪያው ክፍል ባጭሩ የክርስትናን ምንነት የክርስቶስን ማንነት ገልጠናል በሚቀጥለው ደግሞ ስልምናንና መሐመድን እንገልጣለን። ከመሐመድ ታሪክና ከስልምና ምንነት ኃሊ ኃሊውን (ኳርኳሩን) እነሆ! በ570 ዓ.ም አካባቢ የበላሞች መሪ መሐመድ በመካ፣ከአቶ አብደላ እና ከወ/ሮ አሚና ተወለደ። ግን አባቱ መሐመድ ገና በማሕፀን ሳለ፣ተወልዶ ሳያየው ሞተ። እናቱም ከጥቂት ዓመት በኋላ ባሏን ተከተለች። አሚና የመሐመድ እናት ገና በሕይወቷ ሳለች ለሀሊማ ለአሳዳጊነት ሰጥታው ነበረች። በሲራቱል ራሱል (ገች:105-16) እንደ ተጻፈው፣መሐመድን አንድ አስቸጋሪ መንፈስ እንደ ያዘው ተገንዝቦ፣የሀሊማ በዓል፣ሀሊማ!ይህን ልጅ መንፈስ ርኩስ ይዞታል ብዬ አምናለሁ፣ከመገለጡ በፊት ወደ ዘመዳቹ ውሰጅው አላት።

ሀሊማም ለእናቱ ለአሚና በሰጠችው ጊዜ እናቱ አሚና ደንግጣ ሰይጣን፣(ጂኒ፣መንፈስ ርኩስ) ይዞታል ብለሽ ታምኛለሽን? አለቻት። ሞግዚቷም አዎን አለች። (Mijanul Hagg page 347)

ዓሊ ሃባቢም ኢንሳኑል ኡዩል በሚለው ሥራው፣የመሐመድ እናት አሚና መሐመድን ከዐይነ ጥላ፣ከዛር፣ከጅን፣ከአዶ ከብሬ ልታድነው አስማትና መተት ትጠቀም ነበር። (እምነ ዝኩር) በአረኝነቱና በጎረደማንነቱ ጊዜ ያለው ታሪኩ በዝርዝር አይታወቅም፤በዚህ ጊዜ አንድ ድርጊት ተፈጽሟል፤ከሌሎች ልጆች ጋራ ሲጫወት ገብርኤል የሚባል ዛር ወይም መንፈስ ወደ እሱ መጣ። ያዘውና ከመሬት ላይ ጥሎ ልቡን ቀደደው፤ቀዶ ከልቡ የረጋ ደም ያዘና ይህ ካንተ የሰይጣን ድርሻ ነው አለ። ልጆችም ወደ ሞግዚቱ እየሮጡ መጥተው በርግጥ መሐመድ ተገድሏል አሏትና ተመልሰው ሊያዩት ቢሄዱ ቀለሙን ለውጦ አገኙት። (muslim) miskat (v) page 36)

ከዚህም በላይ መሐመድ ራሱን ሊገልድል ያሰላስል ነበር፤)ሲራቱል ራሱል ቁጥር 156) መሐመድም በአባቱም በእናቱም ዕጓለ ማውታ ሁኖ ቀረ። ስለዚህ የአባቱ አባት አያቱ አብደላ ሙታሊብ ሊያሳድገው ወሰደው፣ግን እሱም ከሁለት ዓመት በኋላ ሞተና ዐረፈ። ከዚያ በኋላ መሐመድ ወደ አጎቱ ወደ አቡ ጣሊብ ሞግዚትነት ተዛወረ። ከአቡ ጣሊብ ጋራ ሲኖር እስከ 12 ዓመቱ እረኛና ዕንጨት ለቃሚ ሆኖ አደገ፤በዚህ ጊዜ በእየሚዳውና ጫካው፣በእየዛፉ ሥር ሲተኛ መንፈስ ርኩስ ተደርቦ ለከፈው፣ስለዚህ እየታመመ ይቸገር ነበር፤ዘመደቹም በመስቀልና ጸበል ለማስለቀቅ ሞክረው ሳይሆንላቸው ቀረ። መስቀልንና

የስቅለትን ታሪክ ለዘለዓለሙ ጠልቶ የቀረውም በዚህ ምክንያት ነው። መልከ መልካምና ደመ ግቡ ከሆነ ካልተጠመቀ፣ብዙ የሀገር ቤት ልጅ ሁሉ የዚህ ዐይነት ችግር ይደርስበታል፤መሐመድም መልከ መልካም ወይም ደመ ግቡ ስለ ነበረ፣ያቃጀው፣ ያስጎራው፣ባሪያም ይጥለው ነበረ።

ከበሽታው ሲነቃ ተግባሩን በትጋት ስለሚፈጽም አጎቱ አቡጣሊብ ይወደው ነበር። በ12 ዓመቱ ወደ ሶርያ ለንግድ ሲሄድ አስከትሎት ሄደ፤በዚህ ጊዜ ከአይሁድና ከክርስቲያን ኅብረተሰብ ጋራ ተዋወቀ። ከእነርሱም ጥራዝ ነጠቅ ወሬን አጠራቀመ። ከዚያ ተመልሶ አንድ ጊዜ ጎረደማን፣በሌላው ጊዜ ደግሞ እረኛ እየሆነ ወደ ሃያ ዓመቱ ተጠጋ። ከዚህ በኋላ ባሏ ለሞተባት አንድ ሀብታም ቱጃር ነጋዴ ወይዘሮ ከዲጃ ተቀጥሮ ከመካ ሶርያ፣ከሶርያ መካ እያለ ሲራራ ነጋዴ ሁኖ ንግዱን ያጧፈው ጀመር። ከዲጃም መልኩንና ትጋቱን ዐይታ ለጋብቻ ጋበዘችው፤እሱም ምንም ከቁሬሽ ወገን ቢሆኑም ትውልዱ፣ ዕንኳ ማውታና ገንዘብ ወዳጅ ስለሆነ፣15 ዓመት እንደምትበልጠው እያወቀ የጋብቻውን ግብዣ ተቀበለና፣ተጋብተው እስከ ከዲጃ ዕለተ ሞት ድረስ በፍቅር ኖሩ። ሀብቷ ይቀርብኛል ብሎ በኋላ ያሳየውን የአምንዝራ ጠባዩን ደብቆ ኖረ። በዚህ ጊዜ ብዙ ነገር ተሠርቷል፤

1. መሐመድ ውቃቢው (ጌታው) ሲወርድበት ይጨነቃል፣የሚሆነውም ይጠፋዋል፤ፊቱ ይለወጣል፣ይቸገራል፤በጣም ይከብዳል፣ከግመል ላይ ሳለ የሆነ እንደሆነ ግመሏ ከብዷት ትወድቃለች፣ትሰብራለች። ይህንም ዘይድ ገልጦታል፤አንድ ጊዜ አንድ እግሩ ከላዬ ላይ ወድቆ መንቀሳወስ አቃተኝ፣እንደዚህ ያለ ከባድ እግር አይቼ አላውቀም። ነብዩ ባጎራ ቁጥር፣ነፍሱ ከሥጋው የተለየች ትመስላለች፣የሰከረም ይመስላል፤ምክንያቱም ባሪያ ይጥለዋልና ነው። (ኢንሳኑልኡዩም በሚዛኑ አልሐቋ እንደ ተጠቀሰ p.346)

2. ከዲጃን ካገባ በኋላም በእየዚዜው ወደ ሂሩ ተራራ ዋሻ እየሄደ ይሰነብት ነበር። ከዚያ ምን እንደ ሚያደርግ አይታወቅም፣ሲመለስ ግን ያገዝፈዋል፣ያንቀጠቅጠዋል፣ይጥለዋል፣ያደፍቃል።ወባ እንደያዘው ብርድ ብርድ አለኝ፣ በረደኝ አልብሱኝ ይላል፣ለያዥ ለገራዥ ያስቸግራል። እንዲህ እንዲህ ሲል ቆየና፣በእየሀገሩ እንዳሉት ባለአውላዎችና አጉርዋች ገብርኤል ታየኝ እያለ ይለፈልፍ ጀመረ። (ማ! ይሙት? ለዘካርያስ የዮሐንስ መጥምቅን ከክርስቶስ በፊት መምጣት የነገረ፣የእግዚአብሔር ልጅ ከአንቺ ይወለዳል ብሎ ለድንግል ማርያም ያበሠረ፣መልአክ እግዚአብሔር ቅዱስ ገብርኤል፣እንዴት ቃሉን ለውጦ፣አምላክ አይደለም፣አምላክ አልተወለደም፣አይወርድም አይወለድም ይላል? ስለዚህ በመሐመድ ላይ ያደረ ርኩስ መንፈስ

አይወለድም ይላል? ስለዚህ በመሐመድ ላይ ያደረ ርኩስ መንፈስ በገብርኤል ስም እየተጠራ ታይቶታል እንጂ እግዚአብሔርና ገብርኤ ልስ ቃላቸውን አይለውጡም፣ለአስተርየም እንደ ዛር እያንቀጠቀጡም እንደባርያም ጥለው አረፋ አያስደፍቁም፤ እንዲህ ያለ እንኳንስ በቁርአን እንኳ ታማኝነታቸውና፣ ከሰማይ መውረዳቸው በተመሰከረላ ቸው ቅዱሳት መጻሕፍትና በአዋልድም የለ፤ ከዚህ ላይስ ፍርዱን ለአስተዋይ አንባቢ መተው ይሻላል መሰለኝ፡ በሂሩ ዋሻ እየገባ ይዘጋ ነበር፣ለብዙ ሌሊት፣በዚህ ጊዜ አላህ አልተገለጠለትም ነበር።

3. ያን ጊዜ (ገብርኤል) ይዞ፣ለሦስተኛ ጊዜ ተጫነኝ ትልቅ ድካም እስኪሰማኝ ድረስ አለ። ወደ ቤቱም እንደ ተመለሰ ከዲጃ ከዲጃ ጠቅልይኝ ጠቅልይኝ አለ። እነሱም ፍርሃቱ እስኪለቀው ድረስ ጠቀለሉት። (mishat (v) pages 356-357) ከዲጃም በእየጊዜው ከዱር እየገባ በመጣ ቁጥር ታጥናናው ነበር (እምነ ዝኩር ቁጥር 154)

4. ኢብን ይሥሐቅ በመጀመሪያ አስተርእዮ (መገለጥ) ከሱ ላይ ከመውረዱ የመሐመድ ጓደኞች ዐይነ ጥላ ወይም መንፈስ ርኩስ አለበት፣ይዞታል እያሉ ይፈሩ ነበር። ያው በሽታ እየመጣ በእየጊዜው ይጠናወተዋል።መሐመድም እኑሪ ወይም የጅን ማደሪያ እሆናለሁ፣ያለ ዚያም እብዳለሁ ይል ነበር። ወይም ጋኔን በላዬ ላይ ያድራል እያለ ይሠጋ ነበር። ከመንቀጥቀጥና ዐይኖቹን ከመዝጋትና መክፈት መጨፈን በኋላ፣ባሪያ ይጥለዋል፣አረፋ ያደፍቃል፣እንደ ጎረምሳ ግመል ያጓራል (Mijanul Hagg: pages 345)

5. ለአይሻ የአላህ መልእክተኛ፣አንዳንድ ጊዜ ቃጭል እየደወለ ይመጣብኛል፤ከሁሉም የሚያስፈራኝ ይህ ነው። አንዳንድ ጊዜ መልአኩ ሰው መስሎ ይታየኛል፣እየታየ ያናግረኛል፣እኔም የሚለኝን በቃሌ አጠናለሁ።

6. አይሻም፣በእርግጥ ውቃቢው ሲወርድበት ሳለ አይቸዋለሁ። በጣም ብርድ ቀን ነበር፤ግምባሩን ላብ ከጥለቀለቀው በኋላ ተወው። (Mishkat (V, page 360) ::

ከዚህ ላይስ የመሐመድን ጅብሪል የመሰለ ጅኒ፣ኢልቢስ፣ዛር፣አውሊያ ውቃቢ ልጠቀስ መሰለኝ። ይቅርታ ይህን ሁሉ ስም የሰጠሁት የርኩሳን መናፍስትን ተፈጥሮና ጠባዕይ በደንብ ስለማላውቅ ነው፤እኔ አውቃለሁ የሚል ቢመጣ ግን ለመስማት ዝግጁ መሆኔን አስቀድሚ በትሕትና እገልጣለሁ። ርኩሳን መናፍስት በእያጉሪው ቤት እንደሚሰ ማው ልዩ ልዩ ናቸው። በግብርም ሆነ በፍርድ ይለያያሉ። እንዱ የሚያመሰግነውን ሌላው ይረግማል። በቅዱሳን መላእክት፣ጻድቃን፣ሰማ ዕታት ስም ይሰየማሉ። ሚካኤል ነኝ፣ገብርኤል ነኝ፣ማርያም ነኝ፣

ጊዮርጊስ ነኝ፣ወዘተ. እያሉ፣የሚካኤል ለት፣የገብርኤል ለት፣የማርያም ለት አክብሩን፣ዘክሩን፣ዘይሩልን፣ቡና አፍልታችሁ ጨፌ ጎዝጉዛችሁ፣ ጫት እየቃማችሁ መሥዋዕት አቅርባችሁ ካድሙን ይላሉ።
አጉሪው ፈረስ፣አስጎሪው እንደ አካባቢው፣ውቃቢ፣አውሊያ፣ጌታ ወዘተ. ይባላል። ውቃቢ ሲወርድ፣ፈረስ ሲገዝፍ ጸታው የጌታው እንጂ የፈረሱ አይደለም፣ማለት በወንድ ላይ ማሪያም የወረደች እንደሆነ እስክትሄድ ድረስ ወንዱ ፈረስ (አጉሪ) እመቤታችን እየተባለ ነው የሚቀላመጥ። በሴት ላይ ደግሞ ሼክ አንበሶ፣ግራኝ ወይም ጠቋር የወረደ እንደሆነ አሁንም እስኪሄድ ድረስ ጌታዬ! ጌቶች! እየተባለ ይከደማል። ዛር ፈረሱን ያንቀጠቅጣል፣ያንዘፈዝፋል፣በረደኝ አልብሱኝ መጣሁኝ፣ካድሙኝ እያሰኘ ያፈራግጣል፣ያስደፍቃል። የመሐመዱ ጅብ ሪልም አውሊያ ስለሆነ የሚያደርገው እንዲህ ነበር።
ለዚህም የተጨባጭ ማስረጃ ጎሚፈልግ በአገው ምድርና በዳሞት አካባቢ ያለችውን ማርያምን እናቀርባለን። እስዋም ሦስት ስም አራተኛ ቅጽል አላት፤ማርያም፣እመሙላድ፣ውርዝልያ፣እመቤታችን። ይህች ዛር፣መንፈስ፣ውላጅ ተፈጥሮዋ ከምን ንጥረ ነገር እንደሆነ አይታወቅም። ጸታዋም እስዋ በምታስጎራቸውና በምታሳልማቸው ሰዎች ታሪክ የተመሠረተ ነው፤ማርያም ነኝ እያለች የማርያም የማርያም ለት በእየወሩ በ21 ትከበራለች፣እሷ የምትገዛው ቤትሰብ አንድነት ተሰብስቦ፣በወተት የተገነፋ፣በቅቤ የጠለቀ ገንፎ ይዘጋጅና ይበላል። ባዳ ሰው አይበላውም፣አገቡኝ ወስንም ካልወለደ አይበላም ክልክል ነው። በስሟ ከብት ይረባል፣ገንዘብ ይጠራቀማል፣ንስት ንስቱ ይዋለዳል፣ተባት ተባቱ ይሸጥና ንስት ይገዛበታል ወይም ጥሬው ብር በቶፋ ይቀበራል፤የተቀበረውን ገንዘቧን የሰረቀ ወይም የበላ ይሞታል ይባላል። ሌባም ከብቷን አይነካም። የምትገለውም በፊንጢጣው አንጀቱን አውጥታ ነው። ያለ ዘሩ ማንኛውም ሰው አንጀቱ የወጣብት እንደሆነ ወይም ወደ ባህል ባለመድኀኒት ሂዶ ያስመልሰዋል፣በተቀረ ው ጊደር ገዝቶ ለማርያም ከብት ያቆማል። ከዚያ በኋላ በእየወሩ እየደገሠ ሲያከብራት ይኖራል።
የእመ ሙላድ ተገኘዎት ኸመቤታችን ማርያም ነው የሚሏት። ከድንግልና በቀር የቅድስት ድንግል ማርያም ቅጽል ሁሉ ይሰጣታል። እምቢ ካለ ግን አንጀቱ ተጎልጉሎ ወጥቶ፣ብዙ ቀን ተደይና ለሌላው ማስፈራሪያና መቀጣጫ ሁኖ ይሞታል ይላሉ።

እንዲሁም የመሐመዱ መንፈስም ከውርዝልያ፣እመ ሙላድ አይለይም፣ይህች የቅድስት ማርያምን ስም እንደመረጠች ያም የቅዱስ ገብርኤልን ስም መርጦ ዓለምን ያታልላል። እንዲህም ስለሆነ የብዙ አውሊአዎች አለቃ ሊባል ይቻላል።

7. የማንንም ግጥም አጥንቶ፣እያስጠና የኔ ነው ይል ነበር። በዚህም ከገጣሚዎች ጋራ ከሰማይ ከአላህ ወረደ እያለ ይጣላ ነበር። ገጣሚዎች እንደዛሬ ጋዜጠኛ ከካዕባ ላይ አስቀምጠው የፈለገ ያንብ ብለው ይሄዱ ነበርና ኢምራኡል ካይም ምእለቃት የሚል ግጥሙን ከካዕባ ላይ ጥሎት ሄደ፣ያንን መሐመድ ሆዬ! አንሥቶ ለልጁ ለፋጢማ ያስጠና ታል፣እሷም ሰዓቲቱ ደረሰች ጨረቃም ተገመመሰች እያለች በመንገድ እየዘመረች ስትሄድ የኢምራኡል ካይስ ልጅ ሰማቻትና ይህማ የአባቴ ግጥም አይደለ? እንዴት ነው ከሰማይ የወረደ የምትሉት አለቻት፣ወዲ ያው ሂዳ ለአባቷ ለመሐመድ ነገረችው እሱም በአስተባባዮቹ ላይ አንድ ግጥም ገጥሞ ከሰማይ ነው የወረደው አለ። (ሱራህ:10:39) ይልቁንም ዕውቀቱን ባልደረሱበት፣ፍችውም ባልገባቸው ነገር አስተባ በሉ፣እንደዚሁም እነዚያ ከእነሱ በፊት የነበሩት አስተባብለዋል። የኢምራኡል ካይስ ግጥም ከቁርአን ጋራ ተመሳሳይ ነው፣ስለዚህ በእየጊዜው መሐመድ እየሰረቀ የኔ ነው ይል ነበር። አንድ ቀን መሐመድ ለጉባኤው ጸልዮና ቁርአን አንብቦ ከወጣ በኋላ፣የአልሃሪት ልጅ ናድር ገብቶ የሩስተምንና የእስፋደያር የፍርስን ነገሥታት ተረት ነገራቸው። በእግዚአብሔር እምላለሁ፣የመሐመድ ተረቶች ከእኔዎች አይሻሉም። የጥንት ተረቶች እንጂ ሌላ ምንም አይደሉም። እኔ የኔዎቹን እንደ ጻፍኳቸው፣ እሱም ከዚህም ከዚህም የለቃቀማቸው ናቸው። ለዚህም ነው መሐመድ ከሰማይ ወረደ ብሎ በቁርአን (ሱራህ:27.6.) መልሷል፤በርግጥም አስተባበሉ፣በዚያም በእርሱ ተሳለቁበት የወሬውም ግፍ ይመጣባቸዋል።

ስለጤናው ብዙ ከሃዲስና ሱናህ መጥቀስ ይቻላል ግን እስከዚህ የተባለው ይብቃንና ወደ ጠባዩና ጭካኔው፣ውሼቱ እንመለስ።

<u>የመሐመድ ጭካኔና ጠባዕይ።</u>

ብዙ ጊዜ የጦር መሪዎች፣ታላላቅ የሚባሉት ጨካኞች፣ሰው አራጆች፣ ሰካራሞች፣አመንዝሮች፣ከሐዲዎች ናቸው። መስፈርቱ ይህ ከሆነ መሐመድ ሁሉንም ይበልጣል። መሐመድን ትልቅ ነው ከሚሉት ጸሐፊዎች ጋራ እኛም በዚህ እንስማማለን። በተቀረ በዚህ ተቃራኒ መስፈርታቱ፤ርኅሩኅ፣ ለሰው ልጅ ደግ መሥራት፣የእግዚአብሔርን መንግሥት ማስፋፋት፣አድልዎ የሌለበት ሕግ ማቋቋም፣ሁሉንም በሃይማኖቱ፣በጸታው እኩል ማየት የሆነ እንደሆነ ግን መሐመድ አልቦ (ዜሮ) ነው። ይህንም በሚከተለው አንድ ባንድ እንገልጣለን፤

1. ከመዲና ወደ መካ ሲመለስ፣ተመልሶ በድል አድራጊነት ሲገባ፣ ወገኖቹን፣አብሮ አደጎቹን፣ዘመዶቹን የቁሬሽን ጎሳዎች፣ያክስት ያጎቶ ቹን ልጆች ማረ ብለው እነዲዳት መሐመድ መሐሪ ነው ይላሉ። እነዚህን የማረበት ምክንያት በዝምድናና በጥቅም እንጂ በምሕረት

አይደለም። የቀረውን ሕዝብ ግን በጦርነት ድል ሁኖ የተማረከውን ሁሉ ከአራት ዓመት ሕፃን ጀምሮ ያለምንም ምሕረት ይጨፈጭፍ ነበር። ራሱ ቁርአንም በሃይማኖት እያመካኙ ለሰው ማረጅና ለዘረፋ የተመቸ የፓለቲካ መመሪያ ነው።

አንድ ቀን ከመስጊድ ተቀምጠን ሳለ፣የአላህ መልእክተኛ መጣና ተነሡ ወደ አይሁድ እንሂድ አለን። እኛም ከእነሱ እስክንደርስ ድረስ አብርነው ሄድን። የአላህ መልክተኛም ቆሞ እናንተ አይሁድ! መሬት የአላህና የመልእክተኛው መሆን እንዳለባት ማወቅ አለባችሁ፤ስለዚህ ከዚህ አባርራችኋለሁ ብሎ (መከላከያ የሌላቸውን) አባረራቸው፣ባኑ በዲር ሲሸሽ አሲዞ አስገደለው፣ባኑ ኩአይዛን ደግሞ ስለተከራከረ አሰየፈው። (ሳሂህ ሙስሊም ገቅ:963-960 ና ሚስካት 27.454)። ወንዶቻቸውን ገደለ፣ሴቶቻቸውንና ንብረታቸውን ለሰላሞች አካፈለ። (ሳሂህ: ሙስልም: 3:ገፅ 963-964) ሃይማኖት በግድ አይደለም የሚለው የቁርአን ደራሲ እንዲህ ያደርጋል። ስልምናን የተቀበሉ የኩራያዛ ጥቂቶች ተማሩ፣እስራኤል ወይም ክርስቲያን ነን ያሉ ግን ያለምሕረት ተጨፈጨፉ። እንደ ሰይድ ያሉት ጨካኝ አራጆችም የአላህን ፈቃድ ነው የፈጸምሀ እየተባሉ ተሸለሙ፣ተመሰገኑ (እምነ ዝኩር 7.966)።

2. አንድ ቀን የአላህ መልክተኛ ወደ መዲና ገበያ ሂዶ ሰፈ ግድጓድ አስቆፈረ፣አስቆፍሮ፣ከ800-900 አይሁድና ክርስቲያን በቁመናቸው አስገብቶ አፈርና ደንጊያ አስሞላባቸው። (እምነ ዝኩር)

3. አይሻ የመሐመድ ብርቅዬ ምሽቱ፣(አንድ ቀን ደግሞ መሐመድ አቅም የሌላቸውን ሲያርድ ሲያሳርድ) የአላህ መልእክተኛ ወንዶቷን ሲጨፈጭፍ አንዲት ሴት ከኔ ጋራ ነበረች፣ጠሪ ጠራት፣እሷም አቤት አለች፣እኔም ወዮልሽ ምንድር ነው? ወንድ እንጂ ሴት አይገድሉ አልኳት፣እሷም ወዮልኝ እገደላለሁ አለችኝ፣እኔም ለምን አልኳት፣እሷ ም ስለተናገርሁ ብላ መለሰችልኝ። ወዲያውም ከአላህ መልእክተኛ ፊት ወስደው አረዷት።

አይሻ እስከ ዕለተ ሞቷ የዚያች ሴት ሥቃይ ይታየኛል ትል ነበር። ከዚያ በኋላ የአላህ መልእክተኛ የባኑ ቁራይዛን ሀብት ንብረት፣ሴቶች ን ለፈቃድ መፈጸሚያ፣ልጆቹን ለባርነት ለሰላሞች አከፋፈለ። ለራሱም የአላህ መልእክተኛ ከሴቶች መካከል ረሃናን መረጠ፣እሷም መሐመድ እስከ ሞተ ድረስ ከዕቁባቶች አንዷ ነበረች እንዲህ ያለ ነው የሰላሞች መሪ፣አታመንዝሩ ይላል፣እሱ ግን በአዕቁባት ነው።(ሲራቱል ራሱል ቁ689-693)

ሰላም እንደያመነዝር ከቡና ቤት ወይም ከመንገድ ሴት ይዞ ይሄድና ከምኝታ ክፍሉ ሲደርስ አንድ ትንሽ ነገር የዛሬው ሁለት

ወይም አንድ ብር፣ወይም መሐረም የሆነ ነገር ሰጥቶ ጥሎኝ መሆኑ ነው፣ሦስት ጊዜ አግብቼሻለሁ፣ አግብቼሻለሁ፣ አግብቼሻለሁ፣ ብሎ አብሯት ያድራል፣ሲነጋ ደግሞ። ውሸት መናገር ቢኖርብንሳ? ተናገር ብሎ አዘዘው፣ፈቀደለት። ሦስት ጊዜ ፈትቼሻለሁ ብሎ ወደ ጉዳዩ ይሄዳል። ይህ እንኳ ሰሪሃና አልተደረገላትም።

3. ጦርነቱ አልፎ ከተረጋጋ በኋላ ካቢብኑል አሻርን መሐመድ ኢብን ማስላማን ጠርቶ መግደል ተለማመድበት ብሎ አሳረድቷል።

4. ከዓብንም አማን አገር ነው ብሎ ያለመሠሪያ ከተቀመጠበት እነመሐመድ ኢብን አስላማን ሦስት አድርጎ ልኮ አሳረድቷል። (3ኛ ሲያህ ሙስሊም ገቅ 990-991)።

5. ሲራቱል ራሱል (ገቅ 550-553)ከዚህ በላይ አብራርቶ ይጽፋል። መሐመድ ኢብን ማስላማ ዐቅሙን ተጠራጥሮ ይጠይቀዋል፣የአላህ መልክተኛ መሐመድም በአንተ ሥልጣን የወደቀብህን ሁሉ ለመፈጸም ጠንክር ብሎ አዘዘው፣ፈቀደለትም (በዚህም መሐመድ ፖለቲሻን እንጂ የሃይማኖት ሰው አለመሆኑ ይታወቃል።)

6. ከቆመበት የካብን ጎፈሬ ይዞ በለው አለው ጓደኛውም በየፈው ወደቀ፣ወዲያውም ሐኒዬ ትዝ አለኝና በሆዱ ብከተው በጀርባው ወጣ። አንድ ቀን ደግሞ አንዱን ገድለን ወደ መሐመድ አመጣንለት፣ እሱም ተፋበት። ከዚያው ቋጥር ኢብን ይሥሐቅ የአላህ መልእክተኛ ሆይ? ምን ላድርግ ቢለው ያገኘኸውን ይሁዳ ሁሉ ያለምሕረት ግደል አለው። ስለዚህ በንግድ የሚወደዳራቸውን ሁሉ የመሐመድ አሽከሮች እየዞሩ ይገድላሉ፣መሪያቸውም አበጀህ እያለ አረመኔአዊ ግብራቸውን ያሞግሳል፣ያሞካሻል።(ገቅ: 714- 715)

7. አንድ ቀን ደግሞ የመሐመድ ተከራካሪ ትዝ አለንና አሰፈቅደን ከተኛበት ገብተን፣ቤቱን ዘግተን አረድነው። በሰይፉ አንገቱን ስንቀላው አብዱላ ኢብን ኡናይስ ደግሞ ሰይፉን ከሆዱ ከተተበት።

8. በዚሁ ዐይነት የመቶ ዓመት አረጋዊ አቡ አታክንም አረደው፣ገጣሚዋ አስማ ማርባንን አስደብድቦ አስገደላት። (ከዚያው 7.995) የአላህ መልእክተኛ ከማርባ ልጅ ማነው የሚገላግለኝ? አለ። ኡመር ኢብን ኡዳይም ሂዶ ገደላት፣ገድሏትም ተመልሶ፣የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ገደልኳት እኮ አለው። መሐመድም ኡመር ሆይ! አበጀህ፣አላህንና መልክተኛውን ረዳህ አለው።

9. (ሚሽካት 47:404) ግሩም የሚከተለውን መዝግቧል፤ትዱሉ ተላኪ አንድ ቡድን ወደ አቡ ራፌ ላከ። አብዱላ ኢብን አቲክም ከቤቱ ተኝቶ ሳለ ገብቶ ገደለው። ተመልሶም ለመሐመድ ሰይፌን በጀርባው እስኪወጣ ድረስ በሆዱ ከተትሁት ብሎ ፈከረ። በክርስቲያን ዐይን

ይህን የመሳሰሉት ተግባራት መሐመድን ጨካኝ ጀነራል እንዲ ነቢይ አያስኙትም። በእየናቸው መረጃዎች መሠረት መሐመድ በአጠቃላይ የሚከተለውን ይመሳሰላል፤ ሲሉ ስምታ፣ዶር ሞተች በጢስ ገብታ እንዲሉ፣ቅዱስ ጳውሎስ እኔ ክርስቶስን እንደመስልሁ እናንተም እኔን ምሰሉ፣ያለውን ይዞ መሐመድም እኔን ምሰሉ ብሏል፤ (ሱራሀ:3:31) አላህን ብትወዱ፣ከወደዳችሁ እኔን ተከተሉ (ሱራሀ:33:21) በአላህና በምጽአት ተስፋ ላላችሁ ሁሉ የምግባር አብነት የአላህ መልእክተኛ አለላችሁ ይላል፣እንዲህ ያለ ጥሪ ያቀረበው ማነው? ለሚል ጠያቂ፤

ሀ. መሐመድ ከዚህ በፊት ባየነው መሠረት፣ከሕዝብ ዐረብ፣ከሀገር ዐረቢያ፣ከከተማ መካ ከጣዖት ከዕባ ብሎ የተነሣ ለጊዜው የተሳካለት ነጋዴ፣በኋላ ከጨካኞች የጦር መሪዎች ጋራ የሚወዳደር ደም ለማፍሰስ የሚስገበገብ ጨካኝ የወታደር መሪ መምለኬ ጣኦት በዚህም ከሞንጎሉ ጀንጊስ ካን፣ ከጀርመኑ ሂትለር ጋራ ይመሳሰላል። ገንዘብና መሬት ካየ መከላከያ የሌለውን ሕፃን፣ሽማግሌ፣ሴት ባልቴት ሳይለይ ያርዳል፣ይጨፈጭፋል።

ለ. በጸሎት እያመካኘ ዋሻ ገብቶ መንፈስ ርኩስ በገብርኤል ስም እያሳበ ወይም ሲያጎራ ስንብቶ ይመጣል።

ሐ. ይጥለውም ያጎራም ነበረ።

መ. ከዕቁባቶቹ ሌላ 13 ምሽቶች ነበሩት። በዚህም ሕግ ብሎ እራሱ እንዳወጣው በቁርአኑ መሠረት ሳይሆን ያለ ተራ ከወደዳት ጋራ ያድር ነበር። ጌታ በጥንተ ተፈጥሮ አንድ ላንድ ብሎ ሴትና ወንድ አድርጎ የፈጠራቸውን (ለአዳም ማመንዘርን ቢፈቅድ ኑሮ የፈለገውን ያህል ሴት ይፈጥርለት ነበር። ለዘር ብቻ ከሚገናኙት ከእንስሳት ሁሉ ለይቶ በፍትወት ከወንድ እኩል አድርጎ የፈጠራትን ሴት ከወንድ እኩል አላደረገም። ሙሴና ክርስቶስ ያጠኑትን የእኩልነት መብት አፍርሶ ሴትን ለወንድ የምትናገር ከብት አድርጎአል።

ሠ. በመካ ጣዖት በካዕባ እንጂ በአንድ አምላክ አያምንም። በዐረቢያ የነበሩትን ጣዖታት አጥፍቶ በመካ ያለችውን ካዕባን የተወበት ምክንያትም መካ በቱሪስት ገቢ እንደትከብር ነው። እግዚአብሔር አምላክ ዓለም ነው፣በሄትኛውም አቅጣጫ ይገኛል፣ጸላይም በሄትም ዙሮ መጸለይ ይችላል። መሐመድ ግን ወደ መካ ካዕባ ወደ ምትገኝበት ዙራችሁ ጸልዩ፣ስገዱ አለ። ጥቁር ደንጊያ ካዕባ ውሱን ናት፣የምትገኘ ውም መካ ነውና ነው።

ከዚህ ላይስ እናንተም (አይሁድና ክርስቲያን) ወደ ኢየሩሳሌም ዙሩችሁ ትጸልያላችሁ፣ለታቦትም ትሰግዳላችሁ ይል ይሆናል የስላም ተከራካሪ፣ለዚህ መልሱ ቀላል ነው፣በጽላትና በቤተ መቅደስ የእግዚ

አብሔር ስም ተጽፏል፤ስለዚህ እኛ የምንሰግደው ለእግዚአብሔር ስም እንጂ ለመቅደሱ ደንጊያ ወይም ለታቦቱ ቁሳቁስ አይደለም። ይህም በሁሉን ሁሉን ይወቅ በሰሌው ተጽፏል።

ከሌላ በታ እንዳየነው ጣዖትን እግዚአብሔር በሚከተለው ሁኔታ በአሪት (ዘፀ.20: 3-4) ከኔ በቀር ሌሎች አማልእክት አይኑሩሀ፤በላይ ከሰማይ ካለው፣ በታችም በምድር ካለው፣ከምድር በታች ከውኃ ካለው ነገር፣የማንኛቸውንም ምሳሌ፣የተቀረጸውንም ምሳሌ፣የተቀረጸ ውንም ምስል ለንተ አታድርግ፣አትስገድላቸው፣አታምልካቸውም፣—። ከሰማይ ወረደች እያሉ የሚያመካኙበት ያች ጥቁር ደንጊያ፣የአምላክ ስም አልተጻፈባት፣ከግብጽና ከባቢሉን ጣዖት በምን ትለያለች?

ስለዚህ የመሐመድ ጥሪ፣አምላካችሁን ትታችሁ ኑና ጣዖት አምልኩ፣ አመንዝሩ፣ነፍስ በሃይማኖት እያመካኛችሁ ግደሉ፣ዝርፉ፣ውረሩ ነው።

ረ. መሐመድን የመሰለ ዋሾ ፖለቲከኛ ነበር፣አለ፣ወይም ይመጣል ለ ማለት በጣም ያደግታል። በእየቦታው እንዳየነው፣ከእሱ በፊት የነበረ ውን ገድላ ገድልና፣መጽሐፈ ባልቲት፣ተረት ሰብስቦ፣ከሰማይ የወረደ ልኝ ቁርአን ነው ብሎ ብዙ ሕዝብ አስቶአል። በዚህም የክርስቶስ ትንቢት ማቴ.24 በመላ ተፈጽሟል።

መሐመድ በእግዚአብሔር ስም ኀጋውን ለሚያታልሉ፣የመጀሪያው መሪ ነው።

ሰ. <u>መሐመድ ነቢይ አይደለም፣ነው ቢባልም። ከነቢያት ሁሉ ያንሳል፤</u>

ራሱ ከሰማይ ወረደልኝ እያለ በዋሸበት በቁርአንም ቢሆን መሐመ ድ ከሙሴ፣ከአሮን ከእኅታቸው ከመርያምና እግዚአብሔር እያነጋገረ ከላካቸው ነቢያት ሁሉ ያንሳል። እሱን ያነጋገረው ከላይ እንዳየነው በገብርኤል ስም ርኩስ መንፈስ ሲሆን፣ነቢያትን ግን ተገልጦ የታየ ችው ራሱ እግዚአብሔር ነው ያናገረቸውም መንፈስ ቅዱስ ነው። (ዘኁ. 12: 1-15፤1: ነገ.17: 1-6፤ኢሳ.6: 1-13)

# ምዕራፍ 15፤

## መሐመድ ያልሠራው ኀጢአት የለም፤

አንዳንድ ሰላሞች መሐመድ ኀጢአት አልሠራም ይላሉ፤ግን ከዚህ በላይ እንዳየነው በኀጢአት ሥራ የመሐመድ ተወዳዳሪ ፍጡር አለ ለማለት ያስቸግራል ቢባል ከውነት አይራቅም። ይህንም ከዚህ በፊት ባየናቸው መሠረት በቅደም ተከተል እንገልጣለን።

ሀ. ውሸታም ነው፤ ውሸትም ያስተምራል፤ተከታዩ የሚያስዋሽ ነገር ቢያጋጥመኝ፤ምን ላደርግ ቢለው ዋሽ ብሎ ፈቅዶላታል።

ለ. ከሐዲነው፤ ኦሪትና ወንጌል ከሰማይ መውረዳቸውንና ቅዱስነታቸ ውን በቁራን እያመነ፤እሱ ግን ክርስቶስ ሙቶ አልተነሣም፤ማርያም ደግሞ አምላክ ናት ይላሉ ክርስቲያኖች ብሏል፤ክርስቲያኖች ሥላሴ ሦስት ናቸው እነሱም አብ፤መርያም፤ወልድ ናቸው ይላሉ ይላል። የመንፈስ ቅዱስን ህልውና ይክዳል። ክርስቲያኖች አማልእክት ሦስት ናቸው ይላሉ ይላል። በዚህም በሐሰት አትመስክር የምትለውን ኦሪትን አፍርሶ በሐሰት መመስከሩ ነው።

ሐ. ጣዖት ያመልካል፤ ከኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ ያለውን ሕገ ኦሪት ጥሶ ለካዕባ ጥቁር ድንጊያ ይሰግዳል፤ያሰግዳል፤ ሌሎችንም ጣዖታትን አማልክት ያጠፋውም የእሱ አምላክ ካዕባ እንድ ትመልክና ከብፅዓት አድራሽ ከሳሚ ብዙ ገንዘብ ለማግኘት ነው።

መ. የእግዚአብሔር ስም አላህም የአብርሃም አምላክ ስም አይደለም። እግዚአብሔርንም አላህ ያለው ከእሱ በፊት በነበረ ከጣዖታቱ ስም በአንዱ ነው። የጣዖትን ስም ለአምላክ አብሃም መስጠትም እወነተኛ ውን አምላክ መሳደብ ነው።

ሠ. መሐመድ በሐሰት ተሳዳቢ ነው ፤እስራኤልንና ክርሲቲያንን ከሐዲዎች ናቸው ይላል።

ረ. ወንጌልንና ኦሪትን ከዶ፤በአዋልድ፤በአፈ ታሪክ፤በመጽሐፈ ባልቴት ያለውን ሰብስቦ ከሰማይ ወረደልኝ እያለ ብዙ የዋሃንን አታሏል።

ሰ. በወንጌል እንደተነገረው ርግጠኛው ሐሳዊ መሲሕ እሱ ነው፤በስሙ ባይጠራም በግብሩ ፍጹም እሱ ነው።

ተ. ቀማኛ ሌባ ወምበዴ ነው፤ ገንዘብ ከቸገረው ጦሩን አስከትቶ ጎረቤቱን ይዘርፋል፤ገንዘብ ካላት ባሏን አስገድሎ ምሽቱን ያገባል። ገንዘብ ካለው ባለቤቱን አስገድሎ እኔን ስላልተከተለነው እያለ የሐሰት ምክንያት ሰጥቶ ንብረቱን ይቀማል፤ሀብቱን ይወርሳል፤ምሽቱን ያገባል፤ለዚህም አላህ አዝዞኝ ብሎ ይዋሻል። በዩፋ ይህን ሲያደርግ ኑሯል፤የድብቁንማ የሌብነቱንማ! ማን ተናገሮ? ስንቱስ ተቆጥሮ! ማንስ ዐውቆ?

በ. <u>አረመኔ፣ጨካኝ፣ምሕረት የለሽ ነው</u>
መጀመሪያ ቃሉ አረመኔ እንደሚያሳየው ያልተጠመቀ የካዕባ ጥቁር ድንጊያ ጣዖት አምላኪ እንጂ የአምላክ አብርሃም፣የአምላክ ሙሴ፣የሕግ አሪት፣ወይም የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ አይደለም። አሪትን ወይንም ወንጌልን ያልተከተለ ሁሉ በቋንቋው መሠረት ፍጹም አረሚ ነው። በምሳሌያዊ አነጋገር ደግሞ፣ከአራት ዓመት ሕፃን እንሥቶ እስከ መቶ ዓመት ዕድሜ ያለ የጃጀ ሽማግሌ የሚያስጨፈጭፍ እጅ የለሽ አረመኔ በዓለም ላይ እንደ መሐመድ አልተፈጠረም።

ተ. <u>አድላዊ፣ወገናዊ ነው፣</u>
አድልዊንና ወገናዊነትን መሐመድ ጀመራቸው ባይባልም እስከ ፍጻሜ ያደረሳቸው መሐመድ ነው፤መሬት፣ገንዘብ ጥቅም ካገኘ ማንንም ጎረቤት ይወራል፣ይጣላል፣ዘመድ ከሆነና ባለመወረሩ የበለጠ ጥቅም የሚሰጥ መስሎ ከታየው ይምራል። በዚህ መሠረት ነው፣ዘመዶቹንና ወገኖቹን የመካን ሰዎች የማራቸው።

ቸ.<u>አመንዝራ ፣ሴሰኛ ነው፣</u>
ልዑል እግዚአብሔር ጠቢቡ በጥንተ ተፈጥሮ ለወንድ ካንድ በላይ ሴት ያስፈልገዋል ቢል ኖሮ፣የፍላጎቱን ያህል ሰባት፣ስምንት ሴት ይፈጥርለት ነበር፣ለሰው ብዙ ሴት ማግባትም የሚያስፈልገው በመጀመሪያ ዓለም ባልሞላበት ጊዜ እንጂ አሁን ዓለም በተጣበበት ለወሊድ መቆጣጠሪያ ባስፈለገበት፣ በመሐመድ ዘመን አይደለም። ሴትንና ወንድን በፍትወት እኩል አድርጎ መፍጠሩ ከታወቀ ብሽክ የሚቆጠሩ ዘመናት አልፈዋል። ሰው እንስሳ አይደለም፣ወሲብን ለዘር ብቻ የሚፈልግ፤ወሲብ ለሰው ከምግብና ከመጠላያ ቀጥሎ በእየጊዜው የሚያስፈልግ ፈቃድ ነው። እሱም አንድ ወንድ ላንድ ሴት ተብሎ በሙሴና በክርስቶስ መጻሕፍት ከተደነገገ ዘመናት አልፈዋል። ከዚህ ውጭ የሚኖሩ ሕገ ወጦችና አሕዛብ ናቸው። መሐመድም ይህን ያመጣው፣በአከባቢው ከነበሩት ጣዖት አምላኪዎች ዐረባውያንና ወላጆ ካላሳደገው ከራሱ ልቅና ስድ አስተዳደግ ነው።
ከዕቁባቶች ሌላ 13 ምሽት ነበሩት። ለሌላው ሲያዝዝ እኩል ካየሀ ካላደላሀ እኩል ካስተዳደርሀ ሦስትም አራትም ልታገባ ፈቅደንልሃል ይላል፤ራሱ ግን ቁጥር የለሽ ሴት ነበረው፤እነዚህንም የሚገናኘው በዘፈቀደ እንጂ ሌላው እንደ ታዘዘ በተራ አይደለም። ሴቶችም፣ውሽሞቹ ተሰብስበው ለምን በተራ አትመጣልንም ሲሉት፣አላህን አስፈቅጄለሁ፣ከምወዳት ከኢሻ ጋራ እተኛለሁ ብሎ ይመልስላቸዋል፤መልሶላቸዋል። ይህን የሚያደርግ ከካኑ ሊሀያን ነገድ በመካ በካዕባ ቤተ መቅደስ ከነበረው ጣዖት ሥርዓት እንጂ ከአምላክ አብርሃም፣ይስሐቅ ያዕቆብ የመጣ፣ክርስቶስ ያጸደቀውም አይደለም።

ከዚህ ላይ በዐሥርቱ ቃላት በአራት አታመንዝር፤በወንጌል ደግሞ በክርስቶስ "እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለያይ"ብሎ ጋብቻን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው የተሰሳተ? ወይስ በአመንዝረ ቁጥ ር አላህን ጠይቄ አስፈቅጄለሁእያለ፤ሴትን የወንድ ተናጋሪ እንስሳ፤አ ሚዎች ክብት አድጎ ያለፈ መሐመድ ነው? በዚህ ጊዜስ በዘመናችን ያለው አክራሪ ሰላም እግዚአብሔር እንጂ መሐመድማ እንዴት! ይልና መጻሕፍትና ሌሎች ሰዎች ናቸው የዋኹ የተበላኹ ይለናል፡ እንጂ፤መሐመድማ እንዴት ሁኖ ይሳሳታል?እግዚአብሔር ያነጋገራቸ ው እነሙሴ፤ተከታዮቹ ነቢያትም፤ቃለ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶ ስ ራሱም ተሳስቷል፤ያልተናገረውን ተናግሯል ተብሏል፤የተናገረውን ና የሠራውንም ተክዷል፤ይካዳል።

ምን የሁን ፖለቲካ አይደል? የማይሠራ ነገር የለ።ይህን ሊረዳ የሚችል በእየዘመኑ የሚሠራውን የሚከታተል ንቁህ፤ትጉህ፤አስተዋይ አንባቢ ነው።

ስለ መሐመድ አመንዝራነት፤ሴሰኛነት አረመኔነት፤ጨካኝነት ውሸታም ነት ብዙ እየጠቀሱ መናገር ይቻላል፤ግን ብራና ውድ ስለሆነ፤እስከዚህ የሰጠነው ይብቃንና ሌላውን ——— ደግሞ እንይ።

**ጎ. አጉሪ ነው፤ባሪያ ይጥለዋል፤**

አጉሪ መንፈስ ርኩስ፤ዛር ወይም ጎኔን የሚገዛው የሚያስገብረው ከዚያም አልፎ ተርፎ ባሪያ የሚጥለው እንዴት የእግዚአብሔር አገል ጋይ ሊሆን ይችላል? ሲያጎራ ደም ያስፈልገዋል፤በዚህ ጊዜም ለመንፈ ስ ርኩስ ስለሚሠዋ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ወደ አምልኮ ባዕድ መሄዱ ነው። "አንድ ሰው ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ ማገልገል አይች ልም ስላለ፤መሐመድም የጂኒ እንጂ የአምላክ አገልጋይ ሊሆን አይችል ም። አምላክ ከሰይጣን ጋራ ማኅደር አይካፈልም፤

**ነ. በዐሥርቱ ቃላት ሁሉ ኀጢአት ሠርቷል፤**

ጅብሪል ነኝ እያለ በሚመራው መንፈስ ርኩስ መሠረት ዐሥርቱ ቃላትን በሙሉ እየፈለገ ኀጢአት ሠርቶባቸዋል።

1. ከኔ በቀር ሌላ አምላክ አይኑርህ ብሎ ያዘዘውን ሽሮ፤ስሙንም የጣዖት ስም ሰጥቶ ስግደቱንም ለካዕባ ጣዖት ሰጥቷል።

2. የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም ም በከንቱ አትጥራ ያለውን በጣዖት ስም ተክቶ የሐሰት መመሚያ አድርጓል።

3. የሰንበትን ቀን ለውጧል፤ሽሯል፤ አፍርሷል።

4. አባትህንና እናትህን አክብር የሚለውን ጥሶ የእንጀራ እናቱን አሳዳጊውን ነክሷል፤ ደብድቧል። በልጅነቱ የሞቱ እናትና አባቱም ቆይተው ቢሆን ኑሮ ይህ ዕድል አያጣቸውም ነበር።

5. <u>አትግደል፤</u> ሰው ከመጨፍጨፍ በቀር ምን ሥራ ነበረው፤ያውም ሕፃናትና ሽማግሌ፤የጃጁ።
6. <u>አታመንዝር፤</u>ለዚህማ አለሌው እሱ እንደሆነ ከላይ አይተናል መረጃም አያስፈልገው።
7. <u>አትስረቅ፤</u> ለዚህም መሪው ከሠራዊቱ እሱ ነው።
8. <u>በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፤</u>ከመመስከርም አልፎ ሰውም ግደሉ፤ዋሹ ብሎ አስተምሯል፤ ያስተምራል።
9. "የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤የባልንጀራህን ምሽት፤ሎሌውንም ገረዱንም፤በሬውንም፤አህያውንም፤ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማንኛ ቸውንም አትመኝ።" ከዚህ ትእዛዝሳ መሐመድ ያልሠራው የትኛው ነው? መሐመድ የእነዚህ ሁሉ ደምሳሽ የጂኒ ተመሪ ወይም ተገዥ እንደሆነ ለመረዳት አስተዋይ አንባቢ የመሐመድን ታሪክ እንደገና እንዲያነብ ይጠቆማል። አክራሪ ስላምም ታሪኩን አስት አይልም፤ለም ን ተናገርህ? እንዴት ምስጢር አወጣህ? ብሎ ገድዬ ዐርፋለሁ ይላል እንጂ።
10. <u>ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ፤</u>ለዚህም የመሐመድ ነገር መቼም ከእግዚአብሔር ጋራ እልክ ተያይዞ፤ጎን ለጎን፤የጎሪ ጥ እያየ ማጥፋት ነውና፤ባልንጀሮቹን እየገደለና እያስገደለ፤ምሽቶቻቸውን ሲያገባ፤ሀብታቸውን ሲወርስ፤ከብታቸውን፤ሲዘርፍ፤ጥሪታቸውን ሲቀማ ነው የኖረው።
ኧረ! መሐመድ እንዲህ ከሆነ ለምን ብዙ ስላሞች ቅዱስ ይሉታል፤ለም ግባር ለሰው ልጅ ሁሉ አርያ ነው እያሉ ያመስግኑታል?ለሚል ጠያቂ መልሱ ምን ይሆን? የግብር መሪያቸው፤የሃይማኖት አለቃቸው ነው፤ፍ ጡር ሁሉ በሥጋ ዘመዱን፤በግብር መስሉን፤በዕድሜ እኩያውን በጠባ ዕይ ጓደኛውን ይወዳል። እንኳንስ ቀድሞ እና አሁንም የመሐመድ ልጆች አክራሪ ስላሞች በሃይማኖት አስመስለው መንግሥት ለመገልበ ጥ፤መሣርያ የሌላውን መንገደኛ፤ቱሪስት፤ደጋፊ የሌለውን ሽማግሌ፤ ኃይል የሌላቸውን ሕፃናት፤ነፍስ ጡሮችን ሴቶች፤በገዳም ያሉ መነኮሳት ን፤በበረሃ የወደቁ ባሕታውያንን ከፖለቲካ ግንኙነት የሌላቸውን ካህናት፤ጳጳሳት ያለምንም ርኅራኄ ያርዱሉ፤ይጨፈጭፋሉ፤በዚህ አረመኔ ሥራቸውም ይኮሩበታል፤ይፈክሩበታል። ይህንም በእየዕለቱ በመገናኛ ብዙኃን የምናነበውና የምንሰማው ነው።
መሐመዳውይንማ የግብር መሪያቸውን ለማንገሥ በቁርአን ያልተባ ለውን፤በቅዱሳት መጻሕፍት ያልተነገረውን፤ቤተ እስራኤልና ቤተ ክርስቲያን፤የማይቀበሉትን የማያውቁትን ዐውቀውም የማይቀበሉበትን

አዋልድ፣መጽሐፈ ባልቴት፣አፈ ታሪክ ሁሉ ሰብስበው፣ከራሳቸው ቧልታ እየፈጠሩ፣ከኪሳቸው ተረት እየመዘዙ፣ከነቢያት ሁሉ ይበልጣል ዓለም የተፈጠረችውም ለመሐመድ ሲባል ነው ይላሉ። እንዲህ ያለ በየሃይማኖቱ ድርጅት አካባቢ ባይኖር ኑሮ እንዴት በደነቀ ነበር። በውሸትና በተረት መጠራቀሚያ በቁርአን እንኳ በሌለ ማንም በፈጠ ረው አፈ ታሪክ ከሁሉ በላይ ሁኗል፤ጻድቃን ሰማዕታትን፣ ነቢያትን ሁሉ አልፎ ክርስቶስን እንኳ ሳይቀር፣ከአላህ ዙፋን ፊት፣ዙፋን ተዘርግቶለት ተቀምጧል ይላሉ። እንዲህ ያለውን ነገር ከልብ ወለድ ፈጠራ በቀር ማን አየ? ይህ ቢሆን ኑሮማ ከታላላቁ ነቢያት አንዱ እንኳ ሳይናገርለት ባልቀረም ነበር። የፖለቲካ መሪው የውሼት አባት፣የሐሰት ፈጣሪ መሐመድም በቁርአን ያበነካው ነበር። ምን ይሁን? አንድ መረጃ ሳይዙ ምን አውርተን እንከበር በሚሉ የሐሰት ሰባኪያን በእየሀገሩ በሚነዙት ውሸት ዓለም ሲበጠበጥ እንደሚኖር የሚያስረዳው እንዲህ እንዲህ ያለው የልብ ወለድ ፈጠራ ነው። በዚህም ከአላህ ባለሟሎች ሁሉ በለይ ያለው ዒሳ ነው ያለውን የቁርአንንም ቃል ይጥሳሉ፣በዚህም የመሐመድ ተረቶች ደግሞ ከመሐመድ በኋላ የተነሡ ነቢያት ይሆናሉ። እናም መጨረሻው ነቢይ መሐመድ ነው የሚለውን የራሳቸውን ፈጠራ ይንዳሉ።(ሱራህ:11:253፤ 87፤)በእየዘመኑ በሃይማኖት ሽፋን መከላከያ የሌላቸውን ሕፃናት፣ሴቶ ች፣አረጋውያን ሽማግሎች መንገደኞች የሚጨፈጭፉ አክራሪ ስላሞች በቁጥራቸውና በግብራቸው የዚያው የአረማዊው መሐመድ ልጆችና ተከታዮች ናቸው። አክራሪዎች ስላሞች፣የመሐመድ ተከታዮች በቅዱስ ወራቸው በሮመዳን እንጾማለን ያላሉ፤ግን የነቢያቸውን መሪነት ለመፈጸም መሣሪያ የሌለው ሰው ካገኙ እየዞሩ ይጨፈጭፋሉ። በልምና የሚያገለግለው ለጦርነትና ለዘረፋ፣መንግሥትን ገልብጦ ሥልጣን ለመያዝ፤ሀገር ለመውረር፣ርቱዕ (እውነተኛ) ሃይማኖትን ለማጥፋት ነውና።

እነ ዲዳት ክርስቶስንና መሐመድን አነጻጽረው መሐመድን ለማስበለጥ ሞክረዋል፣ከነቢያት ሁሉም በላይ አድርገውታል። በጥናት ሲነጻጸሩ ግን ውጤት የሚከተለው ነው፤

ወልደ እግዚአብሔር ሕያው፣ወልደ ማርያም ሥግው፣ፈጣሪ ዓለማት ኢየሱስ ክርስቶስ፣አምላክ፣ወልደ አምላክ ሲሆን በትሕትና፣በንጽሕና ከድንግል ማርያም ፍጹም ሥጋ ለብሶ፣በፍጹመ ትስብእቱ በዚህ ዓለም 33 ዓመት ከሦስት ወር እንደ ሰው ተመላልሶ፣በፈለገ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆ፣በአይሁድ ተሰቅሎ፣ ሙቶ ተነሥቶ ጽድቅንና ትንቢትን ሁሉ ፈጽሞ በተነሣ በአርባ ቀኑ ዐርጎ በአባቱ ቀኝ በክብር ተቀምጧል። ይህን ሁሉም ሲያደርግ ለመለኮታዊ በሕርዩ ንጢአት ስለማይስማማው ያላንዳች ኀጢአት በደል ወይም አበሳ ነው። በዚህ አንጻር መሐመድ ደግሞ ኀጢአት የት አለሽ? እያለ እየጠራ ሲሠራ ኑሮ ያስነራው ወደ ነበረ መንፈስ አልፏል።

## ምዕራፍ 16፣

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለመሐመድ

በምዕራፍ 9 እንዳየነው እነ አሕመድ ዲዳት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሐመድ ተናግሯል ይላሉ፣ስለ መንፈስ ቅዱስ የተናገረውን እጣመ ው፣ስለ መሐመድ የተናገረውን ደግሞ ሸፍነው፣መሐመድን ትንቢት የተነገረለት ነቢይ ለማስመሰል ብዙ ቀባጥረዋል። አዎ! እነሱ እንደሚ ሉት አይደለም እንጂ በእሉታ መልኩ ጌታም ስሙን ሳይጠራ፣ሐሳዊ መስሕ ፣እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ ብሎ በስፊው ተናግሯል:(ማቴ.24: 21-30፤ማር.13: 5-21፤ሉቃ.21: 7-19)

ስለ መንፈስ ቅዱስ የተናገረውንም ስለመሐመድ ነው ብለው ዐይናቸውን አፍጠው ድርቅ ይላሉ፤ምን ይሁን? የሌባ ዐይነ ደረቅ ተመልሶ ልብ ያደርቅ ይሉሃል ይህ ነው። ለሁሉም ራሱ አንባቢው እንዲፈርድ ጥቅሱን በሙሉ ከዚህ ቀጥለን ጽፈናል፤

1. (ሉቃ.24: 44-49) "እርሱም ከእናንተ ጋራ ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት መዝሙራትም ስለኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤እንዲህም አላቸው፣ክር ስቶስ መከራን ይቀበላል፣በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፤በስሙ ም ንስሓና የኀጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ለአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል። ተብሎ እንዲሁ ተጽፏል፣እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ። እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤እናንተ ግን ከላይ ኀይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ" ብሎ አዝዘዋቸ ው ዐረገ። (ግብሐ.1: 4-8)

በትእዛዙ መሠረት ተስፋውን እየጠበቁ በኢየሩሳሌም ከተማ እንድነት ሁነው ሲጠብቁ፣በተነሣ በ40ኛው በዐረገ በ10ኛው ቀን እንድነት ሁነው እብረው ሳሉ፤"ድንገት እንደ ሚነጥቅ ዐውሎ ነፍስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፣የነበሩበትን ቤትም ሞላው እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳናት ታዩአቸው፣በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸ ው፤በሁሉም መንፈስ ሞላባቸው፤መንፈስ ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በልዩ ልዩ ልሳናት ይናገሩ ጀመር።————።

ከዚህ በላይ ያሉት ጥቅሶች እንደሚናገሩት የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ የተፈጸመው ጌታ ባረገ በ10ኛው ቀን ነው። ለመሐመድ ነው ከተባለ ግን እስከ 600 ዘመን ድረስ ሐዋርያት ሳያስተምሩም፣ክርስቶስን ሳይሰበኩም ሳይሞቱም ኑረው የመሐመድ ሰባኪዮች ሁነዋል ማለትና፣ ለ600 ዘመንም በዓለም የተስፋፋው ክርስትና አልነበረም ማለት ነው። ግራ ቀኙን አስተውሎ የማያነብ ሰው በአንዳዐይናነቱ ሰውን ገደል ይዞ ይገባል። ሁለተኛው ደግሞ በቅዱስ በርናባስ? ወንጌል በሆላንድ

በ1709:ዓ.ም ተገኘ በሚሉት የውሸት መጽሐፍ ላይ የተመሠረት ውሸት ነው። በዓለም አብያተ ክርስቲያን የሥነ ጽሑፍ ታሪክ እንዲህ ያለ እንኳንስ ወንጌልና አዋልድና መጽሐፈ ባልቲትም የለ። እነ አሕመድ ዲዳት ትልቁ ወንጌል ይሉታል። ምን ይሁን ውሸታም የሚያመሰግን ጎደኛውን ውሸታምን አይደል? የበርናበስ ወንጌል ከ1709 ዓ.ም በፊት በየትም አገር ቅጂው ታይቶም አይታወቅ። ታዲያ ከምን መጣ? ለስላም ሁሉም ቀላል ነው፣እንደ ቁርአን ጅብሪል በሚባለው ጂኒ አማካይነት ከሰማይ ወርዶ ይሆናላ! የተጻፈውም በክርስቶስ አካባቢ በነበሩት፣ ዕብራይስጥ፣ ዐረማይስጥ፣ ግሪክ፣ ላቲን ሳይሆን በዘመናዊው ቋንቋ በኢጣልያን ነው። ዋሽ ቢሉኝ እዋሻለሁ ነፍስ በወጥመድ እይዛለሁ ይሉሃል ይህ ነው። የስላም ነገር በክርስቶስ በዘመኑ በቋንቋው የተጻፉትን ወንጌላት ይክዳል፣ከ1700 ዘመን በኋላ በሀገሩ በኢየሩሳሌም ሳይሆን፣በሆላንድ፣በቋንቋው ሳይሆን በኢጣልያን የተጻፈ ወሸት ያምናል። አምኖም ያስተምራል፣ይሰብካል።
ታላቁ የእነ ሂትለር ቀዳሚ፣የኔሮንና የጅስካን ተከታይ፣የእስልምና መሥራች በግብሩ ከላይ ያየነው በወንጌል የተነገረው መሐመድ ይህ ነው።ተከተለው ውቃቢው መልአከ ዓለም በምድር ያከብርሃል፣ያበለጽግሃል፤ጽድቅ፣ድኅነት መንግሥተ ሰማያት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው የሚገኙት።

# ምዕራፍ 17፣

## አዲስ ሕግ አላወጣም ብሏል፣

(አያ አሕመድ ዲዳት፣መጽሐፍ ቅዱስ ስለመሐመድ ገጽ:10) በክፍሉ እንደ ተገለጠው ሐዲስ ሕግና ትምህርት ከፖለቲካ በቀር ያላመጣ መሐመድ እንጂ፣ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለም። ትምህርቱንም ሕጉንም ከዚህ ቀጥለን እንዘረዝራለን፤

ሀ. በአራት በደንብ ያልተብራራውን ምስጢረ ሥላሴን (የሥላሴን በመለኮትአንድነት፣በአካል፣በስም፣በግብር ሦስትነት(ማቴ.28:1-20)እን ግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው ብሎ ሦስትነቱንም አንድነቱንም ገልጧል። ይህን ትምህርት በሰፊው ለመረዳትና ለማጥናት ሁለቱን መጻሕፍቱን ሁሉም ሁሉን ይወቅንና አንድ እረኛ አንድ መንጋን ያነቧል።

ለ. ለሥርዓትና ለምግባርም (ማቴ.5-3—— 48፤)በዚያ ዘመን በሮምና በግሪክ ፍልስፍና በጸሐፍትና ፈሪሳውያን ሥርዓት ትልቅ የሚባለው ሀብታም፣ባለጸጋ፣ድል አድራጊ ኀይለኛ ነበር። በዚያ ዘመን ነው ይህን ያስተማረ፤ሴትን ከወንድ እኩል ያአደረገ፤ሕፃናትን ከዐዋቂ እኩል የቆጠረ። አያ ዲዳት ለዚህ ሁሉ የሚከተለውን ልብ አድርገህ አንብ፤

3. በመንፈስ ድኆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፣መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።

4. የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፣ይጽናናሉና።

5. የዋሆች ብፁዓን ናቸው፣ምድርን ይወርሳሉና።

6. ስለጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፣ይጠግባሉና።

7. የሚራሩ (የሚምሩ)ብፁዓን ናቸው፣ይማራሉና።

8. ልብ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፣እግዚአብሔርን ያዩታልና።

9. የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው፣የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።

10. ስለጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው መንግሥተ ሰማያት የእነሱ ናትና።

11. ሲነቀፉዋችሁና ሲያሳድዷችሁ በእኔም ምክንያት በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ፣ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ ሐሴትም አድርጉ፣ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳደዋቸዋልና።

ሐ. ከዐሠርቱ ቃላትም ብዙዎቹን አጥብቋል፤

1. ጠላትህን ጥላ ወንድምህን ውደድ የምትለውን የኦሪት ትእዛዝ እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ ብሎ ለውጧል (5: 43)

2. አትግደልን በአታስቀጣ (5 :21)
3. አታመንዝርን ሴትን በፍትወት ባያት አመነዘረ ብሎ(5: 27- 28)
4. ምሽቱን የፈታ ሁሉ የፍች ወረቀት ይስጣት የሚለውን ከማመንዘር በቀር ምሽቱን የፈታ ሁሉ አመነዘረ ብሎ (5:31)
5. እስከ ዘመናችን ድረስ በመሐመድ መሪነት በእስላሙ ዓለም ዛሬም እንደሚደረገው ሁሉ ቤት ለወንድ የምትናገር ከብቱ ናት፣ከዚያም ቢያልፍ እንድ ሦስተኛው (ሱራህ 4:11) የነበረችውን አንችም የወንድ እኩያ ነሽ ብሎ ከባርነት አውጥቶ፣ከዝቅተኛነት አንሥቶ የወንድ እኩያ አድርጓታል። እንደ ገና ሙሴና መሐመድ አይመሳሰሉም የሚለውን ምዕራፍ 11ን ያንቧል ለደግ ሥራም፣ለምግባርም ሰድስቱ ቃላተ ወንጌልን ሰጥቷል (ማቴ.25:34-46) በዚህም ከላይ ተጠቀሰው በዘመኑ የነበረውን የሮሞች የግሪክ ልማደ ኅብረተ ስብእና የጸሐፍት ፈሪሳውያንን ግብዝነት ጠራርጎ ጥሏል።
7. የጾም የጸሎት የምጽዋትም ሕግ እንደ ጸሐፍትና ፈርሳውያን እንደ እስላም በዐዋጅ በነጋሪት በአደባባይ ለይስሙላ ሳይሆን የተሸሸገውን ለሚያየው አምላክህ በስውር ስጥ፣ጹም፣ጸልይ ብሎ አዘዟል። ለዚህም ማቴ.ምዕራፍ ስድስትን በሙላ ያንቧል።
8. ዲዳት አሁንም ሳይገባው ለሰን¯በት ቀንም ክብር ሰጥቷል ብሏል፣እንደ ሰባተኛው ቀን አደበንቲስት፤ጌታ የትምርቱን ዘመን ያሳለፈው ሰንበተ አይሁድን እየሻረ ነው። ለዚህም እንድ እረኛ፣አንድ መንጋ ምዕራፍ 23ን በጥንቃቄ ያንቧል።
9. መሥዋዕት አሪትን ሽሮ መሥዋዕተ ወንጌልን ተክቷል። በደመ እንሰሳ የነበረውን በራሱ መሥዋዕትነት ተክቷል።
10. እሱን ያመነ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሆን ሥልጣን ሰጥቷል፤(ዮሐ.1:11-13) የርሱ ወደ ሆኑት መጣ፣የገዛ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም፣ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣በስሙ ለሚያምኑት፣ለእነርሱም የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው ፤እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ከሥጋ ፈቃድ አልተወለዱም።
11. ለአገልጋዮች ሐዋርያት፣ካህናት፣ቀሳውስት የኃጢአት ማስተሰረይ ሥልጣንን ሰጠ:(21-23)ኢየሱስም ዳግመኛ ሰላም ለእናንተ ይሁን፣አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው። ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፣ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችሁላቸውይቀርላቸዋል፤ይቅር ያላላችሁላቸው ይቅር አይባልላቸውም። (ዮሐ.20: 20-23)
12. ተገፎ ፣ተገፎ፣ተሰቅሎ፣ሙቶ፣ተነሥቶ ከዐርባ ቀን በኋላ ብዙ ሰው እያየው ዐርጎ በአባቱ ቀኝ ተቀምጧል።

ታዲያስ አያ ዲዳት ይህ ሁሉ አዲስ፣አስገራሚ፣አስደናቂ አይደለም ወይ? ልባይ አንባቢ ይፍረደው።
ከማሳትና ከክሕደት በቀር አዲስ ነገር የለለ በሚቀጥለው እንደምናየው በቁርአን እንጂ በወንጌል አይደለም።ወንጌልም ሐዲስ፣(መጻሕፍተ ሐዲሳት) የተባለችው ብዙ ነገር ከብሉይ ከኦሪት፣ከነቢያት የተለየ ስለሆነ ነው ክርስቶስ ያመጣውን ሐዲስ ሕግ ሁሉ ገልብጦ፣ዓለምን እንደ ገና ከአብርሃም በፊት ወደ ነበረው የአረሚ ዘመን የመለሰ፣ለደንጊያ ያውም ለጥቁር ስገዱ ያለ፣ሴትን ከወንድ ያሳነሰ፣የምግባርን ትልቅነት ወደ አረመኔነት የመለሰ መሐመድ ነው እንጂ ክርስቶስ እማ! የሠራው ሁሉ ሐዲስ ነው።

## ምዕራፍ:18፤

### በቁርአን አዲስ ነገር የለም፤

በቁርአን ውስጥ ያሉት አዕራረ ክርስቲያን ሁሉ በክርስቶስ ልደት አካባቢ ተነሥተው እስከ 4ኛው መቶ ዘመን ድረስ ቤተ ክርስቲያንን ሲያጨቃጭቁ ኑረው በ1ኛው ያለም ጉባኤ በ325 ዓ.ም በኒቅያ የተወሰኑና የተወገዙ ናቸው።የእነዚህ ኑፋቄዎች መሪዎችም ስባልዮስ፤አረዮስ፤ ሊው ማርክዮን (በነጠላ) በጥቅል ደግሞ ደኪስታውያን ግኖስቲስት ይባላሉ። በሰፊው ለማጥናት አንድ አረኛ አንድ መንጋ ምዕራፍ 26:7.170 ላይ ስድስትን ይመለከቷል።

አምላክ በአካሉ አንድ ነው ለማለት ስባልዮስና አርዮስ ፍርጥርጥ አድረገው አስተምረዋል፤ከመሐመድ የሚለዩት ጦርነት ባለ መከፈታቸውና ሃይማኖትን መሣሪያ አድርገው በሃይማኖት ሽፋን፤በጅሃድ ዐዋጅ ጦርነት ከፍተው ያልተከተሏቸውን አለመውረራቸው ነው።

<u>የቁርአን ብዙ ተረቶች የመጡት፤</u>

ሀ. ብዙ ተረት ጸሐፊዎች በወንጌል ስም ከጻፏቸው ዐሥራ ስድት የተረት መጻሕፍት፤ቤተ ክርሲቲያን ሐሰተኛ ናቸው ብላ ካገለለቻቸው፤

ለ. ሊቃውንቱ ለሃይማኖት ማብራሪያ ሲጽፉ፤የሚፈልጉትን ሐሳብ ለማስገባት ጎን ጎናቸውን ከሚጽፉ፤ ሁለቱም አዋልድ ይባላሉ። እነዚህም በመካከለኛው ምሥራቅ እየተጻፉ ይበተኑ የነበሩ ናቸው። ዛሬም በግሪክ፤በሮም፤በግብጽ በኢትዮጵያ ገዳማት ይኖራሉ አሉ፤በቀሩት የተረት መጽሐፍ መሆናቸው ታውቆ ከቤተ መጻሕፍት ተቀምጠዋል እንጂ ላገልግሎት አይውሉም፤በኢትዮጵያ ግን አሁንም ከኪዳን በፊት ለአገልግሎት የሚነበቡ ከእነሱ አሉ። ቁርአን ከሰማይ ወረደሁ ካለ ከእሱ በፊት የነበሩት ኑፋቄዎችና ክሕደቶች ሁሉ ከሰማይ መውረዳቸውን ማስረዳት አለበት።

ሐ. ታልሙድና የክርስቲያን ትውፊት (በዐረቢያ የነበረው)

1. ሰላም ሁሉ የሆነለት በአካል ሂዶ ያልሆነለት ፊቱን አዙሮ የሚሰግደላት ጥቁር ደንጊያ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ60 ዓ.ም ለአካባቢው የአምልኮት ቦታ እንዲሆን የሮም ጀኔራል የወሰነው ነው። መሐመድም ሌሎችን ጣዓታት ሲያጠፋ ይህችን ጥቁር ደንጊያ ቢያጠፋ ኑሬ ለአምላክ በመንፈስ ስገዱ ማለቱ ነበር። ግን የፓለቲካ መሪ እንጂ የእውነተኛ ሃይማኖት መሪ ስላልሆነ፤የጣዖታትን ወኪል ጥቁር ደንጊያ ካዕባን አክብሮ አልፋል። (ዘፀ.20:3-4) ከኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ፤በሰማይም ሆነ በምድር ወይም ከምድር በታች ካለው ውኃ ውስጥ ከሚኖሩት ነገሮች የማንኛቸውንም ዐይነት ምስል፤ ጣዖት አድርገህ አትሥራ፤እኔ እግዚአብሔር አምላክህ እጅግ ቀናተኛ ስለሆንሁ ተቀርጾ የተሠራ ማንኛቸውንም ጣዖት አታምልክ። (ከዚህ ትእዛዝ በየትኛው ሾልካ አልፋ ነው ያች ትኩል ጥቁር ደንጊያ አምላክ

ሁና ሰላም ሁሉ የሚሰግድላት? መሐመድ የጦር ጀኔራል በስሆነ ሌሎችን በዐረብያ የነበሩትን ደካሞችን ጣዖታት ሲያጠፋ እሷን ለህልውናው ሲል ትቷታል።

2. <u>ሐጂ፤</u>ቃባን መሳለም፣ሳፋን ማርዋን መኅብኘት፣በዋዲ ሚና ደግሞ በቆመ ደንጊያ ላይ አንተ ሰይጣን እያሉ ደንጊያ መወርወር ከመሐመ ድ በፊት የነበረ አምልኮ ነው። አሁንም ይደረጋል። ልማደ ጣዖትን፣ አምልኮ ባዕድን ማጥፋቱ ከምን ላይ ነው፟? መሐመድ የሃይማኖት ነቢይ ቢሆን ኑሮ ጣዖታትን ማጥፋት ነበረበት።

3. <u>ጸሎት</u> ፣በዐረቢያ ደሴት አክል የነበሩት ሳባውያን፣ስልምና ያጠፋቸው በተወሰነ ሰዓት ሰባት ጊዜ በቀን ይጸልዩ ነበር፤መሐመድ ከእነዚህ ሁለቱን ቀንሶ አምስት ጊዜ በቀን ሠራ። ለሙታንም ሳባውያን ይጸልዩ ነበር፤ይህ ልማድ አሁንም አለ።

4. <u>ሮማደን፤</u> ሳባውያን ሠላሳ ቀን ጹመው ዒድን ያከበሩ ነበር። አዲሷ ጨረቃ የዒድ ለት በደንብ ያልታየች እንደሆነ ተብሎ ጾሙ ባአንድ ቀን ተራዘመ። ይህ ልማድ ወደ ስልምና ገብቶ አሁንም በደንብ ይከበራል። የጾማቸው መጀመሪያና መጨረሻ የመጣው ከአይሁድ ታልሙድ ነው። ጾም የሚጀምረው የሰው ዐይን ነጭና ጥቁር ገመድ መለየት ሲያቅተው ነው፤እንዲሁም ጾሙ የሚፈታው የሰው ዐይን ነጭና ጥቁር ገመድ ሲለይ ነው። ይህ ልማድ አሁንም በስልምና ገብቶ ይኖራል። እስከ አሁን ድረስ የዐረቡ ዓለም በዐይኑ እንጂ በሐሳብ ሠርቀ ወርኅ የጨረቃ (መባቻ) ማወቅ አልቻለምና። ዐውደ ወርኅን ወደ ዐውደ ፀሐይ ለውጦ መጠቀም አልቻለም። ጨረቃ የምትወለደው በ27 ሌሊት በ1:ሠርቀ ወርኅ ነው፤ ይህን እንኳ ማስተካከል ባለመቻላቸው፣ማታ ማታ እያንጋጠጡ ሰማይ እያዩ፣ደመ ና የሆነ እንደሆነና ጨረቃን ማየት ካልቻሉ፣እስከ ሦስት ቀን ይቆያሉ፤ ይህም ባይሆን ያለ ቀኑ ገደፍሁ ይሆን በሚል የሕሊና ወቀሳ ይሠቃያሉ። የጨረቃን አቆጣጠርም የተማሩት ከአይሁድ ነው። ይህንም በትሕትና ጠይቀው መማር አቅቷቸው ዘለዓለም ሲሳሳቱ ይኖራሉ። መሪያቸው መሐመድም አላስተካከለውም። ቁርአንን ያህል ትልቅ መጽሐፍ ከሰማይ ያወረደ አላህም የዘመን አቆጣጠርን አላስተካከለም። የሌላውን ቀጥተኛ ነገር እናርማለን ይላሉ፣የራሳቸውን ግን አያስተውሉም። ምክንያቱስ ቢሉ፣ቀጥ ያለ ነገር አይወዱማ! የረመዳን በዓል የሚገደፈው በ27 ሌሊት በአንድ ጨረቃ ነው። እነሱ ግን ጨረቃ ታየች አልታየችም እያሉ ሲደናበሩ ይኖራሉ። ሮመዳንን ለምን ትጾማላችሁ ሲሏቸውም ቁርአን ከሰማይ የወረደበት ወር ነው ይላሉ። ይህም ሦስት ውሸቶች ያዘለ ነው፤

አንደኛ ቁርአን የተሰጠው፣የተጠራቀመው በእየሱራሁ መግቢያ እንደተገለጠው በ22 ዓመት እንጂ በአንድ ወር ወይም ዕለትም አይደ ለም።
ሁለተኛ የሮመዳን ጾም ከመሐመድ በፊት የነበረ የሳባውያን ጾም እንጂ መሐመድ የጀመረውም አይደለም።
ሦስተኛ ራሱ መሐመድ ለፓለታካው እንዲመቸው በእየጊዜው የገጠ መውና ከእየገጣሚዎች የሰበሰበው እንጂ ቁርአን ከሰማይ የወረደ አንድም አንቀጽ የለውም።
ሮመዳን በዐይነቱና በይዘቱ ከጾመ ነቢያትና ሐዋርያት ይለያል። እነዚያ ከጥሉላት (ከእንስሳት ተዋፅኦ) ተለይተው ነበር የሚጾሙት ያውም በቀን፣የእስላሙ ሮመዳን ግን ቀን አይሁን እንጂ ሌሊት ቤትን ዘግቶ ለአፍ የሚጣፍጡ ጥሉላትን መኮምኮም ነው። የካዕባው ጣዖት እንደ ሆነ እንጂ አምላክ አብርሃምስ ሌሊትም ያያል፤ከማንነው የሚሸሸጉት? ቀን ምራቃቸውን ሲተፉ ውለው ማታ ጥሉላትን መኮምኮም ለአስተዋ ይ ሕሊና ያስቸግራል።
5. <u>ከታልሙድ የተወሰዱ ሐሳቦች</u>
ኢየሩሳሌምን በ70 ዓ.ም የሮም ጀኔራል ቲቶ በበዘበዛት ጊዜ ወደ ዐረቢያ የተሰደዱ ብዙ አይሁድ ነበሩ። ከእነዚህ ብዙዎቹ ከኦሪት ይልቅ በተረት፣በዘአንበሩ አበው (ትውፊት) የሚመሩ ነበሩ። በዚያን ጊዜ ብዙ አይሁድ ታልሙድ ለዐሠርቱ ቃላት ማብራሪያ ነው ብለው ያምኑ ነበር። መሐመድም ከታልሙድ ትውፊት ወደ ቁርአን ጨምሯል። ለምሳሌ፣የሚጸለየው ወደ ኢየሩሳሌም ተዙሮ ነበር፣በኋላ ግን መሐመድ ከአይሁድ ጋራ ስለተጣላ ወደ ዐረብ ጣዖት ወደ ካዕባ ተዙሮ እንዲጸለይ አዝዝዋል። (2ኛ ሱራሀ:1-49) ከየትም ከወጣሀበት ስፍራ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ አቅጣጫ አዙር ብሎ አዘዘ። (144) በዚህም ጌታ ለሰሎሞን በትእዛዝ ካሠራው ቤተ መቅደስ የአሕዛ ብ ጣዖት ካዕባ መብለጧ ነው። ፖለቲካ የማይሠራው የለም።
6. መሐመድ ስለ አብርሃም የሚያወቀው ሁሉ ከአይሁድ የተረት መጽሐፍ ሚድራሽ ራባህ ነው። አብርሃምም ጌታዬ ሆይ ሙታንን እንዴት እንደምታስነሣ አሳየኝ ባለ ጊዜ፣አላመንህምን? አለው፣አዎን አምናለሁ ግን ልቤ እንዲረጋ ነው አለ። አላህም አራት ወፎች ያዝና ቆራርጣቸው ከዚያም በእየኮረብታው ላይ ከእነሱ ቁርጥራጭ አድርግ ከዚያም ጥራቸው ፈጥነው ይመጣሉ። በዚህም አላህ አሸናፊ መሆኑን ዕወቅ አለው።
7. ስለ አብርሃም እምነት ሌላው ሱራሀ(6: 7-82) አብርሃምም ለአባቱ ለአዘር ጣዖታትን አማልእክት አድርገህ ትይዛለህ? እነሆ! እኔ ግን አንተም ሕዝቦችህም በግልጽ ስትሳሳቱ አያችኋለሁ ባለ ጊዜ፣አብርሃም

(እንዲያውቅ)ከአረጋጋጮችም ይሆን ዘንድ የሰማያትንና የምድርን መንግሥት አሳየነው። ሌሊቱም በእሱ ላይ በጨለመ ጊዜ ኮከብ አየ፤ይህ ጌታዬ ነው አለ፤በገባም ጊዜ መግባቱን አልወድም አለ። ጨረቃም ወጥታ ባየ ጊዜ ይህ ጌታዬ ነው አለ፣በገባችም ጊዜ፣ጌታዬ ባይመራኝ ከተሳሳቱት እሆናለሁ አለ። ፀሐይም ወጥታ ጮራዋን ዘርግታ ባየ ጊዜ፣ይህ በጣም ትልቅ ነው፣ ጌታዬ ነው አለ፣በገባችም ጊዜ እኔ ከምታጋሩት ሁሉ ንጹሕ ነኝ አለ። እኔ በዚያ ሰማያትንና ምድርን ለፈጠረው ቀጥተኛ ስሆን ፊቴን አዞርሁ፣እናም ከአጋሪዎች አይደለሁም (አለ) ወገኖቹም ተከራከሩት፤አላህ በርግጥ የመራኝ ሲሆን ትከራከሩኛ አላችሁን? በእርሱም የምታጋሩትን ነገር አልፈራም ግን ጌታዬ ነገርን ቢሻ (ያገኛል) ጌታዬም በነገሩ ሁሉ ዕውቀቱ ሰፋ፣አትገነዘቡምን አላቸው።:———::

8. ዳግመኛም ሌላው ሱራህ(19:41-49) በመጽሐፉ ውስጥ አብርሃምን አውሳ፣እሱ በጣም እውነተኛ ነቢይ ነበረና። ለአባቱ አባቴ ሆይ! ለማይሰማና ለማያይ፣አንተንም ለማይጠቅም ለምን ትገዛለህ? ባለ ጊዜ፣ አባቴ ሆይ! ለአንተ በዕውቀት ያልመጣልህ ነገር ለኔ መጥቶልኛልና ተከተለኝ፣ቀጥተኛውን መንገድ እመራለሁ። አባቴ ሆይ! ለሰይጣን አትገዛ፣ሰይጣን ያልረሕማን ዐመፀኛ ነውና። አባቴ ሆይ! የሰይጣን ጓደኛ ሁነህ የአልረሕማን ቅጣት እንዳያገኝህ እፈራለሁ አለው። (አባቱም) አብርሃም ሆይ! አንተ አምላኮቼን ትተህ የምትዞር ነህ? ባትመለስ በእርግጥ እወግርሃለሁ፣ለረዥም ጊዜም ተወኝ አለው። (አብርሃም)ደኅና ሁን፣ወደፊት ከጌታዬ ምሕረትን እለምንልሃለሁ፣እርሱ ለኔ በጣም ሩኅሩኅ ነውና አለው።:———:: እሱም ከአላህ ሌላ ከሚገዙት በራቀ ጊዜ ለእሱ ይሥሐቅንና ያዕቆብን ሰጠነው። ሁሉንም ነቢይ አደረግን።:———::

9. ስለ አብርሃም የተነገረው ሦስተኛው ሱራህ21:52-72 ደግሞ እንዲህ ይላል፤እንደ አሮጌና እንደ ጃጀ ሰው መደጋገም ይወዳል፣ስለ ዚህ ይህን ለመጨረሻ ጊዜ ስለዚህ ርእስ ገልብጠን፣የቀሩትን ሱራሆች ቁጥራቸውን ሰጥተን ወደ ሌላው መልሳችን እናመራለን።

ለአባቱና ለሕዝቦቹ ይህ የምትገዙለት ቅርጻ ቅርጽ ምንድን ነው? ባለ ጊዜ(መራነው)እነሱም አባቶቻችን ለእርሱ ተገዥዎች ሁነው አገኘናቸው አሉት። እናንተም አባቶቻችሁም በርግጥ በስሕተት ውስጥ ነበራችሁ አላቸው እነሱም በምርህ ነው? ወይንስ አንተም ከሚቀልዱት ነህ? አሉት። አይደለም ጌታችሁ የሰማይና የምድር ጌታ ያ የፈጠራችሁ ነው፤እኔም ከመስካሪዎቹ አንዱ ነኝ አለ። በአላህም እምናለሁ ዞረት ስትሄዱ በጣዖቶቻችሁ ተንኮል እሠራለሁ። እንዳለው ዘወር ሲሉም

አንድ ብቻ ሲቀር ሁሉንም ሰብርብር አደረጋቸው፣ይህም ታላቁ ጣዖት ነበር። ይህንም የተወው ወደ እሱ እንዲመለሱ ነው። (መሐመድም ከካዕባ ከትልቁ ጣዖት በቀር የቀሩትን ያረብያ ጣዖታት ሰባብሯል) እነሱም በአማልክቶቻን ይህን የሠራ ማነው? እርሱ በርግጥ ከበደለኞች ነው ተባባሉ። አበርሃም የሚባል መጥፎ ጎረምሳ ሲያነሳቸው ሰምተናል ተባባሉ። አብርሃም ሆይ! በአማልክቶቻችን ይህን የሠራህ አንተ ነህን? አሉት። አይደለሁም፣ይህን ያደረገው ይህ አለቃቸው ነው፤መናገር ይችሉ እንደሆነ ጠይቋቸው አለ።———። የሚከተሉት ስለ አብርሃም እምነት የተጠቀሱት ሱራህዎች እንዲሁ ዝብርቅርቃቸው የወጣ ነው፤ምክንያቱስ ቢሉ ምንጫቸው ዝብርቅርቁ የወጣ ተረት ነውና። (26:70-82፤29:16፤17፤37:83-89፤43:26-30፤ 60:4:)ይህና መሰሎቹ ሁሉ ከመሐመድ በፊት በመካከለኛው ምሥራቅ በእኛም በአዋልድ መጻሕፍት ተጽፎው ይገኛል።(መጽሐፈ ኩፋሌ 1:42-46) አብርሃምም አባቱ ታራን አባቴ! ብሎ ጠራው፣እሱም ልጄ ሆይ! እነሆኝ እኔ አለሁ አለው። እሱም ምንም ቃል ወይም እስትንፋስ የላቸውምና አንተ ከምታመልካቸውና በፊታቸው ከምትሰግድላቸው ከእነዚህ ከጣዖታቱ ለኛ የምናገኘው ምን ረድኤት፣ተድላ ደስታ አለን? ዲዳዎች ናቸውና፣ልቡናንም የሚያስቱ ናቸውና አታምልኳቸው ሰማይን የፈጠረ፣በምድር ላይ ዝናም ለዘር፣ጠል ለመከር የሚሰጥ፣በ ምድር ላይ ሁሉን የሚያደርግ፣ሁሉን በቃሉ የፈጠረ፣ከፊቱ የሰው ሁሉ ደኅንነት የሚገኝ እግዚአብሔርን አምልኩ። ቃል፣ እስትንፋስ የሌላቸው ጣዖታትን እናንተ ለምን ታመልካላችሁ? እነሱ የሰው ሥራ ናቸውና፣እናንተ በጫንቃችሁ ትሸከሙአቸዋለችሁና፣ለሚሠሩአቸው ሰዎች ጽኑ ተዋርዶ ናቸው እንጂ ከነእርሱ ረድኤት አይገኝምና ለሚያመልኳቸውም ሰዎች የልቡና ስሕተት ናቸውና አታምልኳቸው አለ።

አባቱም ልጄ ሆይ! እኔም አውቃለሁ፣ነገር ግን በፊታቸው አገለግል ዘንድ ካህነ ጣዖት ላደረጉኝ ለሕዝቡ ምን አደርጋለሁ? እውነት ነገርንም ብነግራቸው ያመልኳቸው፣ያመሰግኗቸው ዘንድ ልቡናቸው እነሱን ተከትሏልና ይገድሉኛል፣ልጄ ሆይ እንዳይገድሉህ ዝም በል አለው። (የእኛ አንዳንድ ካህናትና ሽሆችም እውነትን የማያስተምሩበት ምክንያት ይህ ነው።) ለሁለቱ ወንድሞቹም ይህን ነገር ነገራቸው። እነርሱም ተቆጥተው ዝም በል አሉት፣እሱም ዝም አለ። ከቋንቋው ጥራት፣ከአሰካኩ ማማር በቀር ከመሐመድ ዝርዝር ይህ ታሪክ በምን ይለያል። ከሰማይ ወረደ የሚለው ተረት ሁሉ ከእሱ በፊት በተጻፈ አዋልድ፣ገድሎች፣ተአ ምሮች ከዐረብና ከትብጥ ወደ ግዕዝ ተተርጉመው በእየ ገዳማቱና አድባራቱ ዕቃ ቤቶች ይገኛሉ።

**10. ሰይጣን ለአዳም አልሰግድ ብሎ ወደቀ፤**

(ሱራህ 2: 34-35) መላእክትም ለአዳም ስገዱ ባልን ጊዜ (አስታውስ) ሁሉም ወዲያውኑ ሰገዱ፤ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ብቻ ሲቀር፣እምቢ አለ፤ኮራም ከከሓዲዎችም ሆነ። (ይህም ከድርሳነ ሚካኤል ጀምሮ በብዙ አዋልድ ተጽፏል።)አዳም ሆይ አንተ ከነምሽትህ በገነት ተቀመጥ፤ ከ፡ሷም በፈለጋችሁት ስፍራ በሰፊው ተመገቡ፤ግን ይህችን ዛፍ አትቅረቡ ከበደለኞች ትሆናላችሁና አልነም። ይህስ ምኑ ነው ሐዲሱ ከሰማይ የወረደው፤(ዘፍ.2: 16-17)

**11. አቤልና ቃኤል፤**

በ፡ሱራህ አምስተኛ በቁጥር 27-32 የተጻፈው ዝርዝርም ከቋንቋው ዝብርቅርቅነት በቀር በዘፍ 4:3-15 የተጻፈ ነው።

**12. ሐሩትና ማሩት፣**

ሐሩትና ማሩት በመላእክት ስም የታወቁት በሱራህ 2:102 የተገለበጡትም የአማርማንያ ጣዖታት ነበሩ። አብያተ መቅደስም ነበራቸው።

**13. የስላምና አዕማደ ሃይማኖት አምስቱ፤**

ከዚህ ቀጥለው የሚዘረዘሩት አምስቱ አዕማደ ሃይማኖትም ከመሐመድ በፊት በዐረቢያ፣በቅዱሳት መጻሕፍት የነበሩ ናቸው። ከዚ.ዮ በፊት በእየአምልኮቱ በእየመንደሩ የኖሩትን አሁን ደርሶ መሐመድ ከሰማይ ወረዱልኝ ያላቸው ለሽርሽር ሂደው ሲመለሱ አግኝቷቸው እንደ ሆነ እንጂ ለመኖር ከእሱ በፊት ከአብርሃም ጀምሮ በመካከለኛው ምሥራቅ ለሁለት ሺህ ዘመናት የኖሩ ናቸው።

ሀ. ከሁሉ አስቀድሞ አላህ አንድነው፣(መሐመድ የአላህ መልክተኛ ነው ግን ለፖለቲካ የተጨመረች ናት) የዚህ ጀማሪ በእየመጻሕፍቱ በኦሪት፣በወንጌል፣በራሱ በቁርአን እንዳየነው አብርሃም ነው፤ቀጥሎም ሙሴ፣ከዚያም በእየዘመኑ የተነሡ እንደነ ኤልያስ ያሉ ነቢያት በመጨረሻው እራሱ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔርን አንድነት ገልጠው አስተምረዋል፣አምልኮ ጣዖትን አውግዘዋል።

መጀመሪያ ጣዖት ማለት ምን ማለት ነው? (በዘፀ.20:3-5) ከኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ። በላይ ከሰማይ ካለው፣በ፡ታችም በምድር ካለው፣ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር፣የማንኛቸውንም ምሳሌ፣ የተቀረጸውን ምስል ላንተ አታድርግ። አትስገድላቸው አታምካቸውም ም እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ ነኝና። (ማር.12:28-30) ጌታ ኢየሱስም ስለዚህ በጠይቁት ጊዜ የሚከተለውን ተናግሯል፤ከጻፎችም አንዱ ቀርቦ ሲከራከሩ ሰማና፣መልካም አድርጎ እንደ መለሰላቸው አስተውሎ፣ከሁሉ አንደኛዋ ትእዛዝ የትኛይቱ ናት?"ብሎ ጠየቀው፣

ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው" ከትእዛዛቱ ሁሉ አንደኛዋ እስራኤል
ሆይ! ስማ!ጌ ታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤
አንተም በፍጹም ነፍስህ፤በፍጽም አሳብህ፤በፍጹም ኀይልህ፤ጌታ
አምላክህን ውደድ የምትል ናት።"
ስለ ካዕባ ስላም ሁሉ ጣዖት አይደለችም እያለ ይከራከራል፤መሐመድ
ም ራሱ ቤተ መቅደስዋ ሲሠራ ልብሱን አንጥፎ ከኮሬሽ መኳንንት
ጋራ ሆኖ አሸራሽቷታል። ሌላውን የዐረቢያን ጣዖት ሁሉ እየዞረ
አጥፍቷል። ደካሞችን ጣዖታት አጥፍቶ ካዕባን አከብሯል። ከዚያ
ተያይዞ፤ስላም ሁሉ የራሱን ጣዖት አስቀምጦ በእየሀገሩ እየዞረ ቤተ
ክርስቲያን ያቃጥላል።ንዋየ ቅዳድሳትን ይዘርፋል፤ዓላማው ፖለቲካ፤ሀገ
ር መውረር፤ሐሳቡ ዘረፋ ነውና።
መሐመድ ለምን ይችን ጥቁር ደንጊያ አላጠፋም? የዚህ መልስ በጣም
ቀላል ነው፤ምክንያቱ ቢዚኔስ (ንግድ) ነው።ብመላ ዐረቢያ ያለው ጣዖት
ሁሉ ከጠፋ ካዕባም ትከበራለች፤መካውያንም ከዓለም በሚመጣው
ሳሚ ገንዘብ ይከብራሉ፤ይበለጽጋሉ። መሐመድም ለጦር ዘመቻ ተከታ
ይ ያገኛል፤አግኝቷል።
ከነዚህ ላይ አንድ የራሴ ገጠመኝ ትዝ ይለኛል፤
አንድ ዘመን ጣሊያንና ለመማር ሮም ነበርሁ፤ንደኛ ስሌለኝ በሚያጋጥ
መኝ ሰው ሁሉ እለማመድ ነበርና አንድ ቀን ከትዱስ ጴጥሮስ
ካቴድራል ተነሥቶ ወደ ራሱ ሱቅ የሚሄድ ነጋዴ አብሮኝ ተሳፋረ።
እኔም እንደ ልማዴ ከንፈሬን ዘርበብ አደረግሁና ሞኝ ለመምሰል፤ወ
ደ ካቴድራሉ እያሳየሁ ይህ ትልቅ ቤተ መንግሥት የማነው? ስሙስ
ማን ይባላል ጌታዬ! ብዬ ጠየቅሁት እሱም የጴጥሮስ ካቶድራል ነው
አለኝ። እኔም ማን ይኖርበታል? ወይንስ የምን መሥሪያ ቤት ነው?
አልሁና ጠየቅሁት፤እሱም ይህ ትልቁ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ነው
በዚያ ባጠገቡ የሚኖሩት ግን ፖፑ፤ጳጳሳቱ፤ቀሳውስት፥ካህናቱ ናቸው
አለኝ እያንጠጠ ኮሚኒስት ነኝ ላይ ነውና። እኔም የተናገራቸውን
ቃላት ደግሞ ሁና ፖፕ፤ጳጳሳት፤ካህናት ቀሳውስት ማለትስ ምንድን
ነው? ምንስ ይሠራሉ? አልሁት። እሱም እነሱስ ለሰው ልጅ የሚጠቅም
ሥራ ምንም አይሠሩም። ከሞቱ በኋላ ጽድቅና ኲነኔ የሚባል አለ
እያሉ ጎጋውን ሕዝብ ያታልላሉ፤እያታለሉም ሕዘቡን እየዘረፉ
ሀብታም ሁነው ይኖራሉ። ወይ ግሩም! ይገርማል የእነሱንስ ነገሩኝ
ጌታዬ!ይህን ያህል ድርጅት በስሙ የተሰየመለት ስውሳ ለሀገርዋ ምን
የሠራ ነው? አልሁት። እሱም ከጥፋት ሕዝቡን ከማደንቁር በቀር
ምንም አልሠራ። ፍልስጥኤም ከሚባል ሀገር ዓሣ አጥማጅ ነበረ
ይላሉ። በኋላ ዓሣ ማጥመድ አልሳካለት ሲል ጊዜ አንድ ኢየሱስ

የሚባል ሰውዬ ሙቶ ተነሥቷል እያለ የሮምን ሕዝብ ሰበከውና የቀሳውስትን ማደሪያ አዘጋጀላቸው እለና ተሰባኪ በማግኘቱ ብዙ ወሬ አወራኝ፤ሊቅነቱንም በደንብ ገለጠልኝ። ወሬአችን ደርቶ ሳለ፣ከሱቁ ደረስንና ለማንኛቸውም ና ውረድና ሱቄን ላሳይህ በሚቀጥለው አውቶብስ ትሄዳለህ አለኝና ተያይዘን ወረድን። "ይህ ነው ሱቄ አለኝና ገባን"፤ሁለት ሠራተኞች ነበሩ። ሱቁም ከደጃፉ እስከ ማጀቱ ሮም ባፈራቻቸው ንዋየ ቅዱሳት፣የክርስቶስ፣የማርያም፣የሐዋር ያት፣የጻድቃን፣የፓፓች፣የካህናት ሥዕሎች፣ትርጾ ትርጾች፣መስቀሎች ነበሩ። እኔም ሁሉንም ቃኘሁና ከንፈሬን ሰብስብ፣ግንባሬን ኮፍተር አድርጌ ምነው ሰውዬ ከመንገድ ሃይማኖትን እያጣላህ፣ካህናትን እያቋሸሽህ አልነበረም የመጣኸው? አልሁት፤እሱም ምንም ሳያፍር ይህማ ሥራ ነው፣ሙያ ነው ንግድ ነው አለኝና ዐረፈ።

በዚሁ አንጻር አጅሬ መሐመድም ሙሴ ብልጣብልጥ ነውና ሌሎቹን ጣዖታት አጥፍቶ ካዕባን አንግሦ፣ለራሱ ክብር፣አግኝቶባታል፣ለሀገሩ ንግድ ከፍቶባታል። ምን ይሁን አባቱ ሲወለድ ያላየው፣እናቱ ያላሳደገችው፣እንዳጎታ ፍራሽ በእየደጁ ወድቆ ያደገ፣መጀመሪያም በአርባቻ(ጥጃ ጥበቃ) በእረኝነት ከዚያም የነጋዴ ጎረደማን ሁኖ መላ ዐረቢያን ዙሮ ያየ፣ሰው ያለገንዘብ ክብር እንደሌለው ዐውቆ ያደገ ነው። 15 ዓመት ከምትበልጠው ሀብታም ነጋዴ ሴት አዳሪ ከድጃ ድንግልናውን የሰደደው ለገንዘብዋ ሲል ነው፤እርጅናዋ ሳይሰማው ለገንዘብዋ ብሎ እስከ ዕለተ ሞቷ ሲገዛት ኑሯል። ከእስዋ በኋላም 11 ሴቶች በውበታቸው ሳይሆን በገንዘባቸው አግብቷል። የመጨረሻዋ አይሻም ለእሱ መንግሥት ብሎ ሲዋጋ የሞተ የጦር አለቃው ምሽት ነበረች። እሷንም በገንዘቧ እንጂ በውበቷ አይደለም። መሐመድ ሥጋዊ ጥቅም ገንዘብና ሥልጣን ካየ ዓላማዬ ሃይማኖት ነው እያለ ጦሩን አሰከትቶ፣በይፋን መዝዞ ከተፍ ነው።

14. ካዕባንማ ስላሞች ሁሉ ከሰማይ የወረዳች ናት ይላሉሳ? ለሚል ጠያቂ፣

ሀ. ከሰማይ ብትወርድ ኑሮ እንዴት አብርሃም ባርኳታል፣ተሳልሟታል ይላሉ? የአብርሃምን ታሪክ በሚዘረዝረው ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ያለ ነገር የለም።

ለ. የዓለም ጣዖታት ሁሉ ከሰማይ የወረዱ ይባላሉ እንጂ ከምድር ፈለቁ፣በቀሉ አይባሉም። ለዚሁም የግሪክን፣የሮምን በጠቅላላም የመካከለኛውን ምሥራቅ፣የግብጽን የሃይማኖት ሚቶሎጂ አንብቦ መረዳት ይቻላል፤በተለየም:(ግብሐ19:35-37)የከተማይቱም ጸሓፊ ሕዝቡን ጸጥ አሰኝቶ እንዲህ አለ፣የኤፌሶን ሰዎች ሆይ! የኤፌሶን ከተማ በታላቂቱ

አርጤሞስ ከሰማይ ለወረደው ጣዖት የመቅደስ ጠባቂ መሆንዋን የማያውቅ ሰው ማን ነው? ይህንም የሚከደው ከሌለ ጸጥ እንድትሉና አንዳችም በችኮላ እንዳታደርጉ ይገባል።የመቅደስን ዕቃ ያልሰረቁ፣አማልክትንም ያልሰደቡ እነዚህን ሰዎች ለምን አመጣችኋቸው?——41።
እንደዚሁምየሮማውያን አማልክት እንዲዮስ ፣እነአጵሎስ ፣የባቢሎኑ ማርዱክ፣የፍልስጥኤሞች በዓል፣ዳጎን፣አጵሎን፣ወዘተ. እረስንቱን! እንደዚህ ነበሩ። መሐመድም የእሱን ጣዖት ተቀናቃኝ አጠፋ እንጂ አምልኮ ጣዖትን አላጠፋም።

15. <u>ሐጂ</u>

ሐጂም ከእሱ በፊት የነበረ አሁንም ክርስቲያኑ ሁሉና አይሁድም የሚያደርጉት፣ኢየሩሳሌም ሳሚ፣ላሊበላ ሳሚ እየተባለ የኖረ የሚኖር ነው።

16. <u>ጸሎት</u>፣

ጸሎትም ከብዙ ሽህ ዘመናት ጀምሮ ከዚህ በፊት እንዳየነው በሳባውያን ዘንድ በቀን ሰባት ጊዜ የነበረ መሐመድ ወደ አምስት የቀነሰው ተግባር ነው። ጌታም ሠርቷል፤(ማቴ.6:5-14)

17. የሮመዳን ጻምም በሳብያን ዘንድ ለ30 ቀን እንደ ነበረ ዐይተናል። ታዲያ የመሐመድ አዲሱ ሥራ የትኛው ነው? አንባቢ ሆይ! አስተውለህ ፍረድ፣አመዛዝነህ ተከተል።

18. <u>ምጽዋት</u>፣

ምጽዋት በሦስት ይከፈላል፣አንድ ስለ ሙት ተዝካር፣ሁለት ለነዳያን፣ሦስት ለካህናት መርጃ። ይህም በሦስቱም ዐይነቱ ከመሐመድ በፊት የነበረ ነው አሁንም በእየሀገሩና ሃይማኖቱ ይኖራል፣ይደረጋል።

19. ኑሮውም የጀኒራሎች፣የዘመናውያን ነገሥታት እንጂ የነቢያት አልነበረም፤ (ሱራህ.33:50-57) የተጻፈው ስለመሐመድ መኖሪያ ክብር ነው፣ከዚህ ግን ለብራና ተብሎ 53ን ብቻ ጽፈን እናልፋለን። እናንተ ያመናችሁ ሆይ! መድረሱን የማትጠባበቁ ስትሆኑ ወደ ምግብ ካልተፈቀደላችሁ በስተቀር የነቢዩን ቤቶች (በምንም ጊዜ) አትግቡ፣ግን በተጠራችሁ ጊዜ ግቡ፤ከተመገባችሁም በኋላ ወዲያውኑ ተበተኑ፤በወግ የምትጫወቱ ከሆናችሁም አትዘግዩ፣ማናደዳችሁ ነቢዩን በእርግጥ ያስቸግራል፣ከእናንተም ያፍራል፣ግን አላህ ከእውነት አያፍርም፤ዕቃም ለመዋስ በጠየቃችሁ ጊዜ ከመጋረጃ ኋላ ሁናችሁ ጠይቋቸው፣ በልቦቻችሁ የበለጠ ንጽሕና ነው፤ የአላህንም መልእክተኛ ልታስቸግሩ፣ምሽቶቹንም ከእሱ በኋላ ምን ጊዜም ልታገቡ፣ለእናንተ አይገባችሁም እንዲህ ያለውን በሕይወተ ሥጋ ቀምጦል ጌታ ነው አንዳንድ ያልገባቸው ስላሞች ስራሱ መጠለያ ከሌለው፣ክርስቶስ፣ከኤልያስ ከሙሴ ጋራ ሊያወዳድሩት የሚፈልጉ። እንዲህ ያለው ተራ ነገርስ ከሰማይ ወረደ እንዴት ይባላል? ላስተዋይ አንባቢ በጣም አስቸጋሪ ነው።

ከዚህ ላይስ መሐመድ አዲስ ነገር አመጣ የሚባለው በምኑ ነው? ብዙ ማግባትና ተንደላቆ መኖር፣ከእሱ በፊት በነበሩት ነገሥታት አልነበረም ወይ? እንዲህ ያለውን ጥቅም ያላወረው ልባይ አንባቢ ያስተወለው። እስክ ዚህ ያለው ስለ ቁርአን ይዘት ይበቃንና ስለ ዝብርቅርነቱ ደግሞ ጥቂት እንመልከት።

## ምዕራፍ 19፤

## የቁርአን ምስቅልቅልነት፣

ቁርአን በይዘትም ሆነ በአጻጻፍ ዝብርቅርቅ ነው
ጎጋው እስላም ቁርአንን ቢያውቅ ኑሮ ያቃጥለው ነበር።

ለምን ጎጋው ብቻ መሪዎች ነገሥታት ጀኔራሎች ሡልጣኖች ሸሆችሳ? የሚል ይነሣ ይሆናል። መሪዎች ለሥላጠናቸው፣ሸሆች፣ለደመወዛቸው፣ቃዲዎችም ለክብራቸው ሲሉ እንዲህ ያላቸውን ነገር አይነኳትም፤ዙረ ውም አያይዋትም። ስለዚህ እንዲህ ያለችቱ ነገር ሁሉ እንደኔ ላሉ የዋሃን፣ጥቡዓን ጎጋዎች፣ጽድቅን ለምንፈልግ ናትና ቁርአንና መሐመ ድ ምን እንደሆኑ ሐቋን፣እትጯን ልንገርህ ልባይና ነባይ አንባቢ!ስማ ኝ። የሐዲሷ ቱርክ መሥራች ሙስታፍ ኬማል አታቱርክ (የቱርክ አባት) የቱርክን መኳንንት ሰብስቦ አምስት ሰዓት ሳይቋርጥ አንብቦ ይህ መጽሐፍ አይደለም፣በዚህ አንመራም ብሎ በተሰበሰቡበት አደራሽ መስኮት ወርውሮ ማርማራ ባሕር ጣለው፣ከዚያ በኋላ በቱርክ ምክርቤት ተቋቁሞ የሀገርዋ መመሪያ ሕገ መንግሥት ወጣ፤ተከናንባ ተሸፍና ትሄድ የነበረች ሴትም ስትገለጥ ጊዜ ባል ምሽቱን፣ወንድሞ እኅቱን መለየት አቃተቸውና ሲደናበሩ ጊዜ በዐይነ ርግቧ አጮልቃ ስታይ የኖረች ሴት እኔ ነኝ ምሽትህ፣እኔ ነኝ ወዳጅህ እያለች ራስዋንም ሌላውንም ታስተዋውቅ ገባች።

ለመሆኑ ቁርአን ምን መሆኑን ከመመርመራችን በፊት እንዴት ነው የተጻፈው የተሰበሰበውስ የሚለውን ጥያቄ ብናስቀደም ምን አለ?

ጥሩ!ቁርአን አንድ አዲስ ነገር የሌለበት፣የዐረቢያ አብያተ ጣዖታት ሥነ ጽሑፍ የታመቀበት፣የአዋልድ ተረት የታጨቀበት፣በመጨረሻ ከቅዱሳት መጻሕፍት አልፎ አልፎ የተጻፉበት የፓለታካ መጽሐፍ ነው፤ይህንም እናስከትላለን።

የቁርአን ጸሐፊ ማን ነው? እንዴትስ ተጻፈ?

ለዚህ ጥያቄ መረጃ ለእያንዳንዱ ሱራህ የእስላም ሊቃውንት የሰጡትን መግቢያ ማንበብ ይቻላል።

ከሁሉ አስቀድሞ የቁርአን ጸሐፊ ማነው?

መሐመድ ከሌላ ቦታ እንደ ተገለጠው ዕንለ ማውታ (የሙት ልጅ ስለሆነ የትም ሲወድቅ፣ወድቆ ሲያድር፣ርኩሳን መናፍስት ይቆራኙታ ል፤ተቆራኙተውም በእየሀገሩ በአጉሪዎች ላይ እንደሚታየው ፈረሳችን ሁን ይሉታል፤እሱም ባለመስከንም ይሁን ወይንም እንደ አሩሲ እመቤት አስታሪቂ በማጣት እይታወቅም፣ዛሬ በእየሀገሩ እንደሚደረገ ው በጸበል፣በመስቀል ለማስለቀቅ ይሞከራል፣ተሞክሮ፣ሳይሆን ስለ ቀረ መሐመድ መስቀልን ይጠላል፣በኋላ ግን በካዕባ ይማጠናል፤ከዚህ ወዲህ ይህን ራእይ አየሁ መልአክ ታየኝ እያለ፣በእየጊዜው

ባለውቃቢዎች እንደሚያደርጉት፤ትላንት ይህን ነገረኝ፤ዛሬ ደግሞ እንዲህ አለኝ እያለ ያወራ ጀመረ፤በኋላ ነገሩ እየበረታ ሲሄድ በዚያ ሀገር በታወቀው መልአክ በቅዱስ ገብርኤል ስም ተላከከና ዐረፈ።
ይህን ታሪክ ለመረዳት (GERHARD NEHLS,CHRISTIANS ASK MUSLIMS:ገጽ:44-48)ያንቧል። መሐመድን ይጥው እንደነበረና ዛር ይሁን ጋኔን ያስነራው እንደ ነበረ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መጽሐፍና በሱራሀ፥በሃዲስ ተተንትኖ ተጽፏል። አውሊያ የሰፈረበት ሰው ስለ ሆነ ዛሬ ይህ ቃየኝ ያለውን በቃል ለተከታዮቹ ያስጠናል፤የሆነለት በቃል ያጠናል፤ያልሆነት ደግሞ በሽቆ፤በመጋሬያ፤በግመል አጥንት፤በጥርብ ዕንጨት በሌላም ለቅምቃሚ ነገር ይጽፋል፤በኋላም የወደቀው ወድቆ የተገኘው ተለቃቅሞ መሐመድ ከሞተ በኋላ መሰብሰብ ተጀመረ።
ከድንገተኛው የመሐመድ ሞት በኋላ ዛይድ ኢብን ጣቢት ቁርአንን ሰብስቦ እንዲጽፍ ታዘዘ። እሱም ቀና ቀናዎቹን አላገኘም።
ሀ. ራሱ መሐመድ ያሰበሰው ከመሐመድ እልጋ ሥር ነበረ። በልቅሶው ተደናግጦ ቤተሰቡ ሲሸበር የቤት እንስሳ ላም ይሁን በሬ በላው፤በዚህም ከመጨረሻ ምሽቱ ከአይሻ ጋራ የነበረው፤በመሐመድ የተሰበሰበው ና የጸደቀው ቁርአን ጠፋ።
ለ. አቡ ሙሳ አልአሻሪ ከ300 በላይ ቁርአንን በቃላቸው ያጠኑ ሰዎች ነበሩ፤ከእነዚያም አንዱ እኔ ነበርሁ፤አሁን ግን ከሱራ ባራት በቀር ሁሉም ተረስቶኛል ብሏል። በዚሁ ዐይነት ሌሎች እያረጁ ሲሄዱ ሽቆውም አርጅቶ እየረገፈ፤ ብዙ ሱራሆች ጠፍተዋል።
ሐ. በኋላ ኡስማን ካሊፍ በሆነ ጊዜ የተጻፈውን ቁርአን ሁሉ አስብስቦ የሱን አጽፎ፤ ስላም ሁሉ ይህን ይቀበል ብሎ፤የቀረው በእየሀገሩ እንዲቃጠል አዘዘና ሁሉም ተቃጠለ። የቀረው ሁሉ መሳሳቱን የእሱው ብቻ ልከኛ መሆኑን የሚመሰክር ማነው?
የቁርአንን ጠቅላላ ሁኔታ ለማወቅ ከተጠቀሰው መጽሐፈ ከገጽ (49-65) ያንቧል።
ቁርአን በእየጊዜው የተባለው የተጠራቀመ ስለሆነ ማንኛቸውም ሱራሀ ርእሱን ተከትሎ የተነሣበትን ዓላማ አያብራራም። እያንዳንዱ በዛም እነሰም ሁለት ወይም ሦስት ቁጥር አንድ መጽሐፍ ነው።
እርእስት መቅድም፤ኅዳግ፤መግቢያ፤መደምደሚያ፤ፅንሰ ሐሳብ በቁርአን አይታወቁም። መደጋገም ያበዛል፤የጃጃ ሽማግሌ፤ወይንም አፉን መፍታት የጀመረ ልጅ እንጂ እንኳንስ አምላክና ጤነኛ ሰው የጻፈው አይመስልም። አምላክን ይህን አጻፍህ ከማለት፤ዕብድ ነህ ማለት ይቀላል። ከሽህ ጊዜ በላይ እግዚአብሔር መሐሪ፤ሩኅሩኅ፤ ቸር፥ይቅር

ባይ፣አስተዋይ፣ዐዋቂ ነው እያለ ጽፏል። የጤነኛ ጸሓፊ ጽሑፍ ቢሆን ኑሮ መጠን ይኖረው ነበር።

የቀረው ይቅርና ስለ አብርሃም እምነት ታሪክ እንኳ ዘጠኝ ጊዜ መላልሶ ጽፏል፤እውነት ከሆነ አንዱ አይበቃም ወይ? እርግጠኛ ስላልሆነ ዘጠኝ ጊዜ መላልሶ ጽፏል፡(ሱራሆች፣2: 260፤6: 74- 84፤19: 42-80፤ 21:52-72፤ 26:70-82፤ 29:16-17፤ 37:83-89፤ 43:26 30፤60:4)ከሱ በፊት ቅዱሳት መጻሕፈት፥አዋልድ፣ተአምራት፣ድርሳና ት በመንፈሳዊ ዓለም ተጽፈዋል፣በሥጋዊውም ለቁጥር የሚያስቸግሩ ብዙ የሳይንስ፣የታሪክ፣የፍልፍስና መጻሕፍት ተጽፈዋል። በዘመናችን ካሉት ደራስያን በይበልጡም የሚወዳደሩ፤ቁርአን ግን ዝብርቅርቁ የወጣ በሥነ ጽሑፍም ሆነ በይዘት ከዚህ ግባ የማይባል መጽሐፍ ነው። ጸሓፊውንና ምንነቱንስ አየን፣ለመሆኑ ይዘቱሳ ለሚል ኀጋ (የዋህ) እሱንም ከዚህ በታች እንቀጥልለታለን፤

<u>ይዘት፣</u>

ሀ. መሐመድ አላህ አንድ ነው ይላል (በአካል) አላህ ግን ብዙ ጊዜ በቁርአን እኛ እያለ በብዙ ይናገራል፣ከዚህ ላይ በቁርአን፣መሐመድ ወይስ አላህ ነው የተሳሳተው። እኛ ማለት የእግዚአብሔርን ሦስትነት (በአካል) ይገልጣል። እኔ ማለት ደግሞ በመለኮቱ አንድ መሆኑን ቁርአን ግልጭ አድርጎ ያሳያል። መሐመድ ጤነኛ ባለመሆኑ ሳይረዳው ቀርቶ፣የቀሩት አስተዋይና የዋሃን ስላሞች ግን አስቀድመው ሰምተው የያዙት እውነት መስሏቸው ነው እንጂ መሪዎቹ ግን ከላይ እንነደ ተጠቀሰው ጥቅም ዐውሯቸው ነው።

ለ. (ሱራሀ. 32:12) በሻን ኑሮ ነፍስን ሁሉ ቅን እናደርጋት ነበር፣ግን ገሃነምን አጋንንትንና ሰዎችን ሰብስቤ በእርግጥ እሞላለሁ፣ማለት ቃሌ ከኔ ተረጋግጧል። (ከዚሁ ከአንድ ሱራህ ቁጥር በመጀመሪያ እኛ (ባሻን) ኑሮ ብሎ ብዙነቱን በኋላ ደግሞ እሞላለሁና ከኔ ብሎ አንድነቱን ገልጧል፤(እንደዚህ ያለውን ንባብ በቁርአን ምስጢረ ሥላሴ በሚለው እናየዋለንና እስከዚያ ርእሳችን እንከተል)።

ሁሉን ቻይ አምላክ ያለምንም መመሪያ ወይም መምሪያ ሕግ ሁሉን ያደርጋል።

ሐ. (ሱራሀ.16:93)አላህ በሻኑሮ አንዲት ሕዝብ ባደረጋችሁ ነበር፣ግን የሚሻውን ሰው ያጣምማል፣የሚሻውነም ሰው ያቃናል፣ይሁን እንጂ በሠራችሁት ሁሉ ትጠየቃላችሁ።ኀጋ ወይም የዋህ አንባቢ ሆይ! እስቲ ይህን ቁጥር መላልሰህ አንበው፣መጀመሪያ አላህ የወደደውን ያቃናል፣የጠላውን ያጣምማል ካለ በኋላ ከዚያው ቁጥር በሥራችሁ ትጠየቃላችሁ ይላል፤ እንዲህ ያለ አነጋገር ልክ ነው ወይ? በርግጥ

ይህ የመሐመድ ወይም በመካ ያለው የካዕባ ገዥ እንጂ የኢየሱስ አባት፣የአብርሃም አምላክ የእውነተኛውና የሐቀኛው እግዚአብሔር አይደለም።

መ. ያላመኑትን ደግሞ እንዲያምኑ የሚያደርግ አላህ ነው፤ገሃነምን የሚሞላበት እንዳያጣ፤ (ሱራህ2:6-7) እነዚያ የካዱት ደግሞ ብታስጠነቅቃቸውም ባታስጠነቅቃቸውም ለእነሱ ያው ነው፣አያምኑም (ምክንያቱም)አላህ በልቦቻቸው ላይ፣በመስሚያቸው ላይ፣አትሞባቸዋል ና፣ዐይኖቻቸውንም በመሸፈኛ ጋርዷል። በእነሱም ላይ ታላቅ ቅጣት አለባቸው።ይገርማል! አላህ የሰውን አእምሮ አዙሮ፣ዐይኑን ዐውሮ፣ል ቡን አነሁልሎ ደግ ነገር እንዳይሠራ ካደረገ በኋላ፣ራሱ ባጠፋው ጥፋት ዐቅም የለሹን ሰው ይቀጣል። ይህም ድመት የያዘቻትን አይጥ ዐውራ እንደምትጫወትባት ማለት ነው። ለዚህም አስተዋይ አንባቢ የሰላሞች አላህ ጨካኙ ግፈኛው፣አምባ ገነኑ፣ፍርደ ገምድሉ፣አምልኮ ቱን የካዕባ ጥቁር ደንጊያ የምትጋራው የእኛው ቸሩና እውነተኛው አምላክ አምላክ አብርሃም አይደለም ከማለት በቀር ምን ይባል?

ሠ. በጠቅላላው ለሰው ዘር ደግሞ፣እንዲህ ብሏል፣(ሱራህ.7:179) ከጋኔንም ከሰዎችም ብዙዎቹን ለገሃነም በእርግጥ ፈጠርን፣ልብ አላቸ ው አያውቁበትም፣ዐይን አላቸው አያዩበትም፣ጆሮ አላቸው አይሰሙበ ትም፣እነዚያ እንደ እንስሶች ናቸው፤ይልቁንም እነሱ በጣም የተሳሳቱ ናቸው፤እነዚያ ዘንጊዎች እነሱና ቸው፡ሰዎችና አጋንንት አያዩም፣አያስ ተውሉም፤ምክንያቱም አላህ ገሃነምን ለሞምላት ፈጥሯቸዋልና ይላል።

ረ. ከፍ ብሎም 178 ቁጥር ላይ፣አላህ የሚያቃናው ሰው ቅን እሱ ነው፤የሚያጣምመው እርሱ ከከሳሪዎች አንዱ ነው። ብዙ አጋንንትንና ሰዎችን ለጋሃነም ፈጥረናልና።

ሰ. (ሱራህ 4:88)ግብዞችን አላህ በሥራቸው ወደ ክሕደት የመለሳቸው ሲሆን፣ከሁለቱ የተከፈላችሁ እናንተ ምን አላችሁ? አላህ ያጣመመውን ሰው እናንተ ልታቃኑ ትችላላችሁን? አላህ ላሳተው ሰው መንገድ ፈጽሞ አታገኝለትም።

ቀ. (ሱራህ.11:118-119) ጌታህም በሻ ኑሮ ሰዎችን ሁሉ አንድ ሕዝብ ያደርጋቸው ነበር ከመለያየት ግን አይድኑም። ጌታህ ካዘነለት በቀር የቀሩትን ለገሃነም መሙያ ፈጠራቸው፤የጌታህም ቃል ገሃነምን በአጋንንትና በሰዎች አንድነት እሞላለታለሁ ትላለች።

በ. (ሱራህ 14: 4) ከመልክተኛ ማንኛቸውንም ለእነሱ ያብራራላቸው ዘንድ በወገኖቹ ቋንቋ እንጂ በሌላ አልክንም፤አላህም የሚሻውን ያጠማል የሚሻውንም ያቀናል፤እሱም አሸናፊ ጥበበኛ ነው።ይህ በብዙ ሱራሆች ተደጋግሟል፣(35:8፣74:31)

ተ. (ሱረቱ 6:149)የተሟላው ማስረጃ ያላህ ነው፣ቢፈልግ ኖሮ ባቀናችሁ ነበር በላቸው።
ሃዲስ ለዚህ አጽንዖ ነገር የሚከተለውን ዘግቧል፤ሁለት ሰዎች ጻድቅና ኃጥእ ካንድ መንደር ይኖሩ ነበር። ሁለቱም ሞቱና ጻድቁ በሲኦል ሲሠቃይ፣ኃጥኡ ግን በገነት ሲፈላሰስ፣ይማሙ አየና ምነው አላህ እንዲህ ያለ ግፍ ብሎ ጠየቀ፤አላህም ከፉ ቀበል አደርጎ ጭጭ በል በገዛ ገንዘቤ የፈለግሁትን አደርጋለሁ አለው። ለአንባቢ የሚያታክቱ ስለ አላህ ፍርደ ገምድልነት ከቁርዓን ለመጥቀስ ይቻላል። ለዚህ እስከዚህ ይብቃንና ወደ ሌሎች አርአስት እንዙር።
ቸ. ከዚህ በታች ደግሞ ሌላው ዝብርቅርቅና መፍለስ ይቀጥላል፤(ሱራቱ 4: 7) በቁጥር 7 ውርስ እኩል ይሁን ብሎ ካዘዘ በኋላ በ11 ደግሞ ለወንድ ሁለት እጅ ለሴት ሢሶ ብሎ ሽሮታል፤ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተውት ውርስ ለወንዶች ግማሽ ክፍል ለሴቶችም ግማሽ ክፍል አላቸው፤በዚህም እኩል አካፍሉ ብሎ ማዘዙ ነው። ከዚያም ቀጥሎ ግን፣በ11 አላህ ለልጆቻችሁ ውርስ ሁለት እጅ ለወንድ ሢሶ ለሴት አዝዞዋል ብሏል። በዚሀም ከአዳም እኩል አድርጎ የፈጠራትን ሴት የወንድ ግማሽ ማድረጉ ነው።
ነ. (ሱራቱ. 73: 2)ሌሊቱን ሙሉ ጥቂት ሲቀር ስገድ (ጸልይ) ካለ በኋላ ወዲያው በ20ኛው ቁጥር ሽሮታል፤አንተ ከሌሊቱ ከግማሽ ያነሰውን ግማሹንም፣ሢሶውንም የምትቆም መሆንህን ጌታህ በእርግጥ ያውቃል ሌሊቱን የማታደርሱት መሆናችሁን ዐወቀ፤ስለዚህ ከቁርአን የተቻላች ሁን አንብቡ ብሎ አቃሏል።
አ. (ሱራሀ. 4:15)ሴቶች ካመነዘሩ ዕድሜ ልክ ይታሰሩ ይላል። በሱራሀ 24 :2 ደግሞ አመንዝራዎቹን መቶ መቶ ግረፏቸው ብሏል፣የትኛው ነው እውነት?
ከ. በደል መመለስ ይልቁንም ነፍስ መግደል እንደ ሱራሀ 2:178 በማዕረግ እኩል፣ደጃዝማች ከደጃዝማች፣ጀኔራል ከጀኔራል ነጻ ከነጻ፣ ሐራ ከሐራ፣ባሪያ ከባሪያ ነበር። እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በተገደሉት ሰዎች ማመሳሰል በእናንተ ላይ ተጽፏል፤ነጻ በነጻ፣ባርያም በባሪያ፣ሴትም በሴት——።
ይህ ከእሬት በፊት የነበረ፣ሰው በገነዘብ እንጂ በሰውነት በማይመዘንበት ጊዜ የነበረ የአረማውያን፣የአሕዛብ ሕግ ነው። እርሱም ከሱራሀ 5 :45 ጋራ ይጣላል፤በእርሱም ላይ በውስጧ ነፍስ በነፍሷ ዐየን በዐይን፣አፍንጫ፣በአፍንጫ፣ ጥርስ በጥርስ፣ጆሮ በጆሮ ቁስሎችንም እንዲሁ ማመሳሰል አለባቸው ብለን ጻፍን።

ወ. በተከበሩት ወሮች አትዋጉ ብሎ ካዘዘ በኋላ በዚያው ሱራህ አፍርሶታል፤(ሱራህ 9: 5-36)የተከበሩት ወሮች ባለቁ ጊዜ፣አጋሪዎቹን ባገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሏቸው ያዟቸውም እነሱንም ለመግደል በመንገድ አሸምቁ ———::የወሮች ቁጥር በአላህ ዘንድ በአላህ መጽሐፍ ውስጉ ሰማያትንና ምድርን በፈጠረበት 12 ወር ነው፣ከእነ ሱ 4 የተከበሩ ናቸው፣ይህ ቀጥተኛው ሃይማኖት ነው፤በእነሱ ውስጥ ነፍሶቻችሁን አትበድሉ፣አጋሪዎችንም በአንድ ላይ ሁነው እንደሚዋጓ ችሁ በአንድ ላይ ሁናችሁ ውጓቸው።

ዐ. ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ከሀ እስከ ወ ባሉት ሆሄያት አላህ ያለምንም ሕግና ገደብ ይምራል፣ይኮንናል፣ያጸድቃል ያሠቃያል ሲል ኑሮ አሁን ደግሞ በሱራህ 3:57ለእነዚያ ለአመኑትና መልካም ሥራዎ ችንም ለሠሩት አላህ ምንዳቸውን ይከፍላቸዋል ብሎ ልክ ሊሰድበው እንደ መጣ እንደ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ጽድቅን በእምነትና በሥራ አድርጎት ዐረፈ። ቀድሞስ በእየሳምንቱ ከሚያጎራና ከሚጥለው ሰው ምን ይጠበቃል?

ዘ. ቁርአን (ስላም)ክርስቲያኖች በሦስቱ ሥላሴ (አማልእክት) ያምናሉ እነሱም አብ፣ማርያም፣ወልድ ናቸው። በዚህ የማይደነቅ ክርስቲያን የለም።ሥላሴ ሦስት አካላት፣ በመለኮት አንድ ናቸው ይህን በምስጢረ ሥላሴ ይመለከቷል። ለጊዜው ግን ሥላሴ አብ፣ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው፣ማርያም የመለኮት ልጅ፣ክርስቶስ በሥጋ የተወለደባት ንጽሕ ሰው እንጂ አምላክ አይደለችም።

የ. የክርስቶስን እናት የሙሴ እኅት አድርጓታል፣በሁለቱ መካከል 1500ዘመን አለ።የክርስቶስን አያት ሐናና የሳሙኤልን እናትም አንድ አድርጓቸዋል። ምን ይሁን በማያውቀው ነገር የሚቀባጥር ሁሉ እንዲህ ካለ የስሕተት ገደል ገብቶ ይወድቃል።

## ምዕራፍ 20፣

## ቁርአን ከክርስትና ምን ያምናል?

ቁርአን ከጌታችን ስቅለትና ሞት ትንሣኤ በቀር የቀረውን ሁሉ ይቀበላል፣ኦሪትን ከነቢያት ጋራ፣ወንጌልን ከሐዋርያት ጋራ አጠቃሎ ይቀበላል። ለሙሴ ኦሪትን፣ለኢየሱስ ወንጌልን አወረድነ፣ሰጠነ ይላል፤

1. **ኦሪትና ወንጌል፤** (ሱራህ.3:3፤44-48) ኦሪትንና ወንጌልንም አውርደናል። እኛ በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባትን ኦሪትን አወረድን። ትእዛዝን የተቀበሉት ነቢያትም አይሁድን በእሷ ፈረዱ፣ ረበናትና ካህናትም እንደታዘዙት በዚሁ በእግዚአብሔር መጽሐፍ ምስክር ነበሩ። ሰዎችን አትፍሩ፣ እኔን ፍሩ፣የእኔን አስተርአየም በአነስተኛ ትርፍ አትለውጡ። እግዚአብሔርም ባወረደው ነገር የማይፈርድ ከሓዲ ነው። በእሷም ውስጥ ነፍስ በነፍስ፣ዐይን በዐይን፣ አፍንጫ በአፍንጫ፣ጆሮም በጆሮ፣ጥርስ በጥርስ፣ቁስልንም በቁስል መልሳችሁ ቅጡ ብለን ጻፍን። በርሱም ይቅር ያለ ይቅር ይባላል፤እግዚ አብሔር ባወረደው ነገር የማይፈርድ በደለኛ ነው በነቢያት ፈለግ ላይም አይሄድም።ብፊቱ የተሰጠችውን ኦሪት የሚያጋግጥም የማርያም ን ልጅ ኢየሱስን ላክን። በውስጡም ቀጥታና ብርሃን ያለበትን ከእሱ በፊት የነበረችውን ኦሪትን የሚያረጋግጥ፣ለጠንቃቆች ሰዎች መሪና ተግሣጽ የሚሆን ወንጌልን ሰጠነው። የወንጌልም ባለቤቶች እግዚአብ ሔር ባወረደው ይኑሩ። እግዚአብሔር ባወረደው ሕግ የማይኖር ዐመፀኛ ነው።

በዚህም ኦሪትና ወንጌል የእግዚአብሔር የሕጉ መጻሕፍትና ኢየሱስም የእግዚአብሔር መልእክተኛ መሆኑን በዝርዝር አስረድቷል።

2. (5:68-69) እናንተ የቅዱሳት መጻሕፍት ባለቤቶች፣እስራኤልና ክርስቲያን! ከጌታችሁ ወደ እናንተ በወረዱት በኦሪትና ወንጌል ካል ሥራችሁ እናንተ ምንም አይደላችሁም በላቸው፤——ያመኑ ሁሉ አይሁድም፣ሳባውያንም፣ክርስቲያንም በእግዚአብሔር ካመኑና በመ ጨረሻው ቀን ካመኑ፣በጎ ሥራ ከሠሩ ፍርሃት የለባቸውምም፣ አያዝኑ ምም። ያጠናክራሉ፤የሚከተሉት ሱራሆች ደግሞ ይህንኑ ሐሳብ ያጠናሉ፤(29:45 ፤10:35፤ 46:11 ፤6:91፤ 35:31፣ 2:40-42)

3. <u>የኢየሱስን የእግዚአብሔር ቃልነትና በድንግልና መወለድ፤</u>
ከዚህ በፊት (ሱራህ. 4:171) እንደ ተጠቀሰው፤እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ!በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፣በእግዚአብሔርም ላይ ከእውነት ሌላአ ትናገሩ፤የማርያምልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብ ሔር <u>መልክተኛና ቃሉም ነው</u>፣ከእሱ የሆነ መንፈስም ብቻ ነው።

4. ከዚህ በፊት የተጠቀሰውን ሱራህ 19:17-22፤ 2:253: ያነቧል።

በዚህም የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ብሏል፣ይህም የእግዚአብሔር ቃል ወልደ አምላክ፣አምላክ ማለትን ው፣ልክ ክርስትያን እንደሚያም ነው።

<u>የኢየሱስን ነቢይነት፤</u>

5. ለዚህም በቁጥር አንድ በዚሁ አንቀጽ የተሰጠውን መልስ ያነቧል።
6. (ሱራህ.3:45-49)———፣እሷም ጌታዬ ሆይ ወንድ ሳይነካኝ ለእኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል አለች፤ነገሩ እንደዚህ ነው፤እግዚአብሔር የፈለገውን ያደርጋል፤እንዳችን ነገር በሻ ጊዜ፣ሁን ይለዋል፣ወዲያውም ይሆናል። ጽሕፈትና ጥበብንም ኦሪትንና ወንጌልንም ያስተምራዋል። ወደ እስራኤል ልጆችም መልክተኛ አድርጎ ይልከዋል። በዚህም የማርያምን ድንግልነት የኢየሱስን መልክተኛነትና ነቢይነት ገልጧል።

## ምዕራፍ 21፣

## ስልምና የክርስቶስን መስቀል ይክዳል፤

በመሐመድ ታሪክ እንደ ተገለጠ፣መሐመድን ባሪያ ይጥለው፣መንፈስ
ርኩስ ያንቀጠቅጠው ያስጎራው ስለነበረ በዙሪያው የነበሩ አይሁድና
ክርስቲያን በመስቀልና በጸበል ለማስለቀቅ ያስቸግሩት ስለነበረ
መስቀልን አይወድም:ስለዚህም የመስቀልን ፍሬያት፣መገፈፍን፣መገረ
ፍን፣መሞትን፣መሰቀልን፣ትንሣኤን፣ዕርገትን ካደና ዐረፈ። የሚመኘ
ውም በጦር መሪነት ዓለምን ለመግዛት ነውና ብዙ ተከታይ ለማግኘት
ከእሱ በፊት 600 ዘመን ዓለም ተቀብሎ የኖረን ሃይማኖት ክዶ፣ከዐረ
ቢያ ጣዖታት አንዲት ካዕባ ጥቁር ደንጊያ አስቀረ። ለአስተዋይ
አንባቢ የቁርአን ሂደትና ይዘት እንዴት እንደሆነ እንዲገባው ከሱራህ
4:155-159 ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን። ቃል ኪዳናቸውንም በማፍረሳቸ
ው በአላህም አንቀጾች በመካዳቸው፣ነቢያትንም ያለጥፋት በመግደላቸ
ውና ልቦቻች ሽፍኖች ናቸው። በማለታቸው ምክንያት (ረገምናቸው)
በእውነቱ በክሕደታቸው ምክንያት አላህ በእሷ ላይ አተመ፣ስለዚህ
ጥቂትን (ጥቂቶች) አያምኑም። (አይሁድን ነው) በመካዳቸውና
በማርያምም ላይ ቅጥፈትን በመናገራቸው(ረገምናቸው)። እኛ የእግዚአ
ብሔርን መልክተኛ የማርያምን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ገደልነ
በማለታቸውም ረገምናቸው። አልገደሉትም፤አልሰቀሉትም፤ግን ለእነ
ሱ የገደሉት ሰው በኢየሱስ ተመስሎ ታያቸው። በእርሱ ነገር የተለያዩ
ትም በመጠራጠር ውስጥ ናቸው። ከመጠራጠር በስተቀር በእሱ ነገር
ምንም ዕውቀት የላቸውም። በእርግጥም አልገደሉትም። ይልቁንም
አላህ ወደ እሱ አነሣው፣______፤ ከመጽሐፉ ሕዝብ፣ከሞቱ በፊት
በእሱ የማያምን የለም፣በዕለተ ትንሣኤም እሱ ይመሰክርባቸዋል።

የቁርአን ነገር በፊት የተናገረውን ረስቶ ሁለት አንቀጽ እንኳ
ሳይጽፍ፣አልሰቀሉትም፣አልገደሉትም ብሎ ከካደ በኋላ ይልቁንም
አላህ ወደ እሱ አነሣው አለና በገዛ ራሱ ሲለፈልፈው የቆለን ሁሉ
አፈረሰና ዐረፈ። ካልሞተ ምኑን ነው የሚያነሣው?የጌታችን ተሰቅሎ
መሞት በትንቢት በአሪት የተነገረ፣በአያሁድ የተረጋገጠ፤በሐዲስ
ኪዳን በራሱ በክርስቶስ፣በሐዋርያት የተመሰከረ፣ተመሰክሮም እየተሰ
በከ ከመሐመድ በፊት ለ600 ዘመን የኖረ ዛሬም በክርስቲያኑ ዓለም
የሚታመን፣ለወደፊቱም ይህን መጽሐፍ ያነበቡ ስላሞች ሁሉ የሚቀበ
ሉት ሐቅ ነው። የዚህን መረጃ በሰፊው ለማወቅ ከክርስቶስ በኋላ ነቢይ
የለም የሚለውን ምዕራፍ ያንቧል።

ክርስቶስ ተቀብሮ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት አላደረም ብሏል አያ
ዲዳት። ይህ ጥያቄ የአይሁድን የቀን አቆጣጠር ከማያውቁ ጎጋዎች
እየተነሣ መልስ ሲሰጥበት ኑሯል።

እያ ዲዳትእክርስትና ደካማ ነጥብ አገኘሁ ብሎ (በድንቁርናው፣ባለማወቁ ይሆናል የሚምቦጠረረው) ዘመን የሚቆጠረው፣ዕለት የሚታሰበው እንደ ቋንቋው፣ባህሉና አካባቢው ነው። በዚሁ መሠረት የእኛና የምዕራባውያን የሰዓት አቆጣጠር ይለያያል። እኛ 12: ስንል፣እነሱ 6፣ስንል እነሱ 1፣4: ስንል 10: ወዘተ. ይላሉ። የአይሁድን የሚከተለው የእኛም ዕለት ከምሽቱ በ12 ጀምሮ በበነጋው በ12 መጀመሪያ ላይ ይጨርሳል። የምዕራብያውያኑ ግን በመንፈቀ ሌሊት ጀምሮ በመንፈቀ ሌሊት ይጨርሳል። በዚህ ምክንያት ነው። የእኛ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ዐርብ ማታ ከ12 ሰዓት በኋላ የቅዳሜን፣ቅዳሜ ደግሞ የእሑድን፣እሑድ የሰኞን ወዘተ. የሚሉ፣የሚያደርሱ የሚያስታኩቱ። ዋዜማም የክብረ በዓል መጀመሪያ ነው። በቀን አቆጣጠር ሦስት ውሳኔዎች አሉ፤ ዕለት፣መዓልት፣ሌሊት። መዓልት ፀሐይ ያለበት 12 ሰዓት ነው። ሌሊት ደግሞ ፀሐይ የሌለበት 12 ሰዓት ነው። ዕለት፣(ቀን) መዓልትንና ሌሊትን 24 ቱንም ሰዓት ያሳያል።

በአይሁድ፣በቤተ እስራኤል አቆጣጠር፣ከአንድ ዕለት አንድ ሰዓት ከተነሣለት፣በሙላ ዕለቱም መዓልቱም ሌሊቱም እንደ ተወሰደ ነው የሚቆጠረው። ይኸውም አንድ ሰው እጁን ሰጠ ወይም ተያዘ ሲባል በሙላ አካላቱን መሆኑን እንደሚያሳየው ማለት ነው። በዚህ ሒሳብ መሠረት ጌታ ዐርብ ሊያልቅ አንድ ሰዓት ሲቀረው በዐሥራሐንድ ሰዓት ተቀብሯል። ስለዚህ የዘዬ አነጋገር ነውና ዐርብ በሞላ ይመጣል፣ይቆጠራል፣በአንድ ሰዓት ምክንያት ሌሊቱም መዓልቱም ተቆጥሯል። ቅዳሜ በሞላ ሌሊት ሁለተኛ ዕለት፤ከእሑድ በመንፈቀ ሌሊት ምክንያት ስድስት ሰዓት አለ፣በሙላ እሑድ ይመጣል፣ሦስት ዕለት፣ሦስት መዓልት፣ሦስት ሌሊት ይሉሃል፣ይህ ነው። ቀን ግን ሌሊትንና መዓልትንም በጠቅላላ 24 ሰዓትም ወይም መዓልቱን ብቻ ፀሐይ የምታበራበትን ጊዜ ብቻ ስለሚያሳይ በዓለ አሻሚ ትርጉም በመሆኑ እንዳያሚታ እንዲህ ባለ ጊዜ አንጠቀምበትም።

ጌታ ራሱ ከሞቱ አስቀድሞ የሰው ልጅ እንደ ዮናስ ሦስት ዕለት በከርሠ መቃብር ያአድራል ብሎ የተነባው በዚህ ትርጉም ነው። ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ከነገደ እስራኤል ተወልዶ በአረማይስጥ ሲናገር ኑሮ ነው የሞተው። ከትንሣኤው በኋላም ይናገረው የነበረ አረማይስጥ ነው። ክዚህም በላይ ጌታ መቼ ሙቶ፣መቼ ተቀበሮ፣መች እንደ ተነሣ በሦስቱም ወንጌላት ቁልጭ ብሎ ተጽፏል። የዮናሱ ግን መቼ? በምን የሳምንቱ ዕለት፣በመቼ ዘመን የሚል የለውም። ሦስት ቀን (ይህንም መዓልት ትርጉም) ሦስት ሌሊት በዓሣው ሆድ ውስጥ አደረ (ዮና.2:1-2) ብሏል። ከዚህ ላይ መቼ

ተነሥቶ መቼ እንደ ጨረሰ ስለማያሳይ ትንቢቱ ተመስና በተነገረው በፍጻሜው ይታወቃል። ለምን ቢሉ ትንቢት ያመለክታል፤ፍጻሜ ግን ይወስናልና። ዮናስ ነቢይ ሲሆን፤ክርስቶስ ግን ወልደ አምላክ ሊተ ነቢያት ነውና። የመጣውም ትንቢታትን ለመፈጸም ነውና። በአጠቃላይ በነሲብ ዮናስ ከዓሣው ሆድ ሦስት መዓልትና ሌሊት አደረ ተባለ እንጂ በቁርጥ 72 ሰዓት ቆየ አልተባለምና።

የዮናስን በዓሣ ሆድ ሦስት ቀን ማደር፤እስራኤልም፤ክርስቲያንም በዓለ ቁርአኑ ስላምም ያምናል። 72 ሰዓት በዓሣ ሆድ ነበረ የሚል ግን ከእነ ዲዳት በቀር የለም። ጌታም የተናገረው በመዓልትና በሌሊት እንጂ ሰዓት ወስኖ 72 ብሎ አይደለም፤(ማቴ.12:39-40) ——እሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው፤ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፤ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም። ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሦስት ቀንና (መዓልት) ሦስት ሌሊት እንደ ተቀመጠ (ነበረ) እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል። የሰው ልጅ አለ፤የተሰቀለና የሞተ፤የተቀበረ በሰው ልጅነቱ (በሥጋው ነውና) ስለዚህ የዮናስን ታሪክ በክርስቶስ መረጃነት ያስተካከሏል እንጂ በነሲብ በጅምላ የተነገረውን ለዝርዝር መረጃ አያደርጉትም፤አይደረግም።

እያ ዲዳት ኢየሱስ እውን ፈጣሪ ነውን? በሚለው ከታቡ ከ 19-27 ለወተወተው ቅጅት ሰዓትን በተመለከት ከዚህ በላይ በዝርዝር ተመልሷል። ዮናስ ሕያው ነበረ፤ክርስቶስሳ ሕያው ነውን? ብሎ ጠይቋል፤ይህ መልስ አምንታም አሉታም ነው፤ምክንያቱስ ቢሉ፤ክርስቶስ ሞተ ሲባል ነፍስና ሥጋው ተለያዩ ማለት ነው እንጂ መለኮት ከሥጋው ከተዋሐደ በኋላ ተለያየ ማለት አይደለም፤መለኮት ከሥጋ ጋራ በለበሰው ሥጋ መቃብር ወርዷል፤ከነፍስ ጋራ ደግሞ በመንፈስ ሲኦል ወርዶ፤ሲኦልን በርብሮ ከእሱ በፊት ለነበሩት ነፍሳት ሁሉ ነጻነትን ሰብኮ አድኖ በሦስተኛው ቀን ተነሥቷል።(1ጴጥ.3:18) በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፤በእርሱም ደግሞ ሂዶ በወሕኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፡፡ ከዚህም በላይ ጌታ፤የሰው ልጅ፤ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው በምድር ውስጥ ሦስት ቀንና ሌሊት እንደ ዮናስ ያድራል አለ እንጂ ሙቶ ወይም በድን ሁኖ አላለም፤በዚህም ዘለዓለም ሕያው አምላክ መሆኑን ያሳያል። የጭቀ ነገር፤በማየውቀው ገብቶ እንጂ መልሱ ይህ ነው።

## ምዕራፍ 22፤

## ስልምና የኢየሱስ ነቢይነት ያምናል፤

ቁርአን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃለ አብነት በድንግልና መወለድ፣ነቢይነ ት፣ወደአባቱ ወደአብ ማረግ ቁልጭ አድርጎ ይጽፋል ይጽፍና መልሶ ለፖለቲካ ሲል፣ክርስቲያን በወሲብ ነው የወለደው ይላል፣ የሚል አስመስሎ ያጭበረብራል። ክሕደቱ የፖለቲካ ሙግት እንጂ የሐቅ አይደለም። ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች ለአንባቢ እናቀርባለን፤

1. ከዚህ በፊት በምዕራፍ 2እንዳየነው በሱራህ 4:171ቁርአን የኢየሱ ስ ክርስቶስን ቃለ እዚአብሔርነት ቁልጭ አድርጎ ተናግሯል፤"የማርያ ም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መልእክተኛና ቃሉም ነው፣ከእሱ የሆነ መንፈስም ብቻ ነው። ከዚህ ላይ ቃልና መንፈስ እንደ ልማዱ ተማቶውበታል። መጻሕፍትና ክርስቲያንም እግዚአብሔ ር ወልድን፣ኢየሱስ ክርስቶስን ቃለ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ቃል) የእግዚአብሔር ልጅ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ይሉታል።

ሀ. (ዮሐ. 1: 1-3)በመጀመሪያ ቃል ነበር፤ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፤ቃልም እግዚአብሔር ነበር፤ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፣ሁሉ በእርሱ ሆነም፤እንዳችም ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም

ለ. (14) ቃልም ሥጋ ሆነ፣ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፣አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው የሆነውን ክብር አየን፣—

——።

ሐ. (ገላ.4 :4) ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን፣ከሕግ በታችም የተወለደውን ልጁን ላከ። እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ፣ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ። ልጆችም ስለሆናችሁ እግዚአብሔር አባ!አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ።

መ. በመለኮቱ የአምላ: ልጅ ነሥጋው ደግሞ የዳዊት ዘር ነው። (ማቴ.22:42፤47 ፤ሮሜ :ን

ሠ. የእግዚአብሔርን መን ... ዚህ ታውቃላችሁ፤ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ ... የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ደግሞ ከእግዚአብሔር አይደለም። ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፣ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል። (1ዮሐ.1:2-3)

2. (ሱራህ:2:87) ለሙሲም መጻሕፍትን በእርግጥ ሰጠነ፣በኋላውም ብዙ መልእክተኞች አከታትለን ላክን። ለማርያም ልጅ ለኢየሱስም ላዕላዊነቱን የሚገልጹ ብዙ ታምራቶች ሰጠነው። በቅዱስ መንፈስም አበረታነው።

3. (136) በእግዚአብሔር፣ሙሴና ኢየሱስም በተቀበሉት፣ነቢያትም ከጌታቸው በተቀበሉት እናምናለን።
4. (253) ለማርያም ልጅ ለኢየሱስም ግልጥ ማስረጃ ሰጥተን በመንፈስ ቅዱስ አጸናነው።
5. (4:158)እግዚአብሔር ወደ ራሱ ወሰደው።
(ሱራህ.42:13)ለእናንተ በሃይማኖት ኖህን ዶዘዝንበትን ደነገግንላችሁ፤ወደ እናንተ ባወረድነው አብርሃምን ሙሴን ኢየሱስን ባዘዝነው ሃይማኖት ጸንታችሁ እንድትኖሩ አዘዝናችሁ።
7. ለማርያም ልጅ ኢየሱስም ወንጌልን ሰጠነው። (57:27)
8. ወደ ማርያም የመጣ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ቃሉ፣ከእሱ የሆነ መንፈሱም ነው።
ቃለ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ) ከዚህ ሌላ እኛስ ምን እንላለን? ልጅ ስንል እኮ ከእግዚአብሔር አብ ከአንደበቱ የሚወጣ ማለት እንጂ እንደ ሰው በግብረ ወሲብ ወለደው ማለት አይደለም። የማርያም ልጅም ስንል በግብረ መንፈስ ቅስዱስ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ ከዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በኋላ ተወለደ ማለት እንጂ በመለኮቱ የአብ ልጅ ከማርያም ህላዌውን ጀመረ ማለት አይደለም። አስተዋይ አንባቢ ስላም ሁሉ ወልደ አብ በመለኮቱ ወልደ ማርያም ብትስብቱ ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበሬ ማለት ምን እንደሆነ መረዳት ይገበዋል፤በውኤት ሙግት ጉንጭ ለማልፋት ሳይሆን፣እውነትንና ጽድቅን ከፈለገ።
9. (42:13)አብርሃምንና ሙሴን ኢየሱስንም ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ በዚያም አትለያዩ ብለን ደነገግን።
10. (57:26-27)ኖህንና አብርሃምንም በእርግጥ ላክን፣በዘራቸውም ነቢይነትንና መጻሕፍትን አደረግን። ከዘራቸውም ቅንም ዐመፀኛም አለ። ቀጥለንም መልእክተኞቻችንን አከታትለን ላክን፤የማርያምን ልጅ ኢየሱስንም ወንጌልን ሰጥተን አስከትለን ላክን። በተከተሉትም ርኅራኄና ይቅርታን ሞላን።
11. (111:45-50) መላእክት ያሉትን አስታውሥ፣ማርያም ሆይ! እግዚአብሔር ከእርሱ በሆነው ቃል፣ስሙ ክርስቶስ ኢየሱስ የማርያም ልጅ፣በዚህ ዓለምና በመጭው ዓለም የተከበረ ከባለሟሎች በላይ በሆነ ልጅ ያበሥርሻል፤በሕፃንነቱና በጎልማሳነቱ ሰዎችን ያነጋግራል፤ከመ ልካሞችም ነው። "ጌታዬ ሆይ! ወንድ ያልነካኝ ስሆን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል?"አለች።ነገሩ እንደዚህ ነው፣እግዚአብሔር ሚሻውን ይፈጥራል፣አንዳች ነገርን በሻ ጊዜ ሁን ይለዋል፣ይሆናል አላት። ጽሕፈትንና ጥበብን፣ኦሪትንና ወንጌልን ያስተምረዋል። ወደ እስራኤልም ልጆች

መልእክተኛ ያደርገኛል፤ይላልም እኔ ከጌታዬ ዘንድ በታምር መጣሁላ ችሁ——::

12. (19:17-22) መንፈሳችንንም ወደ እሷ ላክን፤ፍጹም ሰው መስሎ ታያትናፕ "እኔ ንጹሕ ልጅ ላንቺ ልሰጥሽ (የመጣሁት) የጌታሽ መልእክተኛ ነኝ" አላት። እሷም ወንድ ሳይነካኝ፤አመንዝራም ሳልሆን ለኔ ልጅ እንዴት ይኖረኛል? አለች። እሱም ነገሩ እንደዚህ ነው፤እሱ በእኔ ላይ ገር ነው፤ለሰዎችም ታምር ች ሮታ ልናደርገው የተፈረደ ነገር ነው ብሎ እና አለባት ወዲያውም አረገዘችው።

ለኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብነት። ለእግዚአብሔር አብ ቃልነት በቁርአን የተጻፈ ብዙ ጥቅሶች አሉ። ነቢይነቱም ከዚህ በላይ እንዳየነው በሰፊው ተገልጧል። የሰላም ነገር፤ስለመሐመድ ሐሳዊ መሲሕነት እያነበቡ ይከዷሉ። ለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ ስለመሐመድ የሚለውን ምዕራፍ 15ን እንደገና ከዚህ ጋራ ያገናዝቧል። ሳያውቁና ሳያጠኑ የሚዘላብዱት የእነ እያ ዲዳት አፍ ካላረፈ የእኛም መልስ ይቀጥላል።

# ምዕራፍ: 23፤

## ከመሐመድ የሚያንስ ነቢይ የለም፤

ነቢይ አይደለም እንጂ ነቢይ ቢሆንም ኑሮ ከመሐድ የሚያንስ ነቢይ የለም። ከክርስቶስ በፊት የተነሡትን ነቢያት ሁሉ ራሱ እግዚአብሔር በገሃድ በድምፅ በረአይ ስለ ጊዜውና ስለ ክርስቶስ መምጣት አነጋግሯቸዋል። ከክርስቶስ በኋላ ግን ራሱ ክርስቶስ ትንቢትን ፈጽሞ ሂዷል፤ሐዋርያትም ትንቢታትን ሁሉ እይመለሱ እየገረቡ፤እየቀለሱ ሲያስተምሩ ኑረው አልፈዋል። ስለ ሐሰውተ መሲሕ፤ስለውሸታም እንደ መሐመድ ያሉት ነቢያትም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደ ታየው አፍረጥርጠው ለአስተዋይ አንባቢ ገላልጠው ጽፈዋል።

ለዚህም የሚከተለውን እናቀርባለን፤

1. (ዘፍ.6:1-12-13) እግዚአብሔርም ኖኅን አለው፤የሥጋ ሁሉ ፍጻሜ በፍቴ ደርሷል፤በእርሱ የተነሣ ምድር በግፍ ተሞልታለችና እኔም እነሆ ከምድር ላይ አጠፋቸዋለሁ። ከጎፈር ዕንጨት መርከብ ላንተ ሥራ፤ በመርከቢቱም ጉርዶች አድርግ፤ በውስጥም በውጭም በቅጥራን ለቅልቃት፤(ከ ፲:እስከ ምዕራፍ ስምንት መጨረሻ ያንቧል)

2. (ዘፀ.3:2--------:) የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾክ ቁጥቋጦ መካከል ታየው፤እነሆ ቁጥቋጠው በእሳት ሲነድ ቁጥቋጦውም ሳያቃጠል አየ። ሙሴም ልሂድና ቁጥቋጦው ለምን እንዳልተቃጠለ ልይ አለ። እግዚአብሔርም ሊመለከት እንደመጣ ባየ ጊዘ ከቁጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ ሙሴ! ሙሴ ሆይ!አለ። እርሱም እነሆኝ አለ። ወደዚህ አትቅረብ፤የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው። ደግሞም እኔ የአባትህ አምላክ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለው። ከዚህ ቀጥሎ አራቱ የአራት ክፍሰ ሁሉ ከእግዚአብሔር ና ከሙሴ መካከል የተደረገ የወዳጅ ንግግር ነው። ጠንቅቆ ያንቧል። (በተለይም ዘኍ.12: ምዕራፍን ጠንቅቆ ያንቧል)

3. (ኢያ.1:1-9) እንዲሁም ሆነ የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ከሞተ በኋላ፤እግዚአብሔር የሙሴን አገልጋይ የነዌን ልጅ ኢያሱን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤______9:)

4. (1:ሳሙ.3:3-14) ዔሊም በስፍራው ተኝቶ ሳለ፤የእግዚአብሔርም መብራት ገና ሳይጠፋ፤ሳሙኤልም በእግዚአብሔር ታቦት ባለበት በእ ግዚአብሔር መቅደስ ተኝቶ ሳለ፤እግዚአብሔር ሳሙኤልን ጠራው። እሱም እነሆኝ አለ፤ወደ ዔሊም ሩጦ እነሆኝ የጠራኸኝ አለው____ ዔሊም እግዚአብሔር ብላቴናውን እንደ ጠራው አስተዋለ_______ና ሳሙኤልን ሂደህ ተኛ፤ቢጠራህም አቤቱ!ባሪያህ ይሰማልና ተናገር በለው አለው፤ሳሙኤልም ሂዶ በስፍራው ተኛ።

እግዚአብሔርም መጥቶ ቆመና እንደ ቀድሞው ሳሙኤል!ሳሙኤል ብሎጠራው፤ሳሙኤልም ባሪያህ ይሰማልና ተናገር አለ እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው——————14። 16:1-4፤
5. ቴስብያዊው ኤልያስንም ብዙ አናግሮታል፤(ቀዳ. ነገ 17:1-7)
6. (ኢሳ.6:1-13)ኢሳኢያስንም አነጋግሮታል።
7. (ኤር.ምዕራፍ አንድን በሙሉ)ለኤርምያስ እግዚአብሔር አነጋግሮታል።
8. ሕዝቅኤልም በመላ መጽሐፉ የጌታ እግዚአብሔር ቃል ወደኔ መጣ እያለ ነው የሚናገር።
9. (ሆሴ.1:2) እግዚአብሔር በመጀመሪያ በሆሴዕ በተናገረ ጊዜ እግዚአብሔር ሆሴዕን ምድሪቱ ከእግዚአብሔር ርቃ ታላቅ ግለሙትና ታደርጋለችና ሂድ፤ጋለሞታን ሴትና የግልሙትናን ልጆች ለአንተ ውሰድ አለው።
10. (7:1፣ 1-4) አሞጽ ደግሞ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አሳየኝ——።
11. ኢዮኤልም በመላ መጽሐፉን ከእግዚአብሔር እንደ ሰማው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እያለ ጨርሶታል።
12. (ዮናስ ምዕራፍ:1-4) የእግዚአብሔር ቃል ወደ አማቴ ልጅ ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ።
13. በቀሩት ነቢያት ግን የእግዚአብሔ ቃል በነቢዩ በእገሌ እጅ የእግዚአብሔር ቃል መጣ እያለ ነው የተነገረው። ይህን የመሰለ ከነቢያት መጻሕፍት ሁሉ መጥቀስ ይቻላል። ይህም የነቢያትን ሁሉ ከመሐመድ መብለጥ ያሳያል።

# ምዕራፍ 24፣

## የጥናቱ ውጤት ባጭሩ፣

ይህ ምዕራፍ በዚህ መጽሐፍ የተደረገውን ጥናት ባጭሩ ለማጠቃለል የተዘጋጀ ነው።

ዓላማትን ከነንዛቸው የፈጠረ፣ፈጥሮም የሚጠብቅ የሚያስተዳድር የሚመግብ እግዚአብሔር አንድ ነው።
አንድ አምላክ ነው። ሳይረዱና ሳያውቁ ስም ለማጥፋት ሰላሞች እንደሚያወሩትም ሦስት አምላክ የሚል ክርስቲያንም የለ። እሉም በሦስትነትና በአንድነት፣በዚህ መጽሐፍ ባጭሩና በሁሉም ይወቅ በሰፈው በምዕራፍ አንድ እንደ ተገለጠው እምቅድመ ዓለም ኑሯል፣አሁንም አለ፣ለመጭውም ለዘለዓለም ይኖራል። መጀመሪያና ፍጻሚ፣ኅልፈት የለበትም።

አንድነቱና ሦስትነቱን ለማስረዳት ሊቃውንት ብዙ ምሳሌ ያስማሉ። አንደኛ ትክክል ሁነው በወጡ ሦስት ባላ ባለው አንድ ትልቅ ዛፍ ይመስላል፤በግንዱ(ሥሩ) መለኮታቸው ነው፣አይለያዩም። ሦስቱ፡ሥላሴ፣ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። እነሱም በስም፣በግብር፣በአካል ይለያያሉ፣በመለኮት፣በባሕሪይ፣በህልውና፣በሥልጣን፣በዘመን፣በመንግ ሥት አንድ ናቸው።

<u>በስም</u> አብ፣ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ።

<u>በግብር</u> አብ ይወለዳል(በቃል፣በአንደበት)፤ያሠርጻል፤በእስትንፋስ፤ወ ልድ ይወለዳል እንደኛ አነጋገር በአንደበት፣መንፈስ ቅዱስ ይሠርጻል (በእስትፋስ)

<u>በአካል</u> ሦስቱም ፍጹም ፍጹም አካል አላቸው። አካል ፔርሶን በሚል ትርጉሙ። ቅውምና ህልው መንፈስ እንጂ የማይታይ የማይዳሰስ። የሚዳሰስ፣የሚታይ ሰውነት ያለው ግን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔ ር ወልድ ብቻ ነው፣ሥጋ ስለለበሰ፣ዓለምን ለማዳን ሰው ስለሆነ። የሁለቱም የወልድና የመንፈስ ቅዱስ መገኛ አብ ነው፣ይህም ስለተባለ በዘመን አንድናቸውና አይቀዳደሙም፣አንዱም ከሌላው አይበላለጡም ስለዚህም ፀሐይን ይመስላሉ። ፀሐይ ሦስት ግብር አለው፤አካሉ (ፍሕሙ)ሙቀቱ፣ብርሃ ኑ፡ሦስቱም አካሉ ሲገኝ የተገኙ ናቸው፣አይቀ ዳደሙም። በፍሙ (በአካሉ) አብ፣በሙቀቱ ወልድ፣በብርሃኑ መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ። ፀሐይ ሦስት ግብሩን ይዞ፣እንደያዘ አንድ ፀሐይ እንደሚባል፣እግዚአብሔርም በሥላሴነት ሦስት አካል፣ሦስት ስም፣ ሦስት ግብር ሲኖረው፣እየኖረው አንድ አምላክ፣አንድ እግዚአብሔር ነው፣ይባላል። እግዚአብሔር በሥላሴነት ብዙ ዘመን ካሳለፈ በኋላ በአርያው፣በአምሳሉ ሰሙን እንዲቀድስ መንግሥቱን እንዲወርስ፣ አዳምን ፈጥሮ ገነትን እንዲኮተኩታት በገነት አኖረው። ገነት ግን መከነ ፍሥሓና፣ዓለመ ተድላ ስለሆነች ዲያብሎስ ቀንቶ አታለለውና

አትብላ ያለውን ዕፅ በልቶ ከአምላኩ ተጣልቶ፤ከገነት ወጥቶ በምድረ
ፍዳ በመከነ ኩነኔ በችግር በሥቃይ ሲኖር ጊዜ ወደ ፈጣሪው በንሥሐ
አመለከተ። ፈጣሪውም ሐዘኑን ሰማና ጸሎቱን ተቀበለና አንድያ ልጁን
በፈቃዱ ላከ። እሱም በተለየ አካሉ ከሰማይ ሰመያት ወርዶ ከድንግል
ማርያም ተወልዶ በፈለገ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆ በእደ
አይሁድ ተገፎ፣ተገርፎ፤በዕፀ መስቀል ተሰቅሎ፤ሥጋውን ቆርሶ፤ደሙ
ን አፍሶ ራሱን ስለአዳም ሠውቶ፣ለአባቱ ራሱን ንጹሕ መሥዋዕት
አድርጎ አቅርቦ፣ፍጹም ካሣ ከፍሎ፤ ከሲኦል ሥቃይ፣ከግብናት ዲያብሎ
ስ አዳምን አድኖ፤በሞተ በሦስተኛው ቀን ከመቃብር ተነሥቶ፤በተነ
ሣ በዐርባኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣላቸው ለሐዋርያት
ተስፋ ሰጥቶ፤ ዐርጎ በክብር በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ። መንፈስ ቅዱስም
በዐሥረኛው ቀን መጥቶ፣ሐዋርያትን በልዩ ልዩ ቋንቋ አናግሮ፤ደካሞ
ቹን አጥንቶ፣ፈሪዎቹን አደፍሮ፤ዲዳዎቹን አርትቶ፤ቤተ ክርስቲያንን
መሥርቷል። በዚህም በኦሪትና በወንጌል የተነገረ ትንቢት ተፈጽሟል፣
ተገርብቷል። ከእንግዲህ ወዲህ ሐሳዊ መሲሕ፤ሙሽታም ነቢይ ይነሣል
ተጠንቀቁ ተብሎ ተነግሯል፤ይህ ከሆነ ከ600 ዘመን በኋላ የተነገረው
የጥፋት ትንቢት ደርሰና መሐመድ ተነሥቶ በሰይፍ ብዙ ዓለም
አስካደ።

የመሐመድ፤ምንነትና የቁርአን ከሰማይ አለመውረድ በእየምዕራፉ
አሳይተናል፤እንዳየነው ቁርአን ከሱ በፊት የተነገረ አፈ ታሪክ፤ከመጽ
ሐፈ ባልቲት፤ከአዋልድ የተጠራቀመ ተረት፤መሐመድም ጥቁር
ደንጊያ ጣዖት ካዕባ የምትባል የሚያመልክ፤ባሪያ የሚጥለው እዶ ክብ
ሬ የሚያስጎራው፤ጋኔን ሳቢ፤ቀማኛ፤አመንዝራ፤ጨካኝ፤አረመኔ ኃጣው
እን ሁሉ ለመፈጸም የተፈጠረ የሚመስል ፍጡር እንደሆነ ተገልጧል።
ቀና ኅሊና ያለው እንባቢ ቀናውን መንገድ እንዲይዝ ይረዳ ዘንድ ይህ
መጽሐፍ ቀርቧል፤የእግዚአብሔር መንፈስም በዚህ መጽሐፍ ብዙዎቹ
ን አንባቢያን እውነትን ያውቁበት ዘንድ እንዲረዳ፤ እንድትጸልዩ
ትለመናላችሁ።

አምላክ ሆይ! ያነበብነውን በልቡናችን አሳድርልን። አሜን።

መለሰ፦ተለበሰ ገረባ
መለትስ አምላክና ሰው በአንድ አካል
መስጊድ የስላም ቤተ ጸሎት፤
መደዴ የልተማረ፤ግርፍጥ፤ባላገር፤ገልቱ።
ምኩራብ የአይሁድ ቤተ ጸሎት
ምድረ ፍዳ የቅጣት ዓለም።
ቁርአን ከሰማይ ወረደ የሚሉት የስላም ዋናው መጽሐፍ፤ስላሞች ከሰማይ ወረደ ይበሉት እንጂ፤ውስጡ ሲጠና ግን ከሱ በፊት በነበሩት አረ ታሪክ፤አዋልድ፤መጽሐፈ ባልቲት፤ታልሙድ፤በልጆች ተረት፤የሚጉላ ቤት ጭዋታ የተሞላ ነው። እሱም ተጠቅልዩ ተጠርገ ከሰማይ ወረድሁ አይልም።
ባሪያ ማለው የሰማዩ፤ያየሩ ጥሎ አረፋ አስደፈቀው፤አፈራገጠው።
ትብብአት፤ ሥጋ፤ ሰውነት
አላህ፤ በመካ ቤተ መቅደስ ከነበሩት ጣዖታት የቁራሽ ነገድ አምላክ ስም ነበር። የተመረጠውም በመሐመድ ነው እንጂ የተራ ጣዖት ስም ነው የነበረው። ከዚያ የተነሣውን ዛሬ ዐረቦች ለአምላካቸው ማሳያ ይጠቀሙበታል። አላህና ካዕባ ምንም ቢሆን ከጣዖትነታቸው አይዘሉም አገልጋያቸውም መምለኪ ጣዖት ነው።
አርባዕ በሳምንት አንድ ቀን ዐርብ ወተት ለማግኘት ጥጃ ጥቢያ።
እዩ፦ ብዙ ልምድ ያለው፤ሲያበላ ሲያጠጣ የኖረ።
ካዕባ በመካ ቤተ መቅደስ ውስጥ ከነበሩት 360 ጣዖታት መሐመድ መርጦ ያስቀራት ጣዖት ጥቁር ደንጊያ ናት። እንደ ጥንት ጣዖታት እንደነ ኤፌሶኒቱ አርጤምስ፤እንደ ባቢሎኑ ማርዱክ እንደ ፍልስጥ ኤማውያኑ ዳጎንና አጽሎን ወዘተ. ከሰማይ ነው የወረደች ይሏታል፤ በዚያ በኩል ያላለፉት እነ አብርሃምም ስግደውላታል ይባላል። በደንብ ለመረዳት ባሏ ሲከበር እሷንም ሰጋጅንም በተለቢዥን ደኅና አድርጎ መመልከት ይቻላል። ልሙጥ ጥቁር ደንጊያ ናት፤ጽሕፈት ይሉ ቅርፅ የላትም። ስልምና ለአርት ጥበብ ደመኛ ስለሆነ። ስላም ሁሉ ይህችን ደንጊያ ትቶ የአብርሃምን አምላክ ቢአምላክ ከአምልኮ ጣዖት በወጣ ነበር። መሐመድ ሌሎቹን ጣዖታት ሲሰብር ይህችን የተወበት ምክንያትም የቁሬሾች አምላክ ወይም ቆሌና አድባር ስለሆነችና ለቱሪስት ገቢ መሳቢያ እንድትሆን ነው።
ጅብርኤል በቅዱስ ገብርኤል ስም ስላሞች የሚጠሩት፤መሐመድን ያስኀራ፤ በመሐመድ ላይም ሲወርድ የነበረ ርኩስ መንፈስ ነው።
ጅሐድ ስላም በሃይማኖት እያመካኘ ቅዱስ ጦርነት ነው እያለ ጎጋውን አታሉ፤መደዴውን አሠልጥና ሀገር የሚወርበት ክርስቲያንና አይሁድን የሚያጠፉበት በጭካኔ የታጠቀ፤አረመኔነት የለበሰ የክተት

ዐዋጅ ነው። በዚህ ጦርነት የሞተ ገነት ይገባል፣የተዋቡ ብዙ ሴቶችም ያገባል፣እሳቱም ከሦስተኛው ሰማይ ድረስ ወርዶ ይቀበለዋል። ያሸነፈም እንዳጋጠመው ብዙ ወርቅና ብር ይዘርፋል፣ድላብ ያፍላል፤ንብረት ይቀማል፣ወንዱን ገድሎ ምሽቱን ያገባል፣ሕፃናቱን ይሸጣል፣መሬቱን ይወርሳል። በኋላ ሲሞተም ይጸድቃል ይባላል።

<u>ገሪባ</u> የተዘረጋውን ምንጣፍ ወይም ጀንዲ መለስ፣ከዚህ ትንቢቱ መፈጸሙን ነገረ።

<u>ጋጥ</u> ከቤት ከብት የሚያድርበት ክፍል።

## የተነበቡ መጻሕፍት

መልስ ለመስጠት የተነበቡ ክታባትና መጻሕፍት፣
ሐሰን ኤም በዐጊል (ዶር) ክርስቲያን ሙስሊም ውይይት፣ነጃሺ ኢስላሚክ አሳታሚና ኦዲዮቪዥዋል ድርጅት።
ማንሕ: ሐምማድ አልጀሀይኒ (ዶር) ስለ ኢየሱስ እውነተኛ መረጃ፣ ሁዳ ፕሬስ ሊምትድ፣1989። (ቁርአን እንጂ አልኹሊ፣ሌላ በጣልጠቀሰ ለመረጃነት አያገለግልም)
መሐመድ ዐሊ አልኹሊ፣እስላምና ክርስትና፣ ሁዳ ፕሬስ ሊምተድ፣ 1997፤
(የራሱን ተረት ነው የሚያወራው፣መጽሐፍ ቅዱስን አይቀበልም፤ ስለዚህ የመጽሐፈ ባልቴት ተረብ እንጂ ቁም ነገር የለውም)
ቁርአን (በሁለት መልኩ አገልግሏል)
አሕመድ ዲዳት፣(ከጋዜጣ አንቀጽ የማይበልጡ 5 ክታባት (መጣጥፍ) በትኗል (ለሁሉም በመጽሐፉ ውስጥ መልስ ተሰጥቷቸዋል)
ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለመሐመድ፣ነጃሺ እስላሚክ አሳታሚና የኦዲዮቪዥዋል ድርጅት፣አዲስ አበባ፣1985።
ለ. መሐመድ ከክርስቶስ በኋላ የተነሡ የመጨረሻ ነቢይ፣ሳሚር ሬድማን፣አዲስ አበባ፣1986።
ሐ. ሙሐመድ የታላላቆች ታላቅ፣ ነጃሺ እስላሚክ አሳታሚ ድርጅት፣አዲስ አበባ፣ታኅሣሥ 1987።
መ. ኢየሱስ እውን ፈጣሪ ነውን? ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፣1988።
ሠ. ክርስቶስ በኢስላም፣ ነጃሺ ኢስላሚክ አሳታሚና ኦዲዮቪዥዋል አገልግሎት ድርጅት
አልቡአልዕላ አልመውዱዲ፣ሰብአዊ መብት በኢስላም፣ኢስላማዊ ደዕዋና ዕውቀት ማኅበር፣አዲስ አበባ 1986።
አቡል አዕላ መውዱዲ
ሀ. ቁርኣንን ለመርዳት፣ነጃሺ ኢስላሚክ አሳታሚና የኦዲዮቪዥዋል አገልግሎት ድርጅት፣አዲስ አበባ፣ሐምሌ 1987። ይህ ክታብ የተበተ ነው የቁርኣንን መዝረጥረጥና ጉድለት ግድፈት፣ሐሰት በአንድምታ ለማከምነው፤ግን ከመፈወስ ይልቅ ይብሱኑ አቁስሎታል፣አሳምሞታል
አብደላ ሙ ሁሴን፣ኢስላምን ለምን መረጥን? አፉን የጽሕፈት መሣሪያና መጻሕፍት መደብር፣አዲስ አበባ፣1987።
ሉ. የደዕዋ ስዎች ሥነ ምግባር፣ ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ 1989።
ዐብደላ ሙሐመድ ዓሊ፣ግብፃዊቷ መነኩሲትና ፈረንጆች ሊቃውንት በኢስላም ጎዳና 1987።

ጀማል አልበዳዊ (ዶ/ር) የሴቶች ደረጃ በኢስላም፣ኢስላማዊ ዳዕዋና ዕውቀት ማኅበር፣አዲስ አበባ፣1985፣ ጊርሃርድ ኔለስ፣
ሀ. ውድ አብደላ
ሐ. የናቢ ዒሳ መልክት::
Slam Our Choice Impressions of Reverts to Islam 3rd edition 1993, Dawah, Academy Islamabad Pakistan.
AddArul Qayyimah Is the Black stone an idol? Bhiwandi, Bombay,India 1975.

## ለዚህ ጥናት የሚጠቅሙ መጻሕፍት፤

**መጻሕፍት ቅዱሳት**
ሡልጣን መሐመድ ካሃን፤ የጽድቅ ጥያቄዬ፤ (ይህ ጥሩ ጥናት ነው) አዲስ አበባ፤ጥቅምት 1987።
አልኪታብ የሕይወት መጽሐፍ፤የመጻጻፍ ትምህርት።
ጎድፍሬይ ዴይል፤(ቄስ) እስልምናና አፍሪቃ፤ በእንግሊዘኛ ተጽፎ በጎበዜ ጣፈጠ ተተረጎመ) ንግድ ማተሚያ ቤት፤1949። GERHARD NEHLIS
A, Christian Answer Muslims, July 1992.
B, Christians Ask Muslims, 1S BN 1992

ይህ መጽሐፍ ለጊዜው የተወረወረ መቆያ ነው። ሰፊው ጥናት ግን በራሳቸው ከታባት (መጣጥፍ) ፤ቁርአን፤ሃዲስ፤ልዩ ልዩ የትርጉምና ራሳቸው የሚያምኑባቸው የሐተታ ምንባባት አስረጅነት መሠረት ይቀጥላል፤ማንኛቸውም ሰላም የክርስቶስን ሙቶ መነሣት አምነ እውነቱን እስካልተቀበለ ድረስ መልሱ ይቀጥላል። ለዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ይርዳን።

## የዚህን መጽሐፍ አጠቃላይ ይዘት በአጭሩ የሚገልጥ መወድስ።

ኩሉ ይከውን ለፖለቲካ (አው በፖለቲካ ይትዌለጥ ታሪክ ዓለም)
ኃጥእነ ምግባር ጻድቃነ ወእረማዌ እሚን ክርስቲያን
ኄሠሥተ ፍትው ሢመት ባሕታውያን
መሐመድ በእንተ ዝንቱ
አጥፍአ ጣዖታተ ባዕድ ወያመልክ እብነ
ጸሊመ እንተ ካዕባ
በእኩይ መንፈስ አጥፍዖተ ዓለም አመ ወጠነ።
ኢብሊስሂ (ሰይጣን) ለደምስሶ ዘዐማኑኤል አሚነ
ተሰይመ ጅብሪልሃ ወዓለመ አማሰነ
ንብረተ ኅሊፊት ዓለም እመ ከመዝሰ ኮነ
በገዲፍ ተድላ ዚአሃ ይኄይስ ዘመነነ።